ቁም-ነገር አልባነት
ተጽዕኖ ፈጣሪ ሲሆን
6

የወቅቱ ቁልፍ ጥያቄ
‹‹አለም አቀፉ ፍርድ ቤት
ወይም ኤርትራ››
7

‹‹አዋጅ የሚያወጡት ማጥቃት
የሚፈልጉት ሰው ሲኖር ነው››
አጥናፍ ብርሃኔ [ጦማሪ]
8

የዴሞክራሲ ቀለሞች፤
ከሽግግር እስከ ችግግር
10

ስንቱን የሀገር ሀብት
አጣን?!
12





# የኢትዮ-ኤርትራ ዳግም ፍጥጫ


የድኅረ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ አሰቃቂ ሁኔታና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ! ......................... 15

ከግጥም ጋር በፍቅር የወደቀው ሐያሲ ......................... 19

በመንገድ ላይ... ......................... 20

ብሉይ ወይም ሐዲስ ኪዳን? ......................... 21

“እንደ-ራሴን እንደ መፍትሔ” ......................... 22

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ......................... 24

የቃና ቲቪ
አብዮትና የፈጠረው ስጋት ......................... 26

ጠቡ የሻዕቢያ እና የሕወሃት እንጂ የሕዝብ አይደለም! ......................... 28

የማታ ታክሲዎች ባሕርይ ......................... 29

ቅጥ ያጣው ቤት ......................... 32

16




‹‹እስከ ዛሬ ሥልጣን ስለ ምናሸጋግርበት
መንገድ አልሠራንም››
አቶ የሺዋስ አሰፋ



‹‹የኢሕአዴግ ትልቁ ስሕተት
አንድነትን ማፍረሱ ነው››
አቶ ሀብታሙ አያሌው



‹‹ኢሕአዴግ የብጥብጥ መንገድን ትቶ
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚታረቅበትን
መንገድ ማሰብ አለበት››
አቶዳንኤል ሺበሺ

# ዳግም በወንድማማቾች ፍጅት መክሰር አንሻም!

የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ሕዝቦችን ‹‹የጫካ ፖለቲከኞች›› ለሁለት ከፈሏቸው እንጂ አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ ነበሩ። ዛሬም ቢሆን ሁለቱ መንግሥታት ፀብ ገጠሙ ማለት ሕዝቡ አንድነቱ ተዛብቷል ማለት አይደለም፤ ያሳለፏቸው ታሪካዊ ውጣ ውረዶች እንደተጠበቁ ሆነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ የራሷን አስተዳደር ከጀመረች 23 ዓመታትን አስቆጥራለች። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የአዲስ አበባውና የአስመራው መንግሥታት በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች ሲቆራቆዙ ከርመዋል። ይህ መቆራቆዝም ወደ ድንበር ይገባኛል ውዝግብ አምርቶ በ1990 ዓ.ም ጦርነት ውስጥ እስከ መግባት መድረሱና የ80 ሺህ ወንድማማቾች ሕይወት መቅጠፉ ይታወቃል። ይህ አንዱ አሳዛኝ ታሪካችን ነው። ከዚያ ጦርነት በኋላም አልፎ አልፎ መተነኳኮሱ አልቀረም። ኢሕአዴግ በተለያዩ ጊዜ ሻዕብያን ‹‹ዋነኛ ጠላታችን ነው፤ አሸባሪዎችን አሰልጥኖ ሊያተራምሰን ቀን ከሌሊት አይተኛም›› በማለት ሲከስ፣ ሲወነጅል ኖሯል፤ ዛሬም ድረስ ይኸው ክስ ቀጥሏል። የኢሳያስ አገዛዝም ቢሆን ህወሃት/ኢህአዴግን ሲከስና ሲወነጅል ኖሯል፤ ክሱ ዛሬም ድረስ አልቆመም።

በሁለቱም ሀይላት በኩል ሰላማዊ መግባባት ዛሬም ድረስ ሊደርስ አልቻለም። ይባስ ብሎም በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በጾረና ግንባር ሁለቱም አንዱ አንዱን እየወነጀለ ውጊያ መጀመራቸውን ሰምተናል። ተፈጠረ ለተባለው ችግር አንዱ አንዱን ከመወንጀል ዛሬም አልቦዘነም። ይህ ምንያህል የቂም በቀልኝነት ስሜት በሁለቱም መካከል መኖሩን የሚያሳይ ነው። ይህ መጥፎ ስሜት የሁለቱም ሀገራትን ህዝቦች በሙሉ ይወክላል ብላ ‹‹አዲስ ገጽ›› አታምንም። ኢትዮጵያን አስመልክተን ስንናገር ዛሬ አይደለም ሌላ ብዙ ዋጋ ሊያስከፍል ጦርነት ውስጥ ሀገሪቷና ህዝቦቿ ሊገቡ ቀርቶ አሁንም በዘርፈ ብዙ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ችግሮች ውስጥ እየዳከርን እንገናኛለን። ሰፊው ሕዝቦቿም በአስከፊ ጭቆና፣ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ በድህነት፣ በድርቅ፣ በረሃብ እንዲሁም በነጻነት፣ በዴሞክራሲና በፍትህ ዕጦት እየዳከሩ ነው። ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ሀገሪቷ እኛ ሕዝቦቿ ተሸክመው እየኖሩ ባለበት በዚህ አስከፊ ሰዓት ጦርነትን ለመሸከም የሚችል ጫንቃ ሊኖረን አይገባም ብለን እናምናለን።

ትናንት በባድመ ጦርነት የብዙዎች ሕይወት እንዲሁ በከንቱ መፍሰሱና መሬቱም በኢትዮጵያ እጅ መደላድል ሳያገኝ ቀርቷል። በአደባባይ አስጨፍሮን ከእጃችን የወጣው መሬት ላይ የተሠራው ታሪካዊ ስህተትም መቼም አይረሳም፤ አይዘነጋም። ዛሬም ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ በሚል ሰበብ ዳግም ለመሸወድ የሚፈቅድ የበዛ የዋህ ሕዝብ አይኖርምም። ስለዚህ ለጥቂቶች ለሥልጣን መደላድል ተብሎ ብዙሃን ለሞት የሚማገዱበት የሴራ ፖለቲካ ማብቃትና ማክተም እንዳለበት ‹‹አዲስ ገጽ›› ታምናለች። በከንቱ አንሸዋዋድ! በተሰለቸ ፕሮፖጋንዳና ዳግም የወንድማማቾች ፍጅት ኪሳራ ላይ አንውደቅ! በአገር ውስጥ ያሉትን ውጥረቶች ክስቱ ያበርደዋል ወይም ያስረሳዋል ተብሎ ከታሰበ ደግሞ ትልቁ ስህተት መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን።


በኤድፋይ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግል ማኀበር በፖለቲካ፤በኢኮኖሚ፤በማኀበራዊና በኪነ-ጥበብ ጉዳዮች ላይ የምታተኩር በየ15 ቀኑ ለህትመት የምትበቃ መፅሔት

**ዋና አዘጋጅ**
ኤልያስ ገብሩ
elias.gebru@addisgets.com
elias.gebru12@gmail.com
የካ ክ/ከተማ
ወረዳ11፤ የቤት ቁ. አዲስ
ሞባይል፡ +251-912-064882

**አምደኞች**
ተማም አባቡልጋ
ኤድመን ተስፋዬ
ኤፍሬም ስዩም
ግርማ ካሳ
ፍርድ ያውቃል ንጉሤ
ዩሐንስ ሞላ
ደረጀ መላኩ
አብርሃም ፈቃደ
ዳዊት ሰለሞን
ተስፋዬ አ.

ግራፊክ ዲዛይነር፡ ሀብ ዲዛይን
ሞባይል 0941 39 8446

**አታሚ:-**
ሶፍ ሚክ ማተሚያ ቤት ኃላ/የተ/የግል ማ.
ልደታ ክ/ከተማ
ወረዳ 04 የቤት ቁ. 064

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 02
ፌስቡክ :- facebook.com/addisgets

የቤት ቁ. አዲስ ስልክ:- +251-118898912
ኢ-ሜይል:- info@addisgets.com

ድረ-ገጽ፡ www.addisgets.com



ኤልያስ ገብሩ

# የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወደየት እየሄደ ነው?

ኢትዮጵያ ከዘመናት ጀምሮ እስከዛሬ የመጣችበት የአገዛዝ መንገድ ሥርዓት አልባና መዳረሻው በቅጡ የማይታወቅ ይመስላል፡፡ አንዱ ገዥ ሥርዓት በፈለገውና ባሻው መንገድ ይጓዝና መጨረሻው በውድቀት ይጠናቀቃል፡፡ ታሪካችን የሚያስረዳውም ይህንኑ ነው። ሥልጣንን የሙጥኝ የሚለው ፈሊጥ ለዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ፖለቲካዊ ባህላችን ሆኗል። በሰላማዊና በሚታወቅ መንገድ ሥልጣን ከአንዱ ገዥ ሀይል ወደሌላኛው ሀይል ሲሸጋገር በተግባር እስከዛሬም ድረስ አልተመለከትንም። ‹‹ሥልጣን የምናሸጋግርበትን መንገድ እስከ ዛሬ አልሠራነውም፤ የለንም›› ሲል ለ‹‹አዲስ ገጽ›› ሀሳቡን ይሰነዝራል የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አቶ የሺዋስ አሰፋ። በሀገራችን ሥልጣን በጉልበት እንደርስት ይዛዛል፣ መልቀቂው መንገድ ግን ተፈጥሯዊ ሞት ወይም ግድያ፣ አብዮት ወይም ትጥቅ ትግል ሲሆን ነው። ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ኢትዮጵያ በዘመኗ ዛሬም ድረስ ማየት አልቻለችም። የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብናይ፣ አጼ ኃይለስላሴ በጉልበት በደርግ ወረዱ፣ ደርግም ከ17 ዓመት የእርስ በእርስ ጦርነት በኋላ በጉልበት ለህወሃት/ኢህአዴግ ሥልጣኑን አስረከ። ይኸው ኢህአዴግም ላላፉት 25 ዓመታት ከስልጣን መንበሩ ላይ ብቻውን ቁጭ እንዳላ መኖርን ቀጥሏል። ይህም ‹‹ለምን?›› የሚል ጥያቄን ዘወትር እያብከነከነ ያጭራል።

## የጠንካራ ተቋማት ዕጦት

ሀገር በጠንካራ መሰረት ላይ መቆም እንድትችል ጤናማ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ተግባራዊ ሥራ ሊኖር የግድ ነው። በረዥም ዘመናት በሀገራችን ያለውን እውነታ ስንመለከት ግን ጤናማ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ተግባራዊ ሥራ ነበር ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ የሥልጣን ኮርቻ ላይ የሚቀመጡት ገዥ ሀይላት ቅድሚያ የሚሰጡትና የሰጡትም ለራሳቸው እንጂ እንመራዋለን ለሚሉት ህዝብ አልነበረም፣ አልሆነምም። ይህንን በአጼው ዘመነ መንግስት፣ በደርጉና አሁንም በኢህአዴግ አገዛዝ ውስጥ በግልጽ የሚታይ እውነታችን ሆኗል። እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ጠንካራ ሀገር ሆና ህዝቦቿም በታላቅነት ይኖሩ ዘንድ ነጻ፣ በራሳቸው የቆሙ ጠንካራ ተቋማት በተግባር ሊኖሩ በተገባ ነበር። ሆኖም ነባራዊ ሀቁ ከዚህ በተቃራኒው ነው። ተቋማት ለስምና ለይስሙላ መቋቋማቸው አልቀረም። ነገር ግን ‹ተቋሞቹ› ሥራቸውን የሚያከናውኑት በእውነተኛ ነጻነት ላይ ተመስርተው አይደለም። ሁሉም የሚንስቴር መ/ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋማት፣ እውቀት የሚገበይባቸው ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች፣ አዳዲስ እውቀቶች፣ ችግር ፈቺ-መፍትሄዎች፣ ሳይንስና ቴክሎኖሎጂዎች ...ይፈልቁባቸዋል ተብለው የሚታመኑባቸው የምርምር ተቋማት፣ የፖሊስና የደህንነት፣ ብሎም የመከላከያው ሀይሉ ድረስ በመርህ ደረጃ ተቋቋሙለት ለተባለው ርዕይ፣ ዓላማና ግብ ቆመዋል ብሎ ለመናገር አይቻልም፡፡ ነጻነት አግኝተው በመትጋት ተቋሞቻቸውን የምር ለመገንባት እየሰሩ ነው ብሎ መናገርም እጅግ አዳጋች ነው።

> ‹‹እኛ እና ኢትዮጵያን በሚመስሉ አገሮች ውስጥ ፖለቲካ የለም። አገዛዝ ባለበት ፖለቲካ የለም። ፖለቲካ ማለት ለሥልጣን የሚደረግ ትግል፣ ውድድርና ፉክክር ነው። በአምባገነንነት በሚገዙ አገራት ዘንድ ይሄ የለም

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ዕይታ፣ ተቋማቱ በቅድሚያ ህወሃት/ኢህአዴግ ለራሱ እንዲጠቅሙት አድርጎ ለቀመረው የፖለቲካ ‹ግብ› በተግባር መጠቀሚያ ይሆናሉ፣ በተግባርም የሚታየው ሀቅ ይሄንን ይመሰክራል፡፡ የትኛውም ተቋም ተቋቋምኩለት ላላው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማና ግብ በነጻነት አስቦና ለተግባራዊነቱ ተንቀሳቅሶ መስራት እስካልቻለ ድረስ ‹‹ከአስፈጻሚው አካል ተጽዕኖና ቁጥጥር ስር ነጻ የወጣ ተቋም›› ሊባል አይችልም። በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በነጻ አስተሳሰብ መርህ ላይ ቆመው፣ ለእውነተኛ ለውጥ ለመስራት ጥረት ያደረጉና የሞከሩ ሰዎች ወይም ስብስቦች ከአገዛዙ የዕቅድ መስመር ጋር በመላተማቸው የተነሳ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሥራ ገበታቸው ላይ ለመነሳት ተገድደዋል፣ ስደት ምርጫቸው የሆኑም በርካቶች ናቸው። በዚህ ምክንያትም የሞቱ ዜጎችም ይኖሩናል። ሀገሪቷም ከእነዚህ ዜጎቿ ማግኘት የነበረባትን የለውጥ ፍሬ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እንዳታገኝ ሆኗል።

ኢህአዴግ በአንድ በኩል ‹‹ተቋማትን እየገነባሁ ነው›› ብሎ ቢገልጽም በሌላ በኩል ተቋማት በነጻነት መቆም እንዳይችሉ አቅዶ ይሰራል። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው፣ ነጻ ተቋማት በተገነቡ ቁጥር ዜጎች በነጻ አስተሳሰብ ላይ ተመስርተው ሀይል በማግኘት በነጻነት ሥራቸውን ማከናወን ከጀመሩ ለኢህአዴግ የሥልጣን ህልውና የማታ ማታ አደገኛ መሆናቸው ስለሚታወቅና እሱም ይህንን በሂደት ጠንቅቆ በመረዳቱ ነው።

ፖለቲካውም ተሰርቶ መሬት ላይ መውረድ ስላልቻለ ነጻ ፕሬሱ ጭምሮ እንደተቋም ዛሬም ድረስ መገንባት አልቻለም። ነጻ ፕሬስ ከታወጀ ጀምሮ በርካታ ፕሬሶች ተጀምረው ነበር፡፡ ፕሬሶቹ ለተወሰነ ጊዜያቶች በውጣ ውረድ ውስጥ ታግለው ይሰሩና አንድ ወቅት ላይ ደግሞ መክሰም ግዴታቸው ወይም ዕጣ-ፈንታቸው ይሆናል፤ ይህም ዛሬም ድረስ የዘለቀ አንዱ እውነታችን ነው።

‹‹ቀዝቃዛው ጦርነት ካበቃና የምሥራቁ ጎራ ከተፈረካከሰ በኋላ፣ ቀደም ሲል አምባገነናዊ የነበሩት አገዛዞች ሳይቀሩ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን እንደሚቀበሉና የዴሞክራሲ ተቋማትን እንደሚገነቡ አውጀዋል። ይሁን እንጂ አንዳንድ በቅርጽ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር፣ እነዚህ ተቋማት ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዲሠሩ አይፈቅዱም፡፡ በሌላ አነጋገር ተቋማቱ በይዘታቸው ለሕዝብ ሳይሆን በሕዝብ ላይ የሚሠሩ፣ የአገዛዝ የመግዣ መሣሪያዎች ሲሆኑ ነው የሚታየው፡፡ በዚህ ተግባራቸው ምክንያትም እነዚህ ተቋማት በሕዝብ ዘንድ ተዓማኒነት የሌላቸው ስለሚሆኑ፣ ሥርዓት በተቀየረ ቁጥር እነሱም

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# የኢትዮ - ኤርትራ ዳግም ፍጥጫ

• የ‹‹ተመጣጣኝ ምላሹ›› መጨረሻ የት ይደርሳል?

**የኢትዮ - ኤርትራ ወቅታዊ ሁኔታን አስመልክታ አዲስ ገጽ ተከታዩን ዳሰሳ አቅርባለች**




በ1990 ዓ.ም. ግንቦት ወር መጀመሪያ - ደርግን ገርስሶ ለመጣል እጅ እና ጓንት የነበሩት ሕ.ወ.ኃ.ት. እና ሻዕብያ የ'እፍ እፍ' ፍቅራቸው ማብቃቱን አወጁ። በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. መንግሥት ድጋፍ እና ፈጣን እውቅና ሰጪነት በ1985 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ወደ ነፃ አገርነት የተሸጋገረችው ኤርትራ የራሷን መንግሥት ካቋቋመች በኋላ እንቅልፍ አልወሰዳትም፤ ራሷን በጦር መሣሪያ ስታጠናክር ከርማለች።

በኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው የሻዕብያ መንግሥት ከኢትዮጵያ የተገነጠለበትን የአምስተኛ ዓመት ሻማ ሳይለኩስ በፊት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከሕ.ወ.ኃ.ት ጋር መክሮ ‹‹በይደር አኑሮታል›› የሚባለውን የድንበር ማካለል ጥያቄ ማንሳት ጀመረ። በ1989 የክረምት ወቅት የጀመረው ይህ ጥያቄ በሁለቱ ‹‹ዝሆኖች›› ውይይት ቢደረግበትም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ግጭቶችን ሊያስቀር አልቻለም። በተለይም ሚያዚያ 28/1990 ዓ.ም. በሁለቱ ወገኖች መሀከል የከረረ ፍልሚያ ተካሄደ።

የቀድሞው የትግራይ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ገብሩ አሥራት 'ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ' በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የግጭቱ መንስዔ ያሉትን አብራርተዋል። ‹‹ሚያዚያ 28/1990 ዓ.ም. የተወሰኑ የሻዕብያ የጦር ኃይል አባላት በሰሜን ኢትዮጵያ ጫፍ በትግራይ ክልል ሥር ወደሚገኘው የባድመ ከተማ ሳይፈቀድላቸው ከነትጥቃቸው ለመግባት ሙከራ አደረጉ። በዚህ አጋጣሚ፤ በቦታው የነበሩ የኢትዮጵያ ሚሊሺያዎችና የፖሊስ አባላት ትጥቃቸውን አውርደው እንዲገቡ ሲጠይቋቸው ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ በሻዕብያዎች ላይ ግድያ ተፈፀመ።››

እንደ አቶ ገብሩ ገለፃ እነዚህ የተገደሉ ኃይሎች ለቅኝት የተላኩ ነበሩ። ‹‹ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነውም ሻዕብያዎች ለወራት በዚሁ አካባቢ ከፍተኛ የጦር ኃይል አከማችተው ልምምድ ሲያደርጉ መቆየታቸው ነው።›› ኤርትራ ግን የኢትዮጵያ የፀጥታ ኃይል ሉዓላዊ ግዛቷን ጥሶ ገብቶ ጥቃት እንዳደረሰባት በመግለፅ ደጋግማ ትከስ ነበር። ከዚህ ግጭት ሁለተኛ ቀን በኋላ በሁለቱ ሀገራት የመከላከያ፣ የፕሮፓጋንዳና የደኅንነት ጉዳይ ከፍተኛ ኃላፊዎች በአዲስ አበባ ተገናኝተው ስለ ድንበር ማካለሉ ጉዳይ እና ስለተነሳው ግጭት ቢወያዩም ወደ ሰላም ጫፍ መምጣት አልቻሉም።

በደርግ የተደራጁትን የምድር ጦር እና የአየር ኃይል ድርጅቶችን ያፈረሰው ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ከሱዳን እና ሌሎች አጎራባቾቹ ጋር ለተፈጠረበት ውጥረት ማርገቢያነት በሚል ሰበብ ጦሩን ካጠናከረው ሻዕብያ ጋር 'ደም ሊቃቡ' ከጫፍ ደረሱ፤ ደርግን ለማውረድ ቀለህ የሳቡ ጣቶቻቸውን እርስ በእርስ ሊተኳኮሱባቸው ግድ ሆነ። ኤርትራ ፀብ አጫሪ ባህሪ እያሳየች መሆኗንና ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑን በድንበር አካባቢ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ጥቆማ እየሰጡ እንኳን ከኢትዮጵያ በኩል የተወሰደ እርምጃ እንዳልነበር የተለያዩ ጸሐፍት አትተዋል። ‹‹እስከ ግንቦት 1990 ዓ.ም. ባሉት ወራት ኢትዮጵያ ውስጥ ለጦርነት መዘጋጀት የሚባል ነገር አልነበርም። በድንበሩ አካባቢ የነበረው የትግራይ ሕዝብ ጦርነቱ አይቀሬ ነው አስፈላጊው ዝግጅት ይደርግ እያለ ቢወተውትም ሰሚ አላገኘም።›› ብለዋል አቶ ገብሩ በመጸሐፋቸው። ለዚህ ደግሞ በምክንያት የተጠቀሰው ሰው ከወቅቱ የአገሪቱ መሪ አቶ መለስ ጀምሮ ‹‹ኤርትራ ትወረናለች›› የሚል ግምት አለመያዛቸው እንደሆነ ተነግሯል። በዚህም የተነሳም ኢትዮጵያ ጥቃት ቢሰነዘር መመከት የሚያስችል ዝግጅት አልነበራትም።

## ግንቦት 4/1990

ግንቦት 4/ 1990 ዓ.ም. ለጦርነቱ ሲተጋ እንደነበር የተገለፀው የሻዕብያ ጦር ባድመንና አካባቢዋን ወረረ። ‹‹በወቅቱ በቦታው ከነበሩት የክልሉ ፈጥኖ ደራሾችና ሚሊሺያዎች ጋራ ገጥመው በርካታዎቹን ገደለው፣ አቁስለውና ማርከው ነበር። የሻዕብያ ሠራዊት ወደ አካባቢው የገባው በታንክና በከባድ መሣርያ ታግዞ ስለነበር በአካባቢው የነበረው ኃይል ሊቋቋመው አልቻለም። ከሞትና ከምርኮ የተረፉትን ይዞ ወደኋላ ከማፈግፈግ ሌላ አማራጭ አልነበረውም።››

የተደራጀ እንቅስቃሴ ያደረገው ሻዕብያ ባድመንና ከፊል ሽራሮን ያዘ። አከታትሎም ‹‹ኢትዮጵያ ወስዳብኛለች›› የሚላቸውን ቦታዎች ሁሉ ‹‹አስመልሳለሁ›› በማለት በተለያዩ ግንባሮች

ሰፊ ወታደራዊ ዘመቻ በማካሄድ በሰኔ ወር 1990 ዓ.ም. ዛላ አንበሳን፣ አይጋን፣ ጉሎ መኸዳን በአጠቃላይ አሊቴናንና በጠቅላላው ኢሮብን፣ በአፋር አቅጣጫ ቡሬን የመሳሰሉ መሬቶችን በወረራ ያዘ።›› ብለዋል ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ 'የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ግጭት መንስዔ እና መፍትሄ' በሚለው መጻሕፋቸው ላይ የቀጣይ ቀናቱን የሻዕብያ እንቅስቃሴ ሲያትቱ።

የአሜሪካና ሩዋንዳ መንግሥታት በጥምረት ግጭቱ ረገብ እንዲል የሰላም ዕቅድ አቀረቡ። ኢትዮጵያ ስትቀበለው፤ ኤርትራ እምቢኝ አለች። ጦርነቱ ተጠናከረ። በኤርትራ መንግሥት ወረራ እንደተፈፀመበት ውሳኔ ላይ የደረሰው ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. በሥራ አስፈፃሚው በኩል ‹‹ወረራውን ለመቀልበስ አስፈላጊውን እርምጃ ወስዳለሁ›› አለ።



በሰኔ 1990 ዓ.ም በመቀሌ የሚገኘው አይዳር የተባለውን ትምህርት ቤት ላይ የኤርትራ ጦር ቦምብ አዘነበበት። በርካታ ህፃናት ተማሪዎች ሕይወታቸው አለፈ። የአካል ጉዳትም ደረሰባቸው። ይሄን ያየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆጣ። አስመራ ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ንብረታቸው እየተዘረፈ እንደተባረሩ ሲሰማ ሕዝቡ ሆድ ባሰው። በአገሩ ላይ የሚገኙ 'የጊዜ ሰው' የነበሩ ኤርትራዊያን ሁኔታ በኤርትራ ከሚገኙ ወገኖቹ ጋር አነፃፅሮ ሊቀበለው የማይችለው ቅሬታ ተሰማው።

ከ1990 ክረምት እስከ ጥር 1991 ዓ.ም. ድረስ ጦርነቱ በመጠኑ ተቀዛቅዞ ታየ። ሁለቱም አገሮች ግን አልተኙም፤ በሚሊዮኖች ዶላር አፍሰው ራሳቸውን በጦር መሣሪያ አደራጁ።

ዳር ድንበሩ ተደፍሮ፣ ሉዓላዊነቱ ተጥሶ፣ ወገኖቹ ተጠቅተው ዝም ማለት የማያስችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጣዊ ችግሮቹን አፍኖ ከዳር ዳር ተነቃነቀ። ወደ ጦር ሜዳውም ከተተ። በከባድ ምሽጎች የታጠረውን ባድመን ጨምሮ የተወረሩበትን መሬቶቹን አስመለሰ። ጦሩ ወደ ኤርትራ ተንደርድሮም ሳዋ የተባለውን የውትድርና ማሠልጠኛ ተቋም አየር ጥቃት አደረሰበት። ሽንፈት የተጎነጨችው ኤርትራም የግዷን የሰላም ድርድሮችን ለመቀበል ተስማማች።

በወቅቱ በኢትዮጵያ በኩል የኤርትራ ወራሪነት ስለታመነበት የጦርነቱ ስትራቴጂና ዓላማ ሻዕብያ በኢትዮጵያ የደኅንነት ስጋት እንዳይሆን አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት ዘለቄታዊ መፍትሔ ማበጀት ነበር። የኢትዮጵያ የከፍተኛው እርከን የሥልጣን ባለቤት የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ ግን በዚህ ሳይስማሙ ቀሩ። የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትና በኋላም አንድነት ፓርቲን የተቀላቀሉት አቶ ስዬ አብርሃ 'ነፃነት እና ዳኝነት በኢትዮጵያ' በሚለው መጻሕፋቸው ላይ የአቶ መለስን የውሳኔ ተንሸራታችነት በጉልህ ጠቅሰውታል።

‹‹አቶ መለስ ማወላወል የጀመረው ወረራው ከተፈፀመብን ከሁለተኛው ወር ጀምሮ ነው። ጦርነቱ የማይቀርልን መሆኑ ግልፅ እየሆነ ሲሄድ የምናደርገው ዝግጅት ጥልቀትና ስፋት ግልፅ ለመሆን ያስችለን ዘንድ የጦርነቱ ዓላማ ምን ይሁን በሚለው ላይ ግልፅ መግባባት መኖሩ እጅግ አስፈላጊ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ የሀሳብ ልውውጥ ስንጀምር 'ዓላማው የሻዕብያን ሠራዊት መደምሰስ መሆን ይኖርበታል።' የሚል ሀሳብ ጠንክሮ ሲመጣ አቶ መለስ ይህንን ሃሳብ አልተቀበለውም።›› እንደ አቶ ስዬ ትንታኔ ሠራዊቱን መደምሰስ በወረራ የተያዘውን መሬት እርግጠኛ በሆነ መልኩ ለማስመለስ ይረዳ ነበር። እስከዛሬ በቀጠናው ሽብር ቆስቋሽ መሆኗን

## በዚህ ሰዓት <<የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጣዊ ችግሮቹን አፍኖ ሆ ብሎ ከዳር ዳር ይነሳል ወይ?>> የሚል ጥያቄ ጭሮ <<አዎ!>> የሚል ምላሽ ማግኘት ፍፁም አዳጋች ይሆናል

ሠርክ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚናገርላት ኤርትራ የስጋት መነሻ መሆኗ ያበቃና በሁለቱ መንግሥታት መሀከል በእንጥልጥል የነበሩት ችግሮች ተፈትተው ጠንካራ መደላደል ይፈጠር ነበር። ይህም ማለት ሰሞናዊ የሁለት አገራት ግጭት እና በ'ወጣ ገባ' የሚከሰተው የተኩስ ልውውጥ ከርዕስነት ደረጃ ዝቅ ይል ነበር።

### ዳግም ጦርነት?

የሰሜኑ ጦርነት ዳግም ሊያገረሽ ዳር ዳር እያለ ነው። ሁለቱም አገራት ‹‹ቀድመን ቃታ አልሳብንም›› ሲሉ ትንኮሳ እንደተፈጸመባቸው ቢከሱም በፆረና የተኩስ ልውውጥ ማድረጋቸውን ግን አልካዱም። በ1990 በተጀመረው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በኤርትራ ተይዛ በነበረችው በፆረና ግንባር ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ፣ እሁድ ከሰዓትና ሰኞ ዕለት ጠዋት ከፍተኛ የከባድ መሣሪያ ተኩስ መስማታቸውን ከኢትዮጵያ ወገን ያሉ ዜጎች ለውጪ መገናኛ ብዙሐን ከገለፁ በኋላ የኤርትራ መንግሥት shabait.com በተባለው ይፋዊ ድረ-ገፁ በማስታወቂያ ሚኒስቴሩ አማካኝነት እውነታውን የሚያጠናክር ባለ ስድስት መስመር መግለጫ አወጣ። ‹‹የሕ.ወ.ኃ.ት. መንግሥት በፆረና ማዕከላዊ ግንባር ጥቃት ከፍቶብናል። የጥቃቱ ዓላማና የሚያስከትለው ውጤት ግልፅ አይደለም።(The purpose & ramification of these attack are not clear) በቀጣይም የኤርትራ መንግሥት በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መግለጫዎችን ያወጣል።››

የኢትዮጵያ መንግሥትም ባለፈው ሰኞ የተፈጠረውን ግጭት አስመልክቶ ባወጣው የመጀመሪያ መግለጫ ቅድያ ትንኮሳ የፈፀመችው ኤርትራ መሆኗን የሚገልፅ ክስ አቅርቧል። እሁድ ሰኔ 5 ጠዋት በፆረና ግንባር ጥቃት ለመፈፀም ቀድሞ የተንቀሳቀሰው የኤርትራ መንግሥት ጦር መሆኑን የገለፀው መግለጫው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የአፀፋ እርምጃ መውሰዱን አትቷል። ‹‹ለጥቃት የተንቀሳቀሰው የኤርትራ ኃይል ሙሉ ለሙሉ ተመትቷል›› ብሏል።

የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ ሚኒስጽር የሆኑት አቶ ጌታቸው ረዳ በጦርነቱ በግጭቱ ስለደረሰው አደጋ ከፈረንሳይ የዜና ወኪል ኤ.ኤፍ.ፒ. ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹በሁለቱ ወገኖች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሷል። የበለጠ ጉዳት የደረሰው ግን በኤርትራ በኩል ነው።›› ሲሉ ተናግረዋል። ‹‹ተመጣጣኝ እርምጃ ወስደናልም›› ብለዋል - ለዜና ወኪሉ። ሚኒስትሩ ባለፈው ማክሰኞ ረፋድ በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ ላይ ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ከብዙ ወገናት ‹‹የተመጣጣኝ እርምጃው መጨረሻ የለየለት ዳግመኛ ጦርነት ወይስ ምን ያስከትላል?›› የሚሉ ጥያቄዎችን እያስነሳ ይገኛል።

### በቀጣይ ምን ይሆናል?

አቶ ጌታቸው በማክሰኞው መግለጫቸው ላይ የኢትዮጵያ ጦር ቀጣይ ውሳኔዎች በኤርትራ መንግሥት ሁኔታዎች ላይ እንደሚወሰን ተናግረዋል። ይህም 18 ዓመት ሻክሮ የቆየው እና ውጥረት ነግሶበት የቆየው ድንበር ዳግም ጦርነት ሊቀሰቀስበት እንደሚችል ፍንጭ የሰጠ ሆኗል። በተለይ ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ስጋት እየሆኑ የመጡ የትግል ቡድኖች በኤርትራ መመሸጋቸው ያሳሳበው እንደሆነ የወሰደው እርምጃ ጠቋሚ ሆኗል። ይህንንም ጠቋሚ አስተያየት ከሚኒስትሩ ተደምጧል። ‹‹የኤርትራ መንግሥት በሠራዊቱ አማካኝነት ሊያስፈጽመው የማይችለውን የጣፋት ዓላማ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች፣ የተለያዩ ተላላኪዎችን በመቅጠርና አሰልጥኖ በመላክ፣ ሽፍቶችን በማሰማራት ሁከት የመፍጠር ዓላማ አለው››

‹‹መሬታችን ድረስ ዘልቆ ጥቃት ፈጽሞብናል።›› ያሉት በተባበሩት መንግሥታት የኤርትራ አምባሳደር የሆኑት አቶ ግርማ አስመሮም የኢትዮጵያ መንግሥት ጥቃት የሰነዘረብን ከኦሮሞ እና ከቅማንት ሕዝብ ያለበትን ጫና እና በአገሪቱ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ እግሮች ለመቀልበስ (ትኩረት ለማስቀየስ) የወሰደው እርምጃ ነው።› ሲሉ ለቪ.ኦ.ኤ. የአማርኛው ክፍል ተናግረዋል።

ከሁለቱ መንግሥታት ውጪ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉዳዩ ላይ የሚያንፀባርቃቸው ውሳኔዎች በቀጣይ የሚታዩ ይሆናል። የኢትዮ ሚዲያ ፎረሙ ኤዲተር ዳዊት ከበደ ወይሶ ዳግም ጦርነት ቢቀሰቅስም ከ18 ዓመት በፊት እንደነበረው ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆ ብሎ ከዳር ዳር ይነሳል ወይ?›› የሚል ጥያቄ ‹‹የሰሜኑ ጦርነት እንደገና ሊጀመር ነው!›› በሚለው ጽሑፉ ላይ አቅርቧል። ይህ ጥያቄ የዳዊት ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ነው። በዚህ ሰዓት ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጣዊ ችግሮቹን አፍኖ ሆ ብሎ ከዳር ዳር ይነሳል ወይ?›› የሚል ጥያቄ ጭሮ ‹‹አዎ!›› የሚል ምላሽ ማግኘት ፍፁም አዳጋች ይሆናል።




እንዳለ አሰፋ

endale.asefa@addisgets.com


# ቁም - ነገር አልባነት ተጽዕኖ ፈጣሪ ሲሆን

የሰው ልጅ እንደማኅበረሰብ ሲኖር የማኅበረሰቡን አካላት በጠቅላላው በሁለት ክፍሎ ሊገነዘባቸው ይችላል - ቁም-ነገረኛ እና ቁም-ነገር አልባ በሚል:: ቁም-ነገረኛ የሚባሉት የማኅበረሰብ አባላት በተለያዩ ኃይማኖቶችና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች ሲመዘኑ እውነተኛነታቸው፣ ሰው አክባሪና ታዛኸኘነታቸው፣ የሰው ንብረት ከመመኘትና ከመውሰድ ይልቅ ሌባና ሙሰኛን የመከላከል ፍላጎትና ተግባራቸው፣ ስራና ሀገር ወዳድነታቸው ወዘተርፈ ከግምት ውስጥ ገብቶ ያስከብራቸዋል:: በተቃራኒ ቁም-ነገር አልባ የሚባሉቱ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ማኅበረሰቡ ጥሩ የሚላቸውን መርሆችና እሴቶች በተቃራኒ ተግባራት የሚያከናውኑ ሲሆን በማኅበረሰቡ ዘንድም ተከባሪነታቸው እምብዛም የሆኑ ናቸው::

ቁም-ነገር አልባነት እና ተከታዮቹ በማኅበረሰብ ላይ የመሰልጠንና ገዥ የመሆናቸው እድል ብዙ ጊዜ አነስተኛ ቢሆንም ቁጥጥር እስካልተደረገባቸው ድረስ በታሪክ እንደምናውቀው የሰዶምና ገሞራ ዘመን አይነት አጥፊ ባህሪያቸው የበላይ ሆኖ ቁም-ነገረኛ የሚባለውን ማኅበረሰብም ጭምር መከራና ጥፋት ውስጥ ሲከቱ ይስተዋላል::

ቁም-ነገር አልባነት በራሱም እርስ በርሳቸው ተመጋጋቢ የሆኑ ፈርጆች አሉት:: በብዛት የሚስተዋሉትን ፖለቲካዊ/አስተዳደራዊ እና ማኅበራዊ ፈርጆች ብንመለከት እንኳን በማኅበረሰባዊ ኑሮ ውስጥ የተፈጠረና የዳበረ ቁም-ነገር አልባነት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ውስጥም ዘልቆ ይገባና ይህ ነው የማይባል ከባድ ዝቅጠትን በማኅበረሰቡ ብሎም በሀገር ላይ ሊፈጥር ይችላል::

ይህ የቁም-ነገር አልባነት በቁም-ነገር ላይ ቁጥጥር የማድረግ ጉዳይ በዓለማችን ላይ በተደጋጋሚ የተከሰተ ነገር እንደሆነና አሁንም ዓለማችንን በአጠቃላይ ሀገራችንንም በተለይ የሚያምሱ አስቸጋሪ ሰዎችን ያፈራ ስለመሆኑ አይካድም:: ቁም-ነገር አልባነት በቁም-ነገር ላይ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ:: ዝርዝር ምክንያታቸው ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም የሰው ልጅ ልቅነት ሲያበዛና ቁም-ነገር አልባ ሰዎች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በብዛት ሲፈጠሩ እና ወይም በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ብዛት ያለው ተከታይ ሲያገኙ ቁም-ነገር አልባነት ማኅበረሰብን የመቆጣጠር ነገሩ ይፈጠራል:: የሰዎች ልቅነትን ማብዛትና መልካም ተብለው የሚታወቁ የማኅበረሰቡን ዕሴቶች መሸርሸር እንደመሰልጠን/እንደትክክል መቆጠር ሲጀምር የቁም-ነገር አልባነት ቁጥጥር/የበላይነት መኖሩ ይታወቃል:: ተሰምተው የማይታወቁ፣ ማኅበረሰቡ እንደ በጎ የማይመለከታቸው አዳዲስ ባህሎችም ተቀባይነት እንዲያገኙ ግፊት ይደረጋል::

አሁን ባለንበት ወቅት፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ በየሀገራቱ የተለያዩ የቁም-ነገር አልባነት መዘዞች እየተንፀባረቁ ይገኛል:: ከውጭ ሃገር ያለውን ማሳያ በተለይ በአሜሪካ ያለውን አንዳንድ ጉዳይ በማንሳት ልጀምርና ወደሃገራችን ጉዳይ እመለሳለሁ:: ከትራንስ ጄንደር ጉዳይ ልጀምር:: በዚህ ወቅት ትኩስ የመነጋገሪያ ዜና ሆኖ ያለው የትራንስ ጄንደር የሽንት ቤት ጥያቄ ለአብዛኛው የሃገራችን ሰው ግርም የሚል የልቅነት ውጤት ይመስለኛል:: ትራንስ ጄንደር በአማርኛ ትክክለኛ ትርጉሙን ለቋንቋው ምሁራን ትቼ እንደወረደ ልጠቀመው። ዝርዝር ትርጉሙ አንድ ወንድ ሆኖ የተወለደ ሰው ሆርሞን ወስዶም ይሁን በሌላ ምክንያት ‹‹ሴትነት ይሰማኛል!›› ወይንም ‹‹ሴት ነኝ!›› ብሎ ሲያውጅ እና አንድ ሴት ሆና በሙሉ የሴትነት የአካል ብቃት የተወለደች ሰው በተገለጸው ምክንያት ‹‹ወንድ ነኝ!›› ብላ ራሷን መሳል/ማወጅ ነው::

‹‹ይህም አለ እንዴ?›› ለሚል አንባቢ ሌላ የሚገርም ነገር ስላለው በ'የሽንት ቤት' ጥያቄውን ትንሽ መደመሙ አይቀርም:: እነዚህ በቁጥር ወደ ዜሮ የሚጠጉ ትራንስ ጄንደር ሰዎች ሰሞኑን በተለያየ የሃገሪቱ ክልሎች /states/ በሚያነሱት የሽንት ቤት አጠቃቀም ጥያቄ ብዙ የዜና ሽፋን እያገኙ ነው:: እነርሱ የሚሉት ‹‹በወንድ የአካል ብቃት ብኖርም ሴትነት ስለሚሰማኝ የሴት ሽንት ቤት ገብቼ ልጠቀም›› እንዲሁም በሴት የአካል ብቃት ሆነው ‹‹ወንድነት ተሰማን›› የሚሉት ‹‹የወንዶች ሽንት ቤት ገብቼ ልጠቀም›› ነው:: ታዲያ እዚያው አገራቸውም ቢሆን ጥያቄያቸው ያስገረመውና 'ቀበጣችሁ' ያላቸው ባይጠፉም አበጃችሁ የሚላቸው ሰው በዝቶ አገሩን እያመሱት ይገኛሉ:: ወደፍርድ ቤትም አምርተው በክስ የረቱም አሉ - ሰሞኑን:: ቀስ ብሎ ሁሉም ቦታ ተቀባይነት ማግኘታቸው የማይቀር ይመስላል:: ያኔ ደግሞ በየሽንት ቤቱ የሚደረገውን የመደፋፈር ወንጀል ለመከታተል እንበቃለን::

ከዚሁ ከአሜሪካ ሳንወጣ ሌላ ትልቅ ጉዳይ ላንሳ፤ ስለዶናልደ ትራምፕ:: ይህ ሰው በአሁን ሰዓት አሜሪካንን የሚያክል ግዙፍ ሀገር አስተዳድራለሁ ብሎ ዝብርቅርቁ የወጣ መስመር ይዞ በሚገርም ሁኔታ አጠገቡ የነበሩ ወደ ሃያ የሚጠጉ ተፎካካሪዎችን ተስፋ አስቆርጦ ወደ ዋይት ሃውስ እየገሰገሰ ያለ ሪፐብሊካንን ወክሎ ለፕሬዚዳንትነት ዕጩ ተወዳዳሪ ለመሆን የቻለ ነው:: ሰውየው በብዙ ሰዎች እይታ ስሜቱን ብቻ የሚያወራ፣ ያውም ስሜቱ የማይታወቅና በምንም መስፈርት ለመሪነት የማይበቃ ግለሰብ ነው:: ነገር ግን፣ በኔ እይታ የቁም-ነገር አልባነት ውጤት ብዙ ተከታዮችን አስገኝቶለታልና የሚገርም ጉዞ እያደረገ ይገኛል:: የሚሆነውን ወደፊት እናያለን::

ወደ ዋናውና የሃገራችን ጉዳይ ልመለስ:: በአሁን ሰዓት በመግቢያዬ ላይ የገለጽኳቸውን የቁም-ነገረኝነት መገለጫ እሴቶችና ባህሪያት ተቃራኒ ማድረግ እንደመሰልጠን የሚቆጥሩ በርካታ ወገኖች እያፈራን እንደሆነ አብዛኛው ሰው ይስማማል ብዬ እገምታለሁ:: የዚህ ውጤት ደግሞ በየመስሪያ ቤቱ ገብቶ እጅግ የበዛ ሙሰኝነትን ጨምሮ በርካታ የሥነ-ምግባር ግድፈቶችን እንደ በጎና ታላቅነት መገለጫ የሚቆጥር ማኅበረሰብ ፈጥሯል:: ይህንን የተፈጠረ እኩይ ተግባር መኮነንና ማጋለጥም እንደ አደጋ መታየት ከጀመረ ሰንበተ:: ይህ ቁም-ነገር አልባነት ገደብ አግኝቶ ልቅነቱም ቁጥጥር እካልተበጀለት ድረስ ያሉንን እሴቶች ሁሉ ንደንና አጥፍተን መመለሰ የማይችል የመከራ ዘመን ውስጥ እንዳንገባ ስለምሰጋ ከሁሉም አቅጣጫ መፍትሄ ያሻል እላለሁ::

በተለይ 'መሪ' ነን ብለው በየመስሪያ ቤቱ ያሉ ሰዎች እዚህ ዝቅጠት ውስጥ መገኘት አስከፊነቱን ያጎላዋል፤ ገደብ ለማበጀት የሚደረገውንም ጥረት ክፉኛ ይጎዳዋል:: እናም መልካም መሪ አግኝተን በቁም-ነገር እሴቶቻችን ታንጸን ለመኖር እስክንችል ድረስ እያንዳንዱ የማኅበረሰብ ክፍል ከቤተሰቡ ጀምሮ ቁም-ነገር አልባነትን ለመታገል መንቀሳቀስ ያለበት ይመስለኛል፤ ከአምላክ ብቻ መፍትሄ ከመፈለግ የድርሻችንንም መወጣት ተገቢ ነውና::

> የዚህ ውጤት ደግሞ በየመስሪያ ቤቱ ገብቶ እጅግ የበዛ ሙሰኝነትን ጨምሮ በርካታ የሥነ - ምግባር ግድፈቶችን እንደ በጎና ታላቅነት መገለጫ የሚቆጥር ማኅበረሰብ ፈጥሯል : : ይህንን የተፈጠረ እኩይ ተግባር መኮነንና ማጋለጥም እንደ አደጋ መታየት ከጀመረ ሰንበተ : : ይህ ቁም - ነገር አልባነት ገደብ አግኝቶ ልቅነቱም ቁጥጥር እካልተበጀለት ድረስ ያሉንን እሴቶች ሁሉ ንደንና አጥፍተን መመለሰ የማይችል የመከራ ዘመን ውስጥ እንዳንገባ ስለምሰጋ ከሁሉም አቅጣጫ መፍትሄ ያሻል እላለሁ



ዳዊት ሰለሞን

# የወቅቱ ቁልፍ ጥያቄ

## ‹‹አለም አቀፉ ፍርድ ቤት ወይም ኤርትራ››

ሰብዓዊ መብቶች መከበር ይኖርባቸዋል፣ መንግስታት ደግሞ በሁሉም መስፈርቶች ሰብዓዊ መብቶች መከበራቸውንና እንዳይጣሱ ዋስትና መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መንግስታት በየአገሮቻቸውም መብታቸው መጣሱን ለሚገልጹ ዜጎቻቸው መፍትሄ የሚያበጁባቸውን ተቋማት መገንባት ይኖርባቸዋል፤ ‹‹ሰብዓዊ መብቴ ተጥሷል›› የሚሉ ግለሰቦች ጭምር በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ መድረኮች ፍትህ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ነገር ግን፣ በሚበዙት የአለማችን አገራት በመንግስታት ደረጃ የሚፈጸሙ ስልታዊ የመብት ገፈፋዎች በአገራቱ ውስጥ በሚገኙ የፍትህ ተቋማት ተጣርተው ተጎጂዎች የሚፈለገውን ፍትህ ያገኛሉ በማለት ለማሰብ እንኳን ያስቸግራል፡፡

በአብዛኛው በመንግስታት የሚፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት፣ስልጣንን ጠቅልሎ ለመያዝና ድንበር ተሻጋሪ ጦርነቶችን በማከናወንና የመሳሰሉትን በመፈጸም ነው፡፡ስልታዊ የነበረው በዘመነ አውግስቶ ፒኖቼ የተፈጸመው በቺሊ የዘር ማጽዳት ጭፍጨፋ፣ በኤዲ አሚን የአገዛዝ ዘመን በኡጋንዳ፣ በደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ ዘመንና በኢትዮጵያ በዘመነ ደርግ የተፈጸሙ ወንጀሎች በመንግስታት የተከናወኑ ነበሩ፡፡

በመንግስታት የሚፈጸሙ የጦር ወንጀሎች፣ የዘር ማጥፋትና ኢ-ሰብዓዊ ወንጀሎች መንግስታቱ ባሉባቸው አገራት ወንጀለኞቹ ለፍርድ ቀርበው ፍትህ እንዲሰፍን ማድረግ ባለመቻሉም አለም አቀፉን የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ወለደ፡፡ ሮም ላይ እ.አ.አ በ1990 ዓ.ም በተደረገ ኮንፈረንስ ውልደቱ የተበሰረለት ፍርድ ቤቱ መሬት ላይ ውሎ በተግባር መንቀሳቀስ የጀመረው ከአራት ዓመታት ቆይታ በኂላ ነበር፡፡ በወቅቱም ከአለማችን አገራት መካከል 121ቱ የሮምን የስምምነት ሰነድ በመፈረም ፍርድ ቤቱን ሲያጸድቁ ከፈራሚዎቹ መካከል 33ቱ ያህሉ አፍሪካዊያን መሆናቸው ብዙ ተስፋ አሳድሮ ነበር፡፡ዋና መቀመጫውን በሆላንድ ሄግ ያደረገው ፍርድ ቤቱ ከመነሻው በአቃቤ ህጎቹ ከያዛቸው ክሶች መካከል ከአስሩ ዘጠኙ መገኛቸው አፍሪካ መሆኑም የአፍሪካ መሪዎችን ማስቆጣት መጀመሩ አልቀረም፡፡

ኢትዮጵያ የሮሙን ስምምነት አልፈረመችም፡፡ ለአፍሪካ ህብረትና ለተባበሩት መንግስታት ምስረታ ቁልፍ ሚና የተጫወተችውና በተለይም በኢህአዴግ ዘመን በተግባር ለመዋላቸው ብዙ ምርመራ የሚያስፈልግ ቢሆንም አለም አቀፍ ስምምነቶችን በመፈረም አቻ የማይገኝላት ኢትዮጵያ የሮሙን ስምምነት በፊርማዋ አለማጽደቋ ብዙዎችን ማስገረሙ አልቀረም፡፡ እስካሁን ድረስም ላለፉት 25 ዓመታት አለም አቀፍ ስምምነቶችን፣ ህጎችንና አዋጆችን በመቀበል የማይታማው ኢህአዴግ ሮም ላይ በምን ምክንያት የፊርማ ወኔው እንደከዳው ለማንም ግልጽ አይደለም፡፡

> **ከሶስት ዓመት በፊት የአፍሪካ ህብረት የዙር መሪ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ፍርድ ቤቱን ‹‹ዘረኛ›› በማለት መሰየማቸውም ፍርድ ቤቱ በአፍሪካ መሪዎች የተንሸዋረረ ዕይታ ውስጥ ለመውደቁ ማሳያ ነበር**

አለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በይፋ ከአፍሪካ መንግስታት ጋር መጋጨትና የተለያዩ ንቅናቄዎች የተደረጉበት በስልጣን ላይ የሚገኙትን የሱዳኑን ፕሬዚዳንት ኦማር አልበሽርን ከዳርፉር ግጭት ጋር በተያያዘ በጦር ወንጀለኝነትና በዘር ማጥፋት ወንጀሎች መክሰሱን ማስታወቁን ተከትሎ ነው፡፡

አልበሽር ከፍርድ ቤቱ ለደረሳቸው ክስ ጄኔቭ ላይ በመገኘት ራሳቸውን ለመከላከል ባለመፍቀዳቸው ፍርድ ቤቱ የእስር ማዘዣ ለማውጣት ተገድዷል፡፡ የእስር ማዘዣው የወጣባቸው አልበሽር በትጥቅ ትግሉ ዘመን እገዛ ወዳረጉላቸው የኢትዮጵያ መሪዎች በዛ ያሉ ጉዞዎችን በማድረግ በአፍሪካ ህብረት ስብሰባዎችና በተለያዩ የበዓላት ዝግጅቶች ላይ ታድመዋል፡፡

የአልበሽር ወደ ኢትዮጵያ መመላለስ አዲስ አበባ የሮሙን ስምምነት ባለመፈረሟ አልበሽርን አሳልፋ የመስጠት አስገዳጅ ሁኔታ የለባትም የሚል ማጽናኛ ቢበጅለትም አልበሽር ለአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ከሮሙ ስምምነት ፈራሚዎች አንዷ ወደሆነችው ደቡብ አፍሪካ በማምራት አለም

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# ‹‹አዋጅ የሚያወጡት ማጥቃት የሚፈልጉት ሰው ሲኖር ነው››

## አጥናፍ ብርሃኔ [ጦማሪ]

- ራሴን የማስበው እንደታፈንኩ አድርጌ ነው
- አንቀፅ 14 በራሱ የሕዝብን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ነው

አቤል ዓለማየሁ ስለ ጡመራ፣ የኮምፕዩተር ወንጀል አዋጅና አክቲቪዝም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ ከሆነው [የ'ዞን ዘጠኙ'] አጥናፍ ብርሃኔ ጋር ተወያይቷል።



**ጡመራ (blogging) ምንድን ነው?**

ባሕላዊ ሚዲያ የሚባሉት ጋዜጣ እና መጽሔት ላይ የመሥራት ዕድሉን ያላገኙ ወይም መሥራት ያልፈለጉ ነገር ግን ሀሳባቸውን መግለፅ የሚፈልጉ ሰዎች የሚጽፉበት የኢንተርኔት መድረክ ነው። ያለ ማንም ከልካይ የመሰለህን የምትጽፍበት ስፍራ ቢሆንም ራስህን ሳንሱር ማድረግህ ግን አይቀርም።

**ራስን ሳንሱር ማድረግ ማለት?**

ኢትዮጵያ ውስጥ ራስህን ሳንሱር እንድታደርግ ትገደዳለህ። ሕገ መንግሥቱ ሀሳብን በነፃነት የመናገር መብት የሰጠ ቢሆንም በርካታ አሳሪ አዋጆች ስላሉ በሙሉ ነፃነት ትፅፋለህ ማለት አይቻልም። የጻፍከው ጽሑፍ አመፅ አስነሳም አላስነሳም ደስ ካላልካቸው ልትታሰር ወይም ልትከሰስ ትችላለህ። ከተከሰስክ ደግሞ በኢትዮጵያ ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ነፃ የመውጣት ዕድልህ ጠባብ ስለሆነ ራስህን ሳንሱር ማድረግ የግድ ነው።

**አንድ ጦማሪ እንደ ጋዜጠኛ ኤዲቶሪያል አቋም የማንጸባረቅ፣ ሚዛናዊነት እና አለማዳላትን ታሳቢ ማድረግ፣ በተወሰኑ ቃላት ሀሳብን መግለፅ (ቁጥብነት) አለበት? [በእኛ አገር ተተገበረም አልተተገበረም ጡመራ የራሱ መርህ አለው ብዬ ነው።]**

እንዳልከው የራሱ የሆነ መርህ ይኖረዋል። ጦማሪውም የጻፈውን ነገር ትክክል ነው/አይደለም ብሎ የሚመዝንበት የራሱ መንገድ አለው። እኛ በቡድን ስንንቀሳቀስ [ዞን ዘጠኝን ማለቱ ነው] መደበኛም ባይሆን እንደ ባሕላዊ ሚዲያው ጽሑፎቻችን ከመውጣታቸው በፊት እየተነጋገርን በአስተያየት እናጠናክረው ነበር።

**ሚዛናዊነት እና አለማዳላት ታሳቢ ይደረጋሉ የሚለውን መልስልኝና እንቀጥል።**

ጡመራ ወደ ግላዊነት ያዘነብላል። ማንም ሰው የግል አስተያየቱን ሊያስቀምጥበት ይችላል። ጥናት ሠርቶም ሆነ የግል አስተያየት ላይ ተወስኖ መጻፍ በጦማሪው የሚወሰን

ይሆናል:: ሚዛናዊነት እና አለማዳላትን ታሳቢ ማድረግም እንዲሁ የጸሐፊው ውሳኔ ነው:: ብሎግን እንደ ኦንላይን የውሎ ማስታወሻ (Online Diary) መውሰድ ይቻላል::

**የዞን ዘጠኝ ኢ- መደበኛ ጸሐፊያን ጽሑፎችን የምታሠፍሩት የተጻፉ መርሆዎችን እና ስትራቴጂዎችን ነድፋችሁ ነበር?**

የተጻፈ ነገር አልነበረንም:: ቡድናችን ሁሌም እንደምንለው ኢ-መደበኛ የጦማሪያን እና አራማጆች ስብስብ ነው:: መደበኛ ሚዲያ ብትሆን ግን ያልካቸው ነገሮች ሁሉ መምጣታቸው አይቀርም::

**ጡመራ የግል ምልከታዎች ላይ የሚወሰን ከሆነ ዜጋ ጋዜጠኛ (Citizen Journalist) እና ጦማሪ (Blogger) ልዩነታቸው ምንድን ነው?**

ዜጋ ጋዜጠኝነት በአንድ አምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ የሚፈፀሙ በደሎችን በካሜራ፣ በድምፅ ማስቀረት ሊሆን ይችላል:: ጋዜጠኞች ሊገቡ በሚከለከሉባቸው ቦታዎች በቦታው ያሉ መረጃዎችን ለሕዝብ ማድረስ ነው አንዱ የዜጋ ጋዜጠኝነት ሚና:: አንድ የገጠር ከተማ ውስጥ ለሞት የደረሰን የተራበ ሕፃን ሁኔታ ጋዜጠኛ ገብቶ ለመዘገብ ላይፈቀድለት ይችላል:: በአካባቢው ይንቀሳቀስ የነበረ ሾፌር ምስሉን በካሜራ አስቀርቶ ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ ከለቀቀው ዜጋ ጋዜጠኛ ልንለው እንችላለን:: ዜጋ ጋዜጠኛ ጡመራን ሊደግፈው ይችላል እንጂ አንድ አይደሉም:: ጡመራ በብዛት ግለ አስተያየት ላይ የተመረኮዘ ነው:: አንድ ጦማሪ - ጦማር (ብሎግ) ካለው ባልኩህ መንገድ የዜጋ ጋዜጠኝነት ሚናም ሊጫወት ይችላል::

**አንድ ሰው የሚጦምረው ለምንድን ነው? [አጥናፍ ለምን ይጦምራል?]**

የምጽፈው ውስጤ የታመቀውን ነገር ሰው እንዲያውቅልኝ ስለምፈልግ ነው:: ሀሳቤን በነፃነት የመግለፅ መብቴን ለመጠቀም ስለምሻም ጭምር ነው::

ጋዜጣ ማንበብ በጣም እወዳለሁ:: የጋዜጦች መታፈን መበርታቱ ወደ 'ኦንላይን ሚዲያው' አቅርቦኛል:: አዲስ ነገር ጋዜጣ ተዘግታ አዘጋጆቹ ከአገር ሲወጡ ገበያ ላይ 'ነበር' የምትለው አውራምባ ታይምስን ብቻ ነበር:: እሱም ብዙም ሳይቆይ ተዘጋ:: ከዚያ በኋላ የነበረው አማራጭ ማኅበራዊ እና ኦንላይን ሚዲያው ነበር:: አሁን ያሉት ሚዲያዎች ከተደራሽነት አንፃር ከኦንላይን ሚዲያው ይበልጣሉ ብዬ አላስብም::

**ምንም አይገናኝም እንጂ። ብዙዎቹ የኅትመት ውጤቶች ካላቸው የኅትመት (ኮፒ) መጠን ይልቅ አንተ ያለህ የፌስቡክ ጓደኞች እና ተከታዮች ቁጥር ይበልጣሉ። የብዙዎችም እንዲሁ። [ሳቅ]**

[ሳቅ በሳቅ] በትክክል:: በአሁን ሰዓት የምትፈልገውን ሰው የምታገኘው በማኅበራዊ ሚዲያው እንጂ በመደበኛው ሚዲያ አይደለም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ባሕላዊ ሚዲያው እየሞተ ነው:: በርግጥ ዓለም ላይም የወረቀት ሚዲያው እየቀረ ነው:: ምክንያታቸው ግን ከቢዝነስ አንፃር እንጂ እንደ እኛ አገር በዕቀባ ምክንያት አይደለም::

## ስለ ኢንተርኔት ደኅንነት እና አክቲቪዝም

**የኢንተርኔት ደኅንነት ምን ማለት ነው?**

በሁለት መንገድ ከፍዬ ልንገርህ:: የሳይበር አሸባሪዎች (Cyber Terrorists) የሚባሉ አሉ:: አንድ ተቋም ላይ ጥቃት ለማድረስ የሚሠሩ ናቸው:: በሌላ ወገን ደግሞ በአምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ ፖለቲከኞችን፣ የሰብዓዊ መብት አራማጆችን፣ በጥቅሉ የተቀናቃኝ ጎራውን ለማፈን የሚሠሩ ሥራዎች አሉ:: ሁለቱም ወንጀሎች ናቸው:: እዚህ አገር የሚከሰሰው ግን የመጀመሪያው ብቻ ነው::

እዚህ አገር ውስጥ የኢ-ሜይል እና የሶሻል ሚዲያ አካውንቱ የማይበረበርበት ሰው አለ ብዬ አላስብም:: ዋስትና የለህም:: የኮምፒዩተር ደኅንነት ስንልም ከእነዚህ ዓይነት ሰርጎ ገቦች ራስህን ለመከላከል የምትሠራው የቴክኖሎጂ ሥራ ነው::

**እነዚህ ሰርጎ ገቦች ሥራቸውን የሚሠሩት ከተለያዩ የኮምፒዩተር ኔትወርኮች ላይ ጥቃት አድራሽ ፕሮግራሞችን ወደ አንተ ኮምፒዩተር በመላክ ነው?**

በትክክል! ለምሳሌ ኢ-ሜይል ባልታወቀ ሰው ይላክብህና ያንን ስትከፍት ኮምፒዩተርህ ላይ የማታውቀው ፕሮግራም ይወርድና እያንዳንዷ የተየብካትን ፊደል ወደ ሦስተኛ ወገን እንዲሄድ ያደርገዋል:: ይህም ማለት አካውንትህ ሙሉ በሙሉ በዚያ ወገን ቁጥጥር ስር ነው ማለት ነው:: የምስጢር ቁጥርህን ስታስገባ ወደ እነሱ ስለሚሄድ በቀላሉ ትበረበራለህ::

ኪይሎገር የሚባል ፕሮግራም ነበር:: ስፓም ሜይል (ያለ ተቀባዮች ይሁንታ ለብዙሐን የሚላኩ ኢ-ሜይሎች) ወይም ሜልዌር (የኮምፒዩተር ሥርዓትን ለማናወጥ እና ለመጉዳት የሚሠራ የኮምፒዩተር ፕሮግራም) ይመጣብህና እሱን ስትከፍተው ፕሮግራሙ ኮምፒዩተርህ ላይ ይጫናል:: ራሱን ደብቆም ይቀመጣል:: አንተ ኮምፒዩተርህ ንፁህ ይመስልሀል:: የኮምፒዩተርህን ገበታ አንድ ቁልፍ በነካህ ቁጥር ወደ ሦስተኛ ወገን ይሄዳል:: የሆነ ሰዓት ላይ ደግሞ ይህ የስለላ ሶፍትዌር በፎቶ መልክ መጥቶ ነበር:: ከኢንተርኔት ላይ ፎቶዎችን ወደ ኮምፒዩተር ስታወርድ ፕሮግራሙም አብሮ ይወርድና ሥራውን ይሠራል ማለት ነው - ስለላ::

**የሳይበር ጦርነት ወይም የኢንተርኔት ደኅንነት ቀውስ ዓለማቀፋዊ ችግር መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ እንደ ችግር ርዕስ መሆን ደረጃ ላይ ደርሷል? [መንግሥት ግለሰቦችን ከመሰለል ባለፈ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ለድርጅቶች እና ግለሰቦች ስጋት ናቸው?]**

ባደጉት አገራት ላይ ባንኮች የዚህ ችግር ተጋላጭ ናቸው:: የኢንተርኔት ወንጀል እየተሠራባቸው ይዘረፋሉ:: የኢትዮጵያ የባንክ ሲስተም ከባሕላዊ አሠራር ብዙም ፈቀቅ ያለ አይደለም:: ብዙ ሰው ብሩን የሚያንቀሳቅሰው የባንክ ደብተሩን ይዞ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሰ እንጂ ኦንላይን የባንክ ሥርዓት እየተጠቀመ አይደለም:: የኢንተርኔት የክፍያ ሥርዓት ገና

> **<<ይሄ የኮምፕዩተር ወንጀል ነው፣ ይሄ አብሪተኛ ነው>> ብሎ የሚለየው የትኛው ገለልተኛ ተቋም ነው? ሆን ተብሎ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚውን ለማጥቃት የወጣ አንቀፅ ነው። ያልተመቻቸውን ጽሑፍ <<አከሌ ሕዝብን ለመቀስቀስ፣ ለማሸበር ይህን ጽፏል>> ብለው ለመወንጀያነት ለመጠቀም ነው**

ኢምንት ነው:: እሱም ቢሆን አሥር ጊዜ ‹‹ኔትወርክ ተቋረጠ›› እየተባለ በአግባቡ እየተሠራበት አይደለም:: ስለዚህ የኢንተርኔት ደኅንነት ሥጋት አለብን ማለት አስቸጋሪ ነው::

ድረ-ገፃቸው 'ሀክ የተደረገ' አንዳንድ የመንግሥት ተቋማት አሉ:: ሀክ የተደረገው ግን 'ኢንዴክስ ፋይል' የምንለው የመጀመሪያ ገፃቸው እንጂ ዳታ ቤዛቸው አይደለም:: ስለዚህ ሰራቂው እዚያ ድረ-ገፅ የፊት ሽፋን ላይ የራሱን መልዕክት ይለጥፍ ይሆናል እንጂ ሌላ ምንም ሊያደርግ አይችልም:: አብዛኛዎቹ የመንግሥት ተቋማትም ድረ-ገፃቸው ላይ መረጃ ይለጥፋሉ እንጂ ዳታ ቤዝ የላቸውም:: ስለዚህ አሁን ባለንበት ደረጃ በግለሰቦችም ሆነ በድርጅቶች ደረጃ በአገራችን የኢንተርኔት ደኅንነት ስጋት ነው ማለት አይቻልም::

**በዚህ በኩል እኛ አገር ከግለሰብ የኮምፒዩተር ወንጀለኞች ይልቅ እንደ ስጋት የሚታየው መንግሥት ነው ይባላል። ምን ትላለህ?**

እዚህ አገር ድረ ገፆች ይታፈናሉ:: ዞን ዘጠኝ ሲመሠረት ወደ ሰባት ወይም ስምንት ብሎጎች ተዘግተውበታል:: በርካታ የዳያስፖራ ድረ-ገፆች አገር ውስጥ አይነበቡም:: ይህን የሚያደርገው ማን እንደሆነ ግልፅ ነው:: መንግሥትን ስትጠይቅ ግን ‹‹እኛ እንደዘጋነው ምን ማስረጃ አለህ?›› ይሉሀል::

**እንዲህ ብለው ቢከራከሩህ ምላሻቸውን በምን ፉርሽ ልታደርገው ትችላለህ?**

ከየትኛው ሰርቨር ኮምፕዩተር ላይ በተለቀቀ የእገዳ ትዕዛዝ እንደተዘጋብህ ለማወቅ ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን በጣም አቅም ይጠይቃል::

ብሎግህ ሌላ አገር ላይ እየታየ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የማይታይበት ምንም ምክንያት ስለሌለ ዘጊውን ለማወቅ አስቸጋሪ አይሆንም:: ኢትዮጵያ ላይ ከሚደርሰው የኮምፕዩተር ደኅንነት ስጋት በላይ መንግሥት ‹‹ተቃዋሚ ናቸው›› ብሎ የሚያስባቸው ግለሰቦች ላይ የሚያደርሳቸው ስጋቶች ይበልጣሉ::

ወደ ገፅ 23 ዞሯል



ዳዊት ከበደ
ወየሳ (አትላንታ - አሜሪካ)

# የዴሞክራሲ ቀለሞች፤ ከሽግግር እስከ ችግግር

ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ… የ"አትነሳም ወይ?!" መዝሙሮች ተደምጠዋል፤ በርካታ የተቃውሞ ሰልፎች እና የስራ ማቆም አድማዎች ተደርገዋል። የተቃውሞ ሰልፉ ከመብዛቱ የተነሳ ሁሉንም መዘርዘር ያታክታል። ለምሳሌ "የአጼ ምኒልክ ሃውልት ይፍረስ" የሚሉ ሰዎች ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የሃውልቱን ዙሪያ በጥቁር ጨርቅ ሸፈኑት። ይህ ዜና ተብሎ በሬድዮና በቴሌቪዥን ቀረበልን።

ከዚህ በኋላ የኢህአዴግ ሹማምንት የህዝቡን የጨኸት ትርታ ለማዳመጥ ጸጥ ሲሉ፤ እኛ ደ'ሞ 'ሃውልቱን በመድፍ እናፍርሰው ወይስ በቦንብ እንናደው ወይስ ዲሞክራሲያዊ መብቱን ጠብቀን በገመድ ጎትተን እንጣለው?' እያሉ የሚንሾካሾኩብን መሰለን። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን… ኦህዴድ እና ህወሃት በሃውልቱ መፍረስ ቢስማሙም፤ ኢህዴን (የአሁኑ ብአዴን) ሃሳቡን በመቃወም የራሱን ስብሰባ አደረገ። በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ላይ፤ "እኛ የታገልነው የምኒልክን ሃውልት ለማፍረስ ነው ወይ?" የሚል በሲቃ የታጀበ ንግግር ተደመጠ።

በዚህ ሁሉ ውዝግብ መሀል ግን… እኛ ጋዜጣችንን ለማሳተም የብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤትን ደጀ ሰላም ስንጠና፤ በድንገት ታይቶ የማይታወቅ የኦሮሞ ፈረሰኞች ከኮተቤ፣ ከሱሉልታ እና ከሰላሌ ተሰባስበው… የአጼ ምኒልክ እና የእቴጌ ጣይቱን ፎቶ ከፊት ለፊት ይዘው፤ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማን እያውለበለቡ አራት ኪሎን አቋርጠው፣ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኩል አድርገው፤ ራስ መኮንን ድልድይን ተሻግረው፤ ወደ ምኒልክ ሃውልት ተጓዙ። ብዙዎቻችን የዚህን ጉድ መጨረሻ ለማየት ፈረሰኞቹን ተከተልናቸው። ፈረሰኞቹ አራዳን አልፈው ከአጼ ምኒልክ ሃውልት ዘንድ ሲደርሱ ሃውልቱን ክብ እየዞሩ ቀረርቶ እና ጌራርሳ እያሰሙ፤ ከጥቂት ቀናት በፊት ሃውልቱ የተሸፈነበትን ጥቁር ጨርቅ ቀደው እና ቀዳደው ጣሉት። (ይህን ለምስክርነት የምንናገረው በወቅቱ ኢዜአ ያልዘገበው… ህዝቡ በአይኑ የታዘበው፣ የሴቶች እልልታ የወንዶች ፉጨት ያጀበው ታሪካዊ ትእይንት ስለነበር ነው።)

ከዚያ በኋላ እንኳንስ ሃውልቱ ሊፈርስ ቀርቶ፤ ጭራሽ ወርቃማ እና ብርማ ቀለም እንዲቀባ አደረጉ - ህዝቡና የልጅ ኢያሱ ልጅ።

አጼ ምኒልክ በያዙት ጦርም ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ተደርጎበት፤ ቢያንስ ለብዙ ወራት ቆየ። በጨዋታችን መጀመሪያ ላይ ይህን ጉዳይ የምናነሳሳው… የህዝብን ሃያልነት ማሳያ ምስክር እንዲሆነን ጭምር ነው። ሆኖም የዴሞክራሲ ቀለም ደምቆ እንዲዋብ ህዝቡ መብቱን አውቆ ማስከበር መቻል አለበት። አስቡት። በሽግግር መንግስቱ ዘመን የአጼ ምኒልክ ሃውልት ፈርሶ ቢሆን ኖሮ፤ እንደ ሌኒን ሃውልት የት እንደ ደረሰ ላይታወቅ ይችል ነበር። ክብር ሃውልቱን ለታደጉ ጀግኖች ሁሉ ይሁን።

እንዲህ የአገር ቅርስን በሰላማዊ ሰልፍ የማስተረፍ ስራ የመሰራቱን ያህል፤ ፈገግ የሚሰኙ አይነት ሰልፎችም ተካሂደው ነበር። ከእነዚህ አንዱ ጭር ሲል የማይወደው ኢህአዴግ ያዘጋጀው የህጻናት ሰላማዊ ሰልፍ ነው። ሰልፉ በሴቶች ቢሮ በኩል አድርጎ ለአደባባይ የበቃው፤ የእናት ጡት ወተትን አስፈላጊነት ግንዛቤ ለመፍጠር በሚል ነበር። እናም አንድ ቀን የአካባቢው ትምህርት ቤቶች ተዘግተው… የህጻናት ሰልፍ አራት ኪሎን እንዲያጨናንቅ ተደረገ። የህጻናቱም ጥያቄ አንድ እና አንድ ብቻ ሆነ። አንዷ "የእናት ጡት ለህጻናት!" ስትል ሁሉም በአንድ ድምጽ "የእናት ጡት ለህጻናት" እያሉ ከጠቅላይ ሚንስትሩ ግቢ ደረሱ።

ከያዙት መፈክር ጎን፤ የተዘቀዘቁ ትላልቅ የጡጦ ስዕሎች አሉ። ሁሉም ደግመው ደጋግመው "የእናት ጡት ወተት ለህጻናት።" የሚለውን መፈክር እንደ ውዳሴ ማርያም ይደጋግሙታል። እንዲህ እንዲህ እያሉ በጠቅላዩ ሚንስትር ደጃፍ ትንሽ ቆዩ። በኋላ ላይ የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች በስፍራው መኖራቸውን ካረጋገጡ በኋላ የጠቅላይ ሚንስትሩ ተወካይ ሽክ

**በረከት ስምኦን ራሱ ቃል በቃል እንዲህ ብሎን ነበር፡- "በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ሥሩ የሚሉ ቅዠታሞች አሉ። ዓባይ ቢገነባ ኢትዮጵያ በውሃ ተጥለቅልቃ እናልቃለን እንጂ፤ ምንም አናተርፍም።" ብሎ መግለጫ ጭምር ሰጥቶ ነበር**

ብለው መጡ። እንዲህም አሉ።

"እርግጥ ነው። ህጻናት የእናት ጡት ወተት ያስፈልጋቸዋል።" ካሉ በኋላ የጠቅላይ ሚንስትሩ ተወካይ… የእናት ጡት ወተት ለህጻናት አስፈላጊ መሆኑን አስረዱ። "አሁንም የእናት ጡት ለህጻናት አስፈላጊ መሆኑን ስለተረዳን፤ የሽግግር መንግስቱ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርግላችኋል።" ሲላቸው ከህጻናቱ ጋር የመጡት እናቶች አጨበጨቡ፤ ህጻናቶቹም ተንጫጩ። የሽግግር መንግስቱን አመስግነው ከመበተናቸው በፊት፤ ጋዜጠኞች ለአንዳንድ ህጻናት ጥያቄ አቀረብን።

"ጥያቄያቹህ የእናት ጡት ወተት ማግኘት ነው። አሁን እንደ ሰማነው 'የሽግግር መንግስቱ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል' ተብሏል። እንዴት ↗

ታዩታላቹህ?" አልናቸው፡፡

አንደኛው ህጻን ተገርሞ እኛንም ጓደኞቹንም እያየ፤ "የሽግግር መንግስቱ ጡት አለው እንዴ?" ሲል፤ እኛም ሆንን ጓደኞቹ ዛሬም ድረስ ያልመለስነውን ጥያቄ አቀረበልን፡፡

እንዲህ አስቀው የሚያስቁ ሰላማዊ ሰልፎችን ጎን ትተን፣ ወደ ኋላ ተመልሰን ስንመለከት ግን… ከምንወቃቀስበት ጉዳይ ይልቅ የምንሞጋገስባቸው ጉዳዮች ብዙ አሉን፡፡ ከምንም በላይ "ጨርቅ" ተብላ የተንቋሸሸች ሰንደቅ አላማችን፤ ከወደቀችበት ተነስታ ከፍ ብላ መውለብለቧ ይሰመርበት፡፡

"አባይ ተገንብቶ ለልማት ይዋል፡፡" ስንል፤ በረከት ስምኦን ራሱ ቃል በቃል እንዲህ ብሎን ነበር፡- "በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ሥሩ የሚሉ ቅዠታሞች አሉ፡፡ ዓባይ ቢገነባ ኢትዮጵያ በውሃ ተጥለቅልቃ እናልቃለን እንጂ፤ ምንም አናተርፍም፡፡" ብሎ መግለጫ ጭምር ሰጥቶ ነበር፡፡ በኋላ ላይ የአባይ ግድብ ግንባታ ሲታወጅ ዋና ተዋናይ ሆኖ፤ ጉዳዩን ለፖለቲካ ጥቅም ሲመነዝረው እያየን… "ወይ ጊዜ" ያልንበት ወቅት ሩቅ አይደለም፡፡ በዚያም ተባለ በዚህ፤ ለሰንደቅ አላማችን ከፍ ማለትም ሆነ ለአባይ መገደብ ትልቁ ምክንያት ሳያሰልስ ይታገል የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አለመሆኑን እነሱም ያውቁታል፡፡ በመሆኑም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ህዝባዊ መብቱን ተጠቅሞ የዴሞክራሲው ቀለም እንዲደምቅ፤ የህዝብ ፍላጎት እንዲጠበቅ ያደረገው የኢትዮጵያ ህዝብ… ከምንም በላይ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

ከሽግግር መንግስት እስከ ችግግር ዘመናችን ድረስ ብዙ አሳልፈናል፡፡ አሁንም በትዝታ ወደ ሽግግሩ መንግስት ዘመን እንውሰዳችሁ፡፡ ከሃያ አመታት በፊት ነው፡፡ ብዙዎቹ ሰልፈኞች መፈክር እያሰሙ ወደ ጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ ያመራሉ፡፡ በወቅቱ ጠቅላይ ሚንስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ናቸው፡፡ ሰልፈኞቹ በመፈክራቸው መጀመሪያ እና በደብዳቤያቸው መጨረሻ ላይ "የሽግግር መንግስቱን ቻርተር እንደግፋለን" የሚል ሙሻሙሾ የሚያወርዱ ከሆነ፤ የሰልፈኞቹ ተወካዮች ወደ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጉና ያናግሯቸዋል፡፡ ሰልፉን እራሱ ኢህአዴግ ያቀናበረው ከሆነ ደግሞ ሃያ እና ሰላሳ ሰው ያለበትም ቢሆን፤ በሬድዮ፣ በቲቪ፣ በጋዜጣም ጭምር ስለሰላማዊ ሰልፉ ብዙ ይባልለታል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ከሚሆኑት መካከል፤ "ፓትርያርኩ ስልጣናቸውን እንዲለቁ ሰላማዊ ሰልፈኞች ጠየቁ" የሚለው ዜና አንደኛው ነበር፡፡

በምሽቱ ዜና ላይ… "ፓትርያርኩን በመቃወም ከወጡት ሰልፈኞች መካከል አንዳንዶቹ እንዲህ በማለት አስተያየት ሰጥተዋል ይባልና… በቃለ መጠይቁ ላይ ከሚቀርቡት ሰዎች አንዱ፣ "ፓትርያርኩ በደርግ ዘመን ያገለገሉ ስለሆኑ አንቀበላቸውም" ይላል፡፡ ሌላኛው አስተያየት ሰጪ… "የደርግ ኢሰፓ አባል ናቸው" ብሎ ይከሳቸዋል፡፡ ቀጥሎ ያለው ደግሞ "ከስልጣናቸው ወርደው ለፍርድ ይቅረቡ" በማለት ይደነፋል፡፡ አቡነ መንቆርዮስም ይህን ድራማ አዘል የተቃውሞ ሰልፍ ማታ ላይ በቲቪ ሲመለከቱ ልባቸው ተሰብሮና መንፈሳቸው ተሸብሮ፤ በንጋታው ኢትዮጵያን ለቀው ወደ ጎረቤት አገር እንዲሰደዱ የተደረጉበትን፤ በ'ሳቸውም መንበር አባ ጳውሎስ እንዲተኩ የተደረገበትን ድራማ እንደትላንት የምናስታውስ ብዙዎች ነን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ… የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች… በማንም በምንም አይነት ተቀባይነት አይኖራቸውም ነበር፡፡ ከኤርትራ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ፤ ከስራ የተባረሩ ሰራተኞች፤ ጡረታቸውን የተነጠቁ አባቶች፤ በብሄራቸው የተገፉ ዜጎች፤ ኢትዮጵያዊነትነትን ከፍ አድርገው የዘመሩ የሌላ ብሔር አባሎች… የ'ነዚህ ሰዎች ጩኸት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል፡፡ "መብታችን ይከበር" የሚሉ ድምጾች በአራት ኪሎ ጎዳና ላይ ብዙ ተደምጠዋል፡፡ አንዳንዶቹ ምላሽ ሲያገኙ፤ የተቀሩት ደግሞ ጩኸት ብቻ ሆነው ቀርተዋል፡፡ በኋላ በኋላ ላይ… የማይቀረው ህዝባዊ መዝሙር እና መፈክር የአራት ኪሎን ግቢ ሲያነቃንቀው "ጠቅላይ ሚንስትሩ ስራ ላይ ናቸው… አትጬኹ" በሚል የታጠቁ የወያኔ ሰዎች ወደ ላይ እየተኮሱ ጩኸቱን ይብሱን አባብሰው ሰልፍ መበተን ጀመሩ፡፡

በጋዜጠኝነታችን የህዝቡን ድምጽ ለማሰማት፤ በስፍራው ተገኝተን ክፉና ደግ መታዘባችን አልቀረም፡፡ ሰላማዊ ሰልፈኞች ሰፈር አቋርጠው ሲመጡ በእጃቸው መፈክር ተሸክመው፤ አንዳንዶችም ዘንባባና የዛፍ ቅጠል ይዘው 'ሆ' እያሉ ጠቅላይ ሚንስትሩ ሰፈር ይደርሳሉ፡፡ እዚያ ሲደርሱ መጮህ ስለማይቻል ተወካዮቻቸው ወደ ውስጥ እስከሚገቡ ወይም ደብዳቤውን እስከሚያስረክቡ ድረስ፤ አገር ሙሉ ሰልፈኛ ጥላ ፍለጋ በየአጥሩ ጥግ ለሰአታት ያህል ይቀመጣል፡፡ በዚህ አይነት መሰላቸት ሰዓታት ያልፉና ሰልፈኞች ወደየጉዳያቸው ይበተናሉ፡፡ ከየመንደሩ ይዘዋቸው የመጡት ቁሳቁሶች፤ የካርቶን ላይ ጽሁፎች፣ የወረቀት ስእሎች፣ የጨርቅ ላይ መፈክሮች እዚያው ይጣሉና አካባቢው እብድ የጨፈረበት ገበያ ይመስላል፡፡ ሰልፈኞቹ ከተበተኑ በኋላ ወረቀትና ጨርቁን የሚሰበስቡ ሰዎች ይመጡና ያን ሁሉ ግሳንግስ ሰብስበው ያቃጥሉታል፡፡ ልክ እንደ ተቃጠሉት የመፈክር ካርቶኖች… በሽግግር መንግስቱ እና ከዚያ በኋላ የተነሱ በርካታ ህዝባዊ ጥያቄዎች፤ ምላሽ ሳያገኙ ዶግ አመድ ሆነዋል፡፡ ብዙዎቹ የ"መብታችን ይከበር" ጥያቄዎች ግን ከወረቀት ባለፈ፤ በህዝብ ልብ ላይ የታተሙ በመሆናቸው በውድ ሳይሆን በግድ ተከብረዋል፡፡

እነዚህ ተሸራርፈውም ቢሆን… ለአጭር ጊዜም ቢሆን… ብልጭ ድርግም እያሉም ቢሆን… ህዝቡ እንዲከበሩለት ያደረጋቸው መሰረታዊ የመብት ጥያቄዎች… ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፤ የመሰብሰብና የመደራጀት፣ በነጻ ዳኝነት ፍርድ ማግኘት፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና የህዝባዊ ስልጣን መረጋገጥ ናቸው፡፡ "እነዚህ የመብት ጥያቄዎች በተገቢው መልክ ተግባራዊ ሆነዋል" ብሎ ክርክር የሚገጥም ካለ ውሸታም እንጂ ሌላ ስም አይሰጠውም፡፡ ግን እነዚህ የዴሞክራሲ ደማቅ ቀለም የሆኑ የመብት ጥያቄዎች፤ መንግስት በቸርነቱ ሳይሆን፤ ህዝብ በእምቢ ባይነቱ ያገኛቸው የትግል ስጦታዎች ሆነዋል፤ ይህ እውነት ነው፡፡ 'እነዚህ መብቶች በመንግስት በኩል ከመከበር ይልቅ ተሸርሽረው ተሸርሽረው እያለቁ ናቸው፡፡' ብንል ይህም ሌላ እውነት ነው፡፡

እውነትን መደርደር የሚያስጣላ እና የሚያከራክር ነገር አይደለም፡፡ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መንግስት የሚያሳስበው ባይሆን ኖሮ፤ ሌላ ተዛማጅና ግራ ተራማጅ ህጎች ማውጣት ባላስፈለገው ነበር፡፡ ህገ መንግስቱ ሲረቅና ሲጻፍ ሁሉንም ወገን የሚያረካ ሆኖ አልተዘጋጀም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ግን… የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶች እንደሚከበሩ ይደነግጋል፡፡ ይህ ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለስላሴም ሆነ በደርግ ህገ መንግስት ላይ በግልጽ የተካተተ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ መሰረታዊ መብቶች በጽሁፍ እንጂ በተግባር ባልተረጋገጡባት አገር… በአሳዛኝ መልኩ ትውልድ አልፎ ትውልድ በመተካት ላይ ይገኛል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ… ሰብአዊ መብት፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣ የፍትህ፣ የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብት ሙሉ ለሙሉ ያልተረጋገጠባት አገር፤ "ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" የሚለውን ስም ለመሸከም አቅም አይኖራትም፡፡ ይህን እያልን… መብታችን እየተበዘበዘ፤ የዲሞክራሲ ቀለም እየደበዘዘ ሊሄድ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ግን ለዘላለሙ አይቀጥልም፡፡ የሰው ልጅ… እስከ ልጅ ልጁ እየተረገጠ ሊገዛ አይችልምና… ጨለማ በጠዋት ጮራ እንደሚገፈፍ ሁሉ… የደበዘዘው የዲሞክራሲ ቀለም የሚደምቅበት ምዕራፍ ቀስ በቀስ መምጣቱ የተፈጥሮ ግዴታ ነው፡፡

ከማጠቃለላችን በፊት የዚህን ጽሁፍ ዋና መልእክት እዚህ ላይ ለማስፈር ወደድን፡፡ ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ የሽግግር መንግስት አቋቋመ፡፡ እኛም (አብዱራህማን አህመዲን እና ሙሼ ሰሙ) ጋር በመሆን "የኢትዮጵያ ወጣቶች ህብረት" የሚባል ሊግ አቋቋምን፡፡ አላማችን ወጣቱን በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ ማሰባሰብ ነበር፡፡ እንደ ታሰበውም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ህብረቱን ተቀላቀሉ፡፡ እንቅስቃሴው አዲስ አበባን አዳረሰ፡፡ ስብሰባ የምንጠራባቸው አዳራሾች እስከ አፍንጫቸው ድረስ እየሞሉ ህዝቡ በውጭ ሆኖ ስብሰባውን ይከታተል ጀመር፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ከመንግስት የምዝገባም ሆነ የስብሰባ ፈቃድ ተሰጥቶን አያውቅም፡፡ (በ'ርግጥ ኢህአዴግ፤ በኋላ ላይ ሊጉን በጉልበት አፈረሰው) ወጣትነት ደፋር ያደርጋል፡፡ የመሰብሰብና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብታችንን መንግስት እንዲሰጠን ስላልፈለግን እኛም በህዝብ ጉልበት መብታችንን አስከበርን፡፡ ከምንም በላይ ግን፤ "መንግስት መብት ይሰጥሃል እንጂ፤ መብትህን አያስጠብቅልህም፡፡" የሚለው መመሪያችን ተስማምቶናል፡፡ እውነት ነው፡፡ መንግሥት መብትህን በሕግ እና በሕገ-መንግሥት ላይ ጽፎ ይሰጥኻል እንጂ፤ መብትን የማስጠበቅ ኀላፊነት የሚጣለው በ'ያንዳንዱ ግለሰብ እና ማኅበረሰብ ላይ ይሆናል፡፡

መሰረታዊ መብቶቻችን በህጉ እና በህገ መንግስቱ ላይ እንዲሰፍሩ ትውልድን የተሻገረ ትግል ተካሂዷል፡፡ እነዚህን መብቶች በውድም ሆነ በግድ ተግባራዊ ስናደርግ፤ አምባገነናዊ አስተዳደር እየወደቀ፤ የዴሞክራሲ ቀለም እየደመቀ ይሄዳል፡፡ ከሽግግሩ መንግስት እስከ ችግግሩ ዘመን ድረስ የሄድንበት መንገድ… የግልና የወል መብትን የማስጠበቅ ታሪክን የያዘ ባለብዙ ምእራፍ ታሪክ ነው፡፡ በሁሉም ምእራፎች መብታችንን ለመጨፍለቅ ጥረት ሲደረግ እንጂ ስንወድቅ አልታየንም፡፡ አሁንም ከመጨረሻው ምእራፍ በፊት የመጨረሻውን ጩኸት እየጮሁ፤ "በህግ አምላክ!" የሚሉ ደፋሮች አልታጡም፡፡ የ'ነሱ ጩኸት ከዳር እስከ ዳር እንዲደመጥ፤ የለኮሱት ሻማ ብርሃን እንዲሰጥ… የዲሞክራሲ ቀለሞች በብዕሮቻቸው ጫፍ እንዲደምቅ ለሚያደርጉት ትግል ህዝቡ ሊያግዛቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ከሽግግር መንግስት እስከ ችግር ዘመናችን ድረስ ብዙ ጊዜ ወድቀን፤ ብዙ ጊዜ ተነስተናል፡፡ በዚህ የቀራንዮ መንገድ ላይ ብዙዎች ወድቀው ቀሩ፣ ሌሎች መንገዳቸውን ቀየሩ፡፡ አንዳንዶች ሞቱ፤ ሌሎች ታሰሩ፤ ብዙዎች ተሰደድን፡፡ እንዲህም ሆኖ ከያለንበት የምንጮኸው ወድቀን እንዳልቀረን ለማብሰር ጭምር ነው፡፡ የዴሞክራሲ ቀለሞች እስከሚደምቁ ድረስ ድምጻችንን እናሰማለን፡፡ እንደ ዘፈን አዝማች፤ "መንግስት መብት ይሰጥኻል እንጂ፤ መብትህን አያስጠብቅልህም፡፡" እንላለን፡፡ ጎበዝ! እንግዲህ ለራስህ እወቅበት፡፡

ጸረጀ መላኩ
tilahungesses@gmail.com



# ስንቱን የሀገር ሀብት አጣን? !

ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በሀገራችን ህልውና ላይ ከፈጸሙት ስህተቶች ሁሉ ትልቁ የሀገራችንን ታሪካዊም ይሁን ህጋዊ መብት ወደጎን በመተው በግል ውሳኔያቸው ኤርትራን በተመለከተ በአቶ ኢሳያስ የሚመራው ቡድን የጠየቃቸውን ሁሉ ያለአንዳች ማመናታት መስጠታቸው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ለንደን ላይ ተደርጎ በነበረው የሰላም ድርድር ሚስተር ኸርማን ኮሆን ለአቶ መለስ ዜናዊ የምጽዋን ወደብ ኢትዮጵያ እንድትጠቀም የሚያስችል መላ ሲያቀርቡ ፍላጎት እንዳለሳዩ ይነገራል፡ ፡ በአውሮፓውያን አቆጣጠር 1994 ዓ.ም የፈጸሙትን ስህተት ደግሞ በ1998 ማረም የሚያስችላቸው ሁኔታ ቢፈጠርም ይህንን እድል ሳይጠቀሙበት ሆን ብለው ማለፋቸው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም እድሉን እንጠቀምበት ያሉትን ሁሉ በተለያየ የሀሰት ክስ በመክሰስ ማሰራቸው፣ ከስራ ማባረራቸው፣ ማሰቃየታቸው …ወዘተ በታላቅ ምሬትና ሀዘን የሚታወስ በሀገራችንም ታሪክ እንደ ትልቅ ጠባሳ የሚቆጠር የታሪክ አሻራ ነው።

ይህ መሰረታዊ ስህተት በሀገራችን ላይ እያደረሰ የሚገኘው አደጋ እስከዛሬም በብዙ መልኩ ለዕድገታችንም ሆነ ለመሰረታዊ ህልውናችን አደጋ ሆኖ ይገኛል። በዚህ ጽሑፍ ይህ ስህተት በአሁኑ ሰዓት ከሚታየው ረሀብና በህዝባችን ላይ ከደረሰው አደጋ እንዲሁም ከመሰረታዊ የልማት ጉዞ አኳያ ያስከተለውን ተጽዕኖ በመጠኑ ያሳያል የሚል ግምት አለኝ። ይህንንም በማድረግ ከእርስ በእርስ ፍራቻ ተላቅቀን፣ ‹‹ካፈርኩ አይመልሰኝ›› የሚል ስሜትን አስወግደን እያንዳንዳችን የፖለቲካ ልዩ ተጠቃሚ ሳይሆን ሀገርንና ህዝብን ለመታደግ ምን መደረግ እንዳለበት ለመነጋገር ተጨማሪ መንደርደሪያ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

## ታሪካዊ የባህር በሮቿን የተነጠቀቻው ኢትዮጵያ፤ ያጋጠማት የኢኮኖሚ ድቀት

ኢትዮጵያ ከምትገኝበት እጅግ ወደ ኋላ ከቀረ ሁኔታ ለመላቀቅ እጅግ ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወይ ገቢዋን እጅግ ማሳደግ ይኖርባታል ወይም ደግሞ ወጪዋን መቀነስ ይኖርባታል። ከገቢ ውጪ የሚተርፍ ገንዘብ ነው አንድን ሀገር ሀብት እንድታከማች ወይም አዳዲስ የልማት ስራዎችን ለመስራት አቅም እንዲኖራት ወይም ለክፉ ጊዜ የሚሆን መጠባበቂያ እንዲኖራት የሚያደርገው።

በሀገራችን አሁን እየተካሄደ ነው እየተባለ የሚነገረን የልማት ስራ በአብዛኛው የሚካሄደው ወይ በእርዳታ ወይም በብድር በሚገኝ ገንዘብ ነው። ይህ የራሱ ችግር አለው። ብድር ጊዜውን ጠብቆ ከነወለዱ መከፈል ይኖርበታል። ይህ ሲሆን ደግሞ ያለ የሌለን ሀብት አሟጦ ለአበዳሪው ነው የሚያስረክበው። በአብዛኛው የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች፣ የተበደሩትን ገንዘብና ወለዱ ለመክፈል ከሚችሉት አቅም በላይ እየሆነ ከማይወጡበት ማጥ ውስጥ እንደሚወድቁ የሚታወቅ ነው፡ ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚሁ ሁኔታ ሰለባ ነበረች። ኢትዮጵያ የብድሯን መጠን ለመክፈል ከምትችለው በላይ እንደሆነ ታውቆ ከዓመታት በፊት የብድር ምህረት (ብድር ስረዛ) ተደርጎላት ነበር። አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ የምትበደረው ገንዘብ ከዓመት አመት በፈጣን ሁኔታ እያደገ ነው፡ በዚህ ከቀጠለም ለመጭው ትውልድ የምታስተላልፈው እዳ እንጂ ሀብትን አይሆንም።

የሀገራችንን ያለ የሌለ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ በማራቆት ላይ የሚገኘው አንዱ ወደውጪ ለሚላከውና ወደሀገር ለሚገባው ሸቀጥና ምርት የምትከፍለው የወደብ ኪራይና የቀረጥ ወጪ ነው። ይህ ወጪ ከአመት አመት እየጨመረና ከአቅም በላይ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው።

ይህ ሁሉ እዳ የመጣብን ደግሞ ባለሁለት ወደብ የነበረችው ሀገራችን ወደብ አልባ በመሆኗ ነው። በዚህ አንጻር ለኢሳያስ አፈወርቂ (ሻዕብያ) አገዛዝ አሳልፎ የተሰጠው የኢትዮጵያ ታሪካዊና ህጋዊ ግዛት በመሰረታዊ እድገታችንና አቅም ግንባታ ላይ እያደረገ ያለውን ቀጥተኛ ተጽዕኖ በመጠኑም ቢሆን መመልከት ይጠቅማል።

ሻዕቢያ ኤርትራን ተረክቦ አስመራ ላይ መንግስት ከመሰረተ ወዲህ ኢትዮጵያ በአሰብም ሆነ በምጽዋ ወደቦች በኩል ለምታስገባውም ሆነ ወደውጭ ለምትልከው ምርት (እቃ) ለአቶ ኢሳያስ መንግስት ቀረጥ እና የወደብ ኪራይ ስትከፍል ቆይታለች። በአውሮፓ አቆጣጠር ከ1998 ዓ.ም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወዲህ ደግሞ የአሰብንም ሆነ የምጽዋን ወደብ መጠቀም አቁማ የወጪና የገቢ ንግዷን በጅቡቲ በኩል ካደረገች በኋላ ለጅቡቲ የምትከፍለው ገንዘብ እጅግ ብዙ ሆኗል። ይህ ወጪ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ የገቢና ወጪ ንግድ ዘጠና ከመቶ (90%) ያክሉ የሚካሄደው በጂቡቲ በኩል ነው። የኢትዮጵያ የፋይናንስና የኢኮኖሚ እድገት ሚኒስቴር የነበሩት አቶ አህመድ ሽዳ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 ዓ.ም ላይ እንደተናገሩት ‹‹ኢትዮጵያ ለባህር ወደብ ክፍያ በየዕለቱ ሁለት ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ትከፍላለች›› ይህም ማለት የሀገሪቱን የውጭ ንግድ 16% ያክሉን ለጅቡቲ የወደብ ኪራይ ታስረክባለች ማለት ነው። ወይ ነዶ! (ይህንን መረጃ http://addisstandard.com… ላይ ማግኘት ይችላሉ)

በአጭሩ ኢትዮጵያ ለሚጢጢዋ ጅቡቲ ላሜ ቦራ ሆናለች። እልፍ አእላፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች ደማቸውን ያፈሰሱለት የቀይ ባህር የተፈጥሮ በር እንዲህ እንደ ዋዛ መዘጋቱ ሲታሰብ በእውነቱ ልብን ያደማል፣ ሆድንም ይበጠብጣል።

የአለም ባንክ የ2013 ሪፖርት እንደሚያሳየው፣ የራሳቸው ወደብ የሌላቸው ሀገሮች አንድ ኮንቴነር እቃን ወደውጭ ለመላክ የሚያወጡት ውጪ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2006 ዓ.ም 2220 የአሜሪካን ዶላር ነበር። ይህ ዋጋ በ2013 ዓ.ም ወደ 3000 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። ባንጻሩ የራሳቸው ወደብ ያላቸው ሀገሮች ለተመሳሳይ ኮንቴይነር ወጫቸው በግማሽ (50%) ዝቅ ይላል። http://addisstandard.com/ethiopia-spending-two-million-usd-per-day-for-transit-costs/

ይህን ሁኔታ ከሀገራችን እውነታ ጋር ✍

**“ራሱ መንግስት ያመነው ለጅቡቲ የሚከፈለው በቀን ሁለት ሚሊየን ዶላር የወደብ ወጪ የራሳችን ወደብ ቢኖረን ወጪው በ50% ይቀንስ ነበር ብለን ብናስብ እንኳ የራሳችን ወገን የሆነውን የአፋር ህዝብ መኖሪያ የሆነውን የአሰብን ወደብ መጠቀም ባለመቻላችን የምንከፍለው እዳ በቀን በቀን አንድ ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ማለትም በአሁኑ ምንዛሬ ስሌት (በ21 የኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ በቀን 21 ሚሊየን ብር)፣ በዓመት ደግሞ 365 ሚሊየን ዶላር ማለትም 7 ቢሊየን 665 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ያክል ኢትዮጵያ ታጣለች ማለት ነው ። ይህ በዝቅተኛ ስሌት ሲታሰብ ነው**

ስናዛምደው እጅግ የሚዘገንን ሁኔታን እናያለን፡ ፡ ራሱ መንግስት ያመነው ለጅቡቲ የሚከፈለው በቀን ሁለት ሚሊየን ዶላር የወደብ ወጪ የራሳችን ወደብ ቢኖረን ወጪው በ50% ይቀንስ ነበር ብለን ብናስብ እንኳ የራሳችን ወገን የሆነውን የአፋር ህዝብ መኖሪያ የሆነውን የአሰብን ወደብ መጠቀም ባለመቻላችን የምንከፍለው እዳ በቀን በቀን አንድ ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ማለትም በአሁኑ ምንዛሬ ስሌት (በ21 የኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ በቀን 21 ሚሊየን ብር)፣ በዓመት ደግሞ 365 ሚሊየን ዶላር ማለትም 7 ቢሊየን 665 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ያክል ኢትዮጵያ ታጣለች ማለት ነው ። ይህ በዝቅተኛ ስሌት ሲታሰብ ነው።

በዚህ ስሌት ላለፉት 15 ዓመታት ብቻ የደረሰውን አላስፈላጊ ወጪ ለማስላት (የባከነ ገንዘባችን) የዶላሩ ምንዛሬ በየጊዜው ስለሚለዋወጥ በማዕከላዊ ደረጃ ምንዛሬው 1 ዶላር በ 17 የኢትዮጵያ ብር ነበር ብለን ብንወስድ በ15 አመት ውስጥ ያጣነው 15 X 365 = 5,475,000. (አምስት ቢሊየን አራት መቶ ሰባ አምስት ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር) በማዕከላዊ ምንዛሬ በአንድ ዶላር 17 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ሲመነዘርም ዘጠና ሶስት ቢሊየን ሰባ አምስት ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር ያክል ነው።

የገንዘቡን መጠን በማየት ብቻ ሥርዓቱ የወሰደው አርቆ አሳቢነት የጎደለው እርምጃ ምን ያህል ኪሳራ በሀገራችን ላይ እንዳደረሰ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በዚህ ገንዘብ በሀገራችን ውስጥ ምን ማድረግ ይችላል (ይችል ነበር) የሚለውን መመልከት ደግሞ የሁኔታውን ተጽዕኖ ይበልጥ ለመረዳት እንድንችል ይረዳናል።

## የኢትዮጵያ ህዝብ እየከፈለ የሚገኘው ቀጣይ ዋጋ

ባለፉት 15 አመታት የተከሰተውን ድርቅ ሙሉ በሙሉ ያለምንም የውጭ እርዳታ መቋቋምና አንድም ህጻን በረሀብ እንዳይሞት ማድረግ ይቻል ነበር። ሀገራችን ባለፉት 15 አመታት ውስጥ ተከታታይ ድርቅና ረሀብን አሳልፋለች። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ሁሉ ችግሩን ለመወጣት የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚመጣው በማያቋርጥ ልመና፣ በአብዛኛው ከባዕዳን በተለይም ከምዕራቡ መንግስታት ነው።

ብዙ ሰዎች ‹‹ችግሮችን ያስከተለው የዝናብ እጥረትና ድርቅ የተፈጥሮ ውጤት ስለሆኑ እነዚህ ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ናቸውና ማንም ሊወቀስበት አይገባም›› ይላሉ። ይህ ትክክል አይደለም፣ ‹‹ድርቅ ተፈጥሯዊ ነው›› ብንል እንኳ፣ ‹‹ኢትዮጵያ ይህ አይነቱን የተፈጥሮ መለዋወጥ የሚያስከትለውን አደጋ ለመቋቋም ለምን በቂ መጠባበቂያ አላከማቸችም?›› ወደሚለው ጥያቄ ይወስደናል። የተለያየ መረጃ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ሀገራችን ወደብ አልባ እንድትሆን በመደረጉ የተነሳ የምንከፍልውን ወጪ ማስወገድ ብንችል በየጊዜው የተከሰተውን ረሀብ ያለአንዳች የውጭ እርዳታ ለመቋቋም የሚያስችል ሀብት ማከማቸት ትችላለች ። ይህን በመረጃ ለመመልከት ያክል በምዕራባውያን አቆጣጠር በ2008 ዓ.ም የተከሰተው 10 ሚሊየን ወገኖቻችንን ያጠቃውን ድርቅ ለመቋቋም ሀገራችን ያስፈልጋታል ተብሎ የነበረው US$ 460 ዶላር ነበር። (http://www.wfp.org/…) ይህ ገንዘብ በአንድ አመት ከሶስት ወር ውስጥ ለጅቡቲ ለወደብ የምንከፍለው ገንዘብ ነው።

አሁን በ 2015 /2016 ከኤልኒኖ (El Niño) ጋር በተዛመደ የተከሰተው ድርቅ እስከ 15 ሚሊየን የሚጠጉ ወገኖቻችንን በረሀብ እየገረፈ ይገኛል። ‹‹ይህን አደጋ ለመቋቋም በሚቀጥሉት ስድስት ወራት $ 285 ሚሊየን ዶላር ወይም 173 ሚሊየን ዩሮ ያስፈልጋል›› ሲል የተባበሩት መንግስታት የምግብ ፕሮግራም ገልጧል። (http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/8319741.stm) ምናልባትም ‹‹በአመት ውስጥ ከላይ የተገለጸው ገንዘብ ሁለት እጥፍ ያስፈልጋል›› ብለን ብንገምት በአጠቃላይ እስከ 855 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ያስፈልጋል ማለት ነው።

ዴሰምበር 9፣ 2015 ዓ.ም ታትሞ ለንባብ የበቃው ሪፖርተር ጋዜጣ የሀገሪቱን ባለሥልጣናት ጠቅሶ አሁን የሚታየው ድርቅ እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመቋቋም 1.4 ቢሊየን ዶላር እንደሚያስፈልግ ዘግቧል። (http://vps17307.inmotionhosting.com…)

ኢትዮጵያ በየአመቱ 365 ሚሊየን ዶላር ያላአግባብ ለጅቡቲ ለወደብ ክፍያ እንደምታወጣ ስናስብ ይህን ታይቶ የማይታወቅ እየተባለ የሚነገረውን ድርቅ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ያለምንም የውጭ እርዳታ የአራት አመት የወደብ ወጫችን ብቻ ሊሸፍንልን እንደሚችል ማሰብ ተገቢ ነው።

ይህ ባለመሆኑ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያዊ ህጻናት፣ አዛውንቶችና ሌሎችም ወገኖቻችን ምግብ አጥተው ህይወታቸው እየተቀጠፈ እንደሆነ ስንመለከት ከፍተኛ ብስጭትና መጠን የሌለው ቁጣ ቢሰማን ያለምክንያት አይደለም።

## ተጨማሪ በጀት መመደብ ይቻል ነበር

ያለአግባብ ለወደብ ኪራይ የምንከፍለው ገንዘብ ለእያንዳንዱ የሀገሪቱ ክልል 10 ቢሊየን 350 ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር ተጨማሪ በጀት መመደብ ይቻል ነበር።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት በዘጠኝ የአስተዳደር ክልሎች የተዋቀረች ነች። ይህ የባከነ ገንዘብ ለእያንዳንዱ ክልል እኩል ቢከፋፈል ኖሮ አሁን ባላቸው አመታዊ በጀት ላይ በአመት በአመት ለእያንዳንዱ ክልል ቢያንስ 690 ሺህ ብር በ15 አመት ውስጥ ደግሞ ለእያንዳንዱ ክልል 10 ቢሊየን 350 ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር ተጨማሪ በጀት መመደብ ይቻል ነበር። ይህ ሲሆን ደግሞ በተጨማሪው ገንዘብ ምን ያክል መምህራንን፣ የጤና ባለሙያዎችን፣ የልማት ሰራተኞችንና የእርሻ ባለሙያዎችን መቅጠር እንደሚቻል፣ ምን ያክል የልማት ስራ መስራት እንደሚችል፣ ምን ያክል በየጎዳናው የሚንከራተቱ ህጻናትን፣ እናቶችና አዛውንቶችን ለመታደግ እንደሚያስችል፣ ምን ያክል የድንገተኛ አደጋ መቋቋሚያ ፕሮጋራም ማዘጋጀት እንደሚቻል ..ወዘተ ማገናዘብ አስቸጋሪ አይደለም።

በሀገሪቱ በሚገኙ ከተሞች በርካታ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን በመገንባት የሱስ ተገዢ የሆነውን ወጣት በመታደግ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጤንነቱ የተጠበቀ ትውልድን መፍጠር ይቻል ነበር። እዚሁ ሀገር ቤት የስራ እድሎችን በመፍጠር፣ ስደትን በከፍተኛ ደረጃ መግታትም ይቻል ነበር። ይሔ ደግሞ አንዳንድ አረቦች በወገኖቻችን ላይ የሚጽሙትን አረመኔያዊ ድርጊት ማስቆም የሚያስችል ነው። ምንጊዜም ቢሆን ድህነት ያዋርዳል እንጂ አያስከብርም። በኢኮኖሚያዋ ጠንካራ እና የታፈረች ሀገር ብንገነባ ኖሮ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ዘንድ መዘባበቻ ሆነን አንቀርም ነበር። ከእነዚህ ባሻገር (እንደ አንዳንድ የምጣኔ ሀብት ጠበብት ጥናት ከሆነ፣ የሀገሪቱን አጠቃላይ በጀት ለማሳደግ የሚችል በጀት ለወደብ ኪራይ ክፍያ ውሏል ማለት ይቻላል። ይህ ደግሞ ሀገሪቱን በኢኮኖሚ ደካማ እንድትሆን አድርጓል።

ለምሳሌ ያህል የዘንድሮውን የ2008 (የ2015/2016ቱን) የሀገሪቱን አጠቃላይ በጀት 50% መሸፈን ይቻል ነበር።

ከሀገሪቱ አጠቃላይ በጀት አኳያ ሲታይ ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ትልቁ በጀት እየተባለ የሚጠቀሰው በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2015 የተመደበው 11 ቢሊየን ዶላር ነው። ( www.theeastafrican.co.ke/… ) ይህ ማለት ለ15 አመት በወደብ አልባነታችን የባከነው ገንዘባችን የአገሪቱን ትልቁን በጀት ከ50% በላይ ሊሸፍን በቻለ ነበር ማለት ነው።

የሀገሪቱን ከፍተኛ የካፒታል በጀት

ሙሉ በሙሉ መሸፈን ይቻል ነበር

እንደ ሀገሪቱ የዘመኑ ባለሥልጣኖች አነጋገር ከሆነ ለ2015 (በአውሮፓውያን አቆጣጠር ) ከተመደበው በጀት ውስጥ ለአጠቃላይ ካፒታል ወጪ የተመደበው ገንዘብ ውስጥ 12.1 ቢሊየን ብር ከውጭ በብርድና በእርዳታ የሚገኝ ነው። ለጅቡቲ በ2014 እና በ2015 የተከፈለው የወደብ ክፍያ ብቻ ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር 365፣000x2x21 (አሁን ባለው ምንዛሬ መሰረት) 15 ቢሊየን 330 ሺህ ብር ነው። ማለትም ያለምንም እዳና የውጭ እርዳታ የሁለቱ አመት በወደብ ክፍያ የምንፈልገውን የካፒታል ወጪ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ ከሶስት ቢሊየን ብር በላይ ለሌላ ጉዳይ ሊውል የሚችል ትርፍ ገንዘብ ማስቀመጥ እንችል ነበር ማለት ነው። (http://allafrica.com..)

በዚህ ገንዘብም ምን ያክል አውራ ጎዳና፣ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ የልማትና ምርምር ጣቢያዎች፣ ፋብሪካዎች …ወዘተ መመስረት እንደሚቻል መገናዘብ አይከብድም።

በመላው በሀገሪቱ የአዕምሮ ጤና አገልግሎትን

ሙሉ በሙሉ ማዳረስ ይቻል ነበር

ይህ በየዓመቱ በራሳችን ላይ ያመጣነው ኪሳራ በጤና ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ ለማመዛዘን ደግሞ በከፊል የሚከተለውን እንመልከት፡- ሀገራችን በአዕምሮ ጤና አገልግሎት በኩል እጅግ ኋላ ቀር ከሚባሉት የአለም ክፍሎች የምትመደብ ነች። በዚህ ሙያ የሰለጠኑ የአዕምሮ ጤንነት የህክምና ሌሎችም ባለሙያዎች (ሳይካትሪስቶች) ከመቶ የማይበልጡ ናቸው። በመላ ሀገሪቱ ለዚህ አገልግሎት የተከፈቱ ሆስፒታሎች ከአራት እና አምስት አይበልጡም። በአጠቃላይ የአዕምሮ ጤንነት ችግር የሚደርስባቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ችግር ውስጥ ነው የሚገኙት። በቅርብ የወጣ አንድ ሰፋ ያለ ጥናት እንደሚያሳየው፣ ለዚህ ችግር መሰረታዊ አገልግሎት ለማቅረብ የሚፈለገው በጀት ከፍተኛ ቢሆንም ሀገሪቱ በኢኮኖሚ የደቀቀች በመሆኗ በቂ በጀት መመደብ ተስኗታል። እንደ ጥናት ወረቀቱ ውጤት ከሆነ፤ የወደብ ኪራይ ባይኖርብን ኖሮ የዜጎችን አዕምሮ ጤንነት ማስጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ የአይምሮ ህክምና ተቋማትን መገንባት እንችል ነበር።

ማጠቃለያ

በዓለም ላይ ከ100 ሚሊየን በላይ ህዝብ ተሸክማ፤ እንዲሁም ከባህር በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እየተገኘች የባህር በር (መውጪያና መግቢያ) የተከለከለች ሀገር ብትሆን ምስኪን ኢትዮጵያ ብቻ ናት። በእውነቱ ያንገበግባል! ስለሆነም ኢትዮጵያን ወደብ ኖሯት ወደነበረችበት ስትራቴጂካዊ ስፍራ ለመመለስ ምኞትና ፍላጎት ያለን ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሰለጠነ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ታላቅ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። አሊያ ህልውናችንም አደጋ ላይ መውደቁ የማይቀር መራር እውነት ይሆናል።

አበቃሁ፤ ቸር እንሰንብት!

# የኢትዮጵያ . . . *ከገፅ 3 የዞረ*

መቀየራቸው አይቀርም፡፡ እየገነቡ ማፍረስ፣ እያፈረሱ መገንባት ትልቅ ችግር ነው፡፡ ጠንካራ አገራዊ ተቋማት ከሌሉ፣ በፖለቲከኞችና በሕዝብ መካከል ብቻ ሳይሆን፣ በራሳቸው በፖለቲከኞች መካከልም መተማመን አይቻልም፤ መተማመን ሳይኖር ደግሞ ዴሞክራሲ ብሎ ነገር የለም፡፡ ትልቁ የኢትዮጵያ ችግርም ይኸው ይመስለኛል፡፡ .... ገለልተኛ አገራዊ ተቋማት የሁሉም ነገር መሠረት ነው፡፡›› ሲል በተቋማት ግንባት ግንባታ ችግሮችን ጠቅሶ በተጓዳኝ መፍትሄውን የሚጠቁመው የ‹‹ውይይት›› መጽሄት አዘጋጅ ጋዜጠኛ በሪሁን አዳነ ነው፡፡

## ፖለቲካ የለም!

በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛ ፖለቲካ ስለመኖሩ ከመጠራጠር አልፈው በግልጽ ፖለቲካ አለመኖሩን የሚናገሩ ወገኖች አሉ፡፡ በ2005 ዓ.ም ‹‹ኢትዮጵያን ማን ይታደጋት?›› በሚለው ርዕስ በአቤል ዓለማየሁና በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በጋራ ተዘጋጅቶ ለንባብ በበቃው መጽሐፍ ውስጥ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም የኢትዮጵን ፖለቲካ አስመልክቶ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹እኛ እና ኢትዮጵያን በሚመስሉ አገሮች ውስጥ ፖለቲካ የለም፡፡ አገዛዝ ባለበት ፖለቲካ የለም፡፡ ፖለቲካ ማለት ለሥልጣን የሚደረግ ትግል፣ ውድድርና ፉክክር ነው፡፡ በአምባገነንነት በሚገዙ አገራት ዘንድ ይሄ የለም፡፡››

በ‹‹አዲስ ገጽ›› የመጀመሪያ ዕትም ላይ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ቃለ-ምልልስ ያደረግንለት ጠበቃ ተማም አባቡልጉ በበኩሉ፤ ከፕሮፌሰር መስፍን ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሀሳቡን በመሰንዘር ‹‹ ...ዜጎች ነጻ ባልሆኑበትና የሕግ የበላይነት በሌለበት ሀገር ውስጥ ፖለቲካ ይኖራል ብዬ ስለማላምን እንደዜጋ ፖለቲካ በሌለበት ፖለቲከኛ መሆን ተገቢ ነው ብዬ አላምንም፡፡ የሕዝብን መብቶችና ነጻነቶችን በሕግና በተግባር በማዋቀር ደረጃ መረጃ ማረጋገጥ ማስቻልን ሁሉም ዜጋ ሊሰራው የሚገባው ብቸኛውና ተቀዳሚው ተግባሩ መሆን ይኖርበታል እላለሁ›› ብሎ ነበር፡፡

እንግዲህ ፖለቲካ የሌለበት በሚባልበት ሀገር ውስጥ መኖር በራሱ ህይወት ለብዙሃን ዜጎቿ በጣም አስቸጋሪ መሆኗ አሻሚ አይሆንም፡፡

*ከቃል ያልዘለለው መድበለ-ፓርቲ ሥርዓት*

በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ቦርድ ህጋዊ ፍቃድ ኖሯቸው እጅግ ፈታኝ በሆኑ ውጣ ውረዶች ውስጥ ታግለው መንቀሳቀሳቸውም ይታወቃል፡፡ ግን እንደነጻ ፕሬሱ ሁሉ ለመጥፊያ ጊዜያቸው ዋረነት ሲቆረጥባቸው በተለያዩ ሴራዎች በአገዛዙ እንዲከስሙ ይደረጋል፡፡ በአንድ ወቅት የሲቪክ ማኅበራት በጥቂቱም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ፡፡ እነኚህ ሲቪል ማኅበራት በኅብረተሰቡ ዘንድ መጠነኛ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናን መፍጠር መቻላቸው በተግባር ስለታየ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ መክሰም እጣ-ፈንታቸው ሆነ፡፡

መድበለ-ፓርቲ ሥርዓት በስም እንጂ በተግባር ላለመኖሩ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በባለፈው ዓመት አምስተኛው ሀገራዊ ብሔራዊ ምርጫና በተገኘው ‹ውጤት› ነው፡፡ ከዚያ ቀደም በነበረው ፓርላማ ቢያንስ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የፓርላማ ውክልና አግኝቶ ነበር - በአቶ ግርማ ሰይፉ አማካኝነት፡፡ ይህም በፓርላማ ውሳኔዎች ላይ ምንም የሚያመጣው ተጽዕኖ ባይኖርም ከኢህዴግ ውጪ የተለየ ሀሳብ ይነሳበት ስለነበር፡፡ ዘንድሮ ግን ሁሉንም የፓርላማ ወንበሮች ገዥው ሀይል ጠቅልሎ በመውሰድ አንድ ነጠላ ዜማን ብቻ መስማትንና ማሰማትን መረጠ፡፡ ይህ የትምክህትና የማን አለብኝነት ድምር ውጤት ነው፡፡ ‹‹ከእኔ ውጪ ለዚህች ሀገር ተቆርቋሪ የለም››፣ ‹‹እኔ ከሌለው ይህቺ ሀገር ብትንትኗ ይወጣል››፣ ‹‹ታግዬ ሥልጣን ስለያስኩ እንደፈለኩ ብሆንስ ማን ከልካይ አለኝ››፣ ‹‹ሁሉንም ጠቅልዬ የመያዝ አቅሜን ተመልከቱ›› ...የሚል ግልባጭ መልስ ይሰጠናል፡፡

ከዚህ እውነታ በኂላ፣ በዘንድሮው አመት ውጥንቅጡ የወጣ ነገር ሀገሪቷና ህዝቦቿ ያስተናገድነውና እያስተናገድን የምንገኘው፡፡ ‹‹በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ክልል ልዩ ዞኖች ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር ይካለሉ የሚለው የህወሃት/ኢህአዴግ ዕቅድ ተግባራዊ አይሆንም›› በሚል ለተራዘም ወራት በኦሮሚያ ክልል ህዝባዊ እምቢተኝነት በተግባር ተነስቶ እስከ 300 ንጹሃን ዜጎች በላይ ለሞት፣ በርካቶች ለአካል ጉዳት፣ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ደግሞ ዜጎች ለእስር ተዳርገዋል፤ የንብረት ውድመትም ተከስቷል፡፡ ይህ ችግር ቂም በቀልን አርግዞ ተዳፈነ እንጂ ሰላማዊ ዕልባት አላገኘም፡፡ ላለፉት 50 አመታት በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅ ድርቅና ረሃብ መግባቱ፣ ከ15 ሚለየን ሕዝብ ላይ ለረሃብ መጋለጡንና በረሃብ የተነሳ የሞቱ ወገኖቻችንን እንዳሉም አይረሳም፤ ችግሩ ዛሬም ድረስ እልባት አላገኘም፡፡ በአዲስ አበባ የአዲሱ የትራፊክ አዋጅን በመቃወም ለቀናቶች የታክሲዎች አድማ ተደርጎም ነበር፡፡ በመቀሌም የባጃጅ አሽከርካሪዎች አዲስ የስምሪት መመሪያን በመቃወም ለቀናቶች አድማ አድርገው ነበር፡፡ በዚሁ በትግራይ ክልል ሌሎች የተቃውሞ ድምጾችም ነበሩ፣ አሁንም አሉ፡፡ በደቡብ ክልል በአርባ ምንጭም በቅርቡ ችግር መከሰቱን ሰምተናል፡፡ በአማራ ቅማንትና ወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ተነስቶ ችግሩ ዛሬም ድረስ አለመረጋጋት አስፍኖ ይገኛል፡፡

ወ/ሪት ሶልያና ሽመልስ የዞን ፱ ጦማሪ እና የሰብዓዊ መብት አቀንቃኝ ኢ-መደበኛ የጦማሪዎች ስብስብ መሥራች አባል በ‹‹አዲስ ገጽ›› 11ኛ ዕትም ላይ በሰጠችው ቃለ-ምልልስ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘንድሮ እየተካሄደ ስላለው የመብት እንቅስቃሴ እንዲህ ብላ ነበር፡- ‹‹ጭቆና እስካለ ድረስ የመብት ጥያቄዎች መልካቸውን እየቀያየሩ መምጣታቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህ መገመት የምችለው አካሄድ መንግሥት እንደሚያስመስለው የሚቆም ነገር እንደማይኖር ብቻ ነው››

በጋምቤላ ክልል የሚኖሩ በርካታ ንጹሃን የኑዌር ጎሳ አባላት በደቡብ ሱዳን አማጽያን በአንድ ሌሊት ህይወታቸው ሲቀጠፍ፣ ሀብት ንብረቶቻቸው ሲዘረፍና ህጻናት ልጆቻቸው ታፍነው ሲወሰዱ በሀገድ ታይቷል፡፡ ዛሬ ላይ ጎረቤት ሀገራት፣ ድንበር ተሻግረው ኢትዮጵያውያንን እንዳሻቸው የማድረግ ድፍረት ላይ ደርሰዋል፡፡

‹‹ለስኳር ፕሮጀክት የተመደበ 77 ቢሊየን ዶላር ጠፋ››፣ ‹‹88 ኮንዶሚኒየም ቤቶች ጠፉ››፣ ‹‹በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የ10 መኪኖች ሊብሬ እንጂ መኪኖቹ የሉም›› ...የሚሉ እጅግ ነውረኛና አሳፋሪ ተግባራት በዛሬዋ ኢትዮጵያ ተደጋግመው እየታዩ ይገኛሉ፡፡

ይህም ብቻ አይደለም፣ ተደርጎ በማይታወቅ መልኩ የማትሪክ ፈተና ከፈተናው ቀን በፊት ቀድሞ በመውጣቱ የተነሳ የፈተናው ቀን ለሁለተኛ ጊዜ እንዲራዘም መገደዱን አይተናል፡፡ ይህ ሀገሪቷ የደረሰችበትን ዝብርቅርቆሽ አንዱ አመላካች አድርጎ ማየት ይቻላል፡፡

የሰሞኑ አጀንዳ ደግሞ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በጾረና ግንባር ውግያ ጀመረች መባሉ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየቱን የሰጠው ጋዜጠኛ ኃለመስለቀል በሸዋምየለህ እንዲህ በማለት ነበር፡-

‹‹ግጭቱን የቀሰቀሱት ህወሃቶች ለግጭቱ መልስ የሰጠው ደግሞ ኢሳያስ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ህግዴፍ ጦርነት የሚጀምርበት ምክንያት የለም፡፡ በአልጀርሱ ስምምነት ብዙው የባድመ መሬት ለኤርትራ መወሰኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን ውሳኔ እየደገፍኩ አይደለም፡፡ ይህንን ስምምነት በመጣስ ህወሃት በሀይል እርምጃ ለማስመለስ ከተንቀሳቀሰ ህግዴፍ ዳግም ጦርነት ውስጥ ሊገባ ይችል ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡ ህወሃት ግን ጦርነት ውስጥ ለመግባት ፍላጎቱም አቅሙም ያለው አይመስለኝም፡፡ ከገባ ግን የሚገባው በሁለት ምክንያቶች ይሆናል፡፡ አንደኛው፣ ታጥቀው በኤርትራ የሚገኙ የኢትዮጵያ ጠንካራ ተቃዋሚዎችን ለመምታትና ሀይል ለማዳከም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የኤርትራ ተቃዋሚዎችን ከአዲስ አበባ ቡና ቤቶች ውስጥ ሰብስቦ በኢሳያስ አፈወርቂ ቦታ ለመተካት ያለመ ይሆናል፡፡ በ1991 ዓ.ም የሉዓላዊነት ጥያቄ በሚል ከ80 ሺኅ በላይ ዜጎቻችን በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሞተዋል፡፡ አሁን ግን ህዝቡ ነቅቷል፡፡ አገዛዙ አሁንም የሉዓላዊነት ጉዳይ በሚል በማጭበርበር መዋጋት አይችልም፡፡ በፕሮፖጋንዳ ተታልሎ ለእነሱ ሄዶ የሚማገድ ወጣት አይኖርም››

የኢትዮጵያ ፖለቲካ አካሄድ መታየት ያለበት ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከማኅበራዊ ... ወዘተ ፋይዳዎች አንጻር መሆኑን የሚስገነዝቡት የቀድሞ የፓርላማ ተወካይና የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ም/ሊቀመንበር አቶ ግርማ ሰይፉ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ ከፖለቲካ ትኩሳቱ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ፖለቲካው ካልተረጋጋ ኢኮኖሚውም ሆነ ማኅበራዊ ፖለቲካውን ማስተካከል አይቻልም ይላሉ፡፡

አቶ ግርማ አያይዘውም ‹‹ገዥው ኃይል ፖለቲካውን ብልህነት ያስፈልገዋል፡፡ ሠጥቶ መቀበል አለብኝ ብሎ ስለማያምን ከዚህ በኂላ ለመስጠት ማሰብ አለበት፡፡ እንደምርጫ ቦርድ አይነት ተቋሞችን ማስወገድ አለበት፡፡ እንዲያ መሆን ከተቻለ በምርጫ ፖለቲካ ተስፋ ያላቸው የፖለቲካ ጨዋታ መጫወት ይችላሉ፡፡ አሊያ የፖለቲካ ጨዋታው ከአድርባዮችና ሆዳሞች ጋር ከሆነ ብዙ ዋጋ ያስከፍለናል፡፡ ኢህአዴግ ‹100 ፐርሰንት የፓርላማ ወንበር አይገኝም፡፡ ይህ እንደማይገባኝ አሁን አውቂያለሁ፡፡ ያንን የማካፍለው ሀይል መምጣት አለበት› ብሎ ለራሱ መናገርና ይህንንም በተግባር መተግበር አለበት፡፡ አሁን ያለው ፖለቲካ ግን ጥሩ አይደለም፡፡ በተለያየ መስክ ጉልበት ይበዛዋል፡፡ በግሌ ፖለቲካው ወደየት እየሄደ ስለመሆኑ ለመናገር ይከብደኛል፡፡›› ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

እንግዲህ በዛሬዋ ኢትዮጵያ በየቀናቱ፣ በየሳምንቱና በየወራቱ አዳዲስ፣ ከባድና አደገኛ ክስተቶች ቅርጻቸውንና መልካቸውን እየቀያየሩ መከናወናቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይህ ወደየት እንደሚወስደን ማወቅ አዳጋች ነው፡፡ ይህ በያዝነው ዓመት እንኳን ሳያልቅ ምን አይነት ከባድ ሀገራዊ ጉዳይ እንደሚከሰት የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ህወሃት/ኢህአዴግ ‹‹ኢትዮጵያን ከመበታተን አደጋ አዳንኳት›› እያለ ቢመጻደቅም አሁን እየተከተለ ባለው ግትር አቋም የተነሳ ‹ኢትዮጵያን አደገኛ ወደሆነ የመበታተን አደጋ ውስጥ እንዳይከትታት ግን ስጋት አለን፡፡

ዮሴፍ ሙሉጌታ ባባ (ዶ/ር)
(kankokunmalimaali@gmail.com)



# የድኅረ - ቅኝ - ግዛት አፍሪካ አሰቃቂ ሁኔታና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ!

## ክፍል 8

ከዚህ በፊት በግልፅ ለማሳየት እንደ ሞከርኩት፣ አውሮፓውያን እና ከቆዳ ቀለማቸው በስተቀር በእነርሱ አምሳያ የተቀረጹት አውሮ-አፍሪካውያን ሎሌዎቻቸው፣ ነጮች ‹‹ጨለማ አህጉር›› ለነበረች አፍሪካ ‹‹ሥልጣኔ›› እንዳመጡ ሊያሳምኑን ይሞክራሉ፡፡ ‹‹አውሮፓውያን ወደ አፍሪካ ባይሄዱ ኖሮ፣ አፍሪካውያን እስከ ዛሬ ድረስ ጨለማ አህጉር ውስጥ ይኖሩ ነበር›› በማለት የሚተርቱም አልጠፉም፡፡ ለዚህ ነው አሠራራቸውና አመለካከታቸው የምዕራባውያን ግልባጭ የሆነው አውሮ-አፍሪካውያን፣ የቅኝ-ግዛት በጐ ጎንን ማየት የሚሹት፡፡ የዘመኑ (contemporary) ወጣት ደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም በቅርቡ ይህንን ጉዳይ የታዘበው እንዲህ በማለት ነበር፡- ‹‹የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ፖሊሲ ከሥልጣኔ፣ ያገራችንን የኑሮ ዘይቤ ደግሞ ከገልቱነት ጋር አቆራኝቶ የማሰብ ዝንባሌ የሚመነጨው ከሊቃውንቱ የግል ገጠመኝ ይመስለኛል፡፡ እኒህ ሊቃውንት በፈረንጅ አሳዳጊዎች ቤት በፍቅርና በክብር ያደጉ በመሆናቸው ቅኝ ግዛትን ሲያስቡ ወደ አእምሯቸው የሚመጣው፣ ‹‹የደስታ ገነት›› ቢሆን አይደንቅም፡፡ ቅኝ-ገዥውን የጉዲፈቻ አባታቸው አምሳያ አድርገው ስለሚያስቡት ነው መሰል ክፉ ገጽታውን ለመልከት [sic] አይደፍሩም፡፡” (በዕውቀቱ ሥዩም፣ ከአሜን ባሻገር፤ 2008 ዓ.ም፤ ገጽ-122) የወረደ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው አውሮ-አፍሪካውያን ግን፣ የድኅረ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ የማንነት ቀውስና የዚህ ውጤት የሆነው የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ድቀት ‹‹አፍሪካን የማሠልጠን ተልእኮ›› (civilizing mission) የሚለው የነጮች አስተሳሰብ መሆኑ በቅጡ ያልተረዱት፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፣ አውሮፓውያን ወደ አፍሪካ አህጉር ይዘው የመጡት ‹‹ሥልጣኔ››ን ሳይሆን ‹‹ውድመት››ን ነው፡፡ ይህ ማለት “ቅድመ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ (pre-colonial Africa) ፈጽሞ ምድረ-ገነት ነበረች” ለማለት አይደለም፡፡ ጦርነትና ግጭት የሰው ልጅ ታሪክ ነባራዊ ክስተት እስከ ሆነ ድረስ፣ አፍሪካውያን ከተጠቀሰው ዓይነት ክስተት ተነጥለው የሚፈረጁበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ የማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕዝብ ታሪክ መልካም እና መጥፎ ገጽታ አለው፡፡ ስለዚህ፣ የሰው ልጅ ታሪክን አንድም ፍጹም ቅዱስ፣ አለበለዚያም ፍጹም እርኩስ አድርጎ ማቅረብ ‹‹የአስተሳሰብ ሽርሙጥና›› ይባላል፡፡ ፍልስፍና ለእንደዚህ ዓይነቱ የእብደት ድምዳሜ ፈጽሞ ቦታ የለውም፡፡ ለማንኛውም እዚህ ቦታ ላይ ሊተኮርበት የሚገባው፤ አውሮፓውያን፣ አፍሪካውያን ላይ ያደረሱት ውድመት፣ ‹‹አፍሪካን የማሠልጠን ተልእኮ›› ከሚለው ፅንሰ-ሐሳብና ከድኅረ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ ፖለቲካዊ ቀውስ ጋራ እንዴት እንደ ተቆራኘ ነው፡፡

በቅድመ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ ዘመን፣ የአፍሪካ ሕዝቦች በሒደት የቀረጿቸው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያ፣ ቴክኒካዊ እና ባህላዊ ሥርዓቶች ነበሯቸው፡፡ አውሮፓውያን እነዛን ሀገር-በቀል ሥርዓቶች በሚገባ ማጥናት ሲገባቸው፣ ከእነርሱ ታሪክና ባሕል (አሠራር) ጋራ ተመሳሳይ ወይም አንድ ወጥ ሆኖ ስላላገኙት ብቻ፣ “ኋላ-ቀር” (traditional) የሚል ተቀጥላ አበጁለት፡፡ እነዚህን ባህላዊ ሥርዓቶች የሚከተሉትን አፍሪካውያን ደግሞ “ያልሠለጠኑ ሕዝቦች” (uncivilized society) በማለት ፈረጇቸው፡፡ በተቃራኒው፣ የአውሮፓ ባሕልና-ታሪክ እንደ “ዘመናዊ” (modern)፣ አውሮፓውያን ደግሞ “የሠለጠኑ ሕዝቦች” (civilized people) ተደርጎ ተስሏል፡፡

በጊዜ ሒደት፣ አብዛኞቹ አፍሪካውያን በእንግዳ ባሕል ተጽእኖ ሥር ወደቁ፡፡ የራሳቸውን ሥርዓት እና “ታሪክ” በመተው፣ የምዕራቡን ዓለም ሥርዓትና “ታሪክ” መከተልና መተግበር ጀመሩ፡፡ አውሮፓውያን ጠበብት፣ ስለ አፍሪካ እና አፍሪካውያን የተረቱትን ተረታ-ተረት ያለ ምንም ጥልቅ አተያይና ብያኔ (critical judgment) ተቀበሉ፡፡ እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ “ዘመናዊ” ወይም “ሥልጣኔ” በሚል ስም፣ በአፍሪካውያን ላይ የሚካሄደው የለየለት “የአእምሮ አጠባ” (brain washing) እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ይህም ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት አፍሪካውያንን በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ጥገኛ አድርገው ለመግዛት ካላቸው ፍላጎት ነው፡፡

“አፍሪካን የማሠልጠን ተልእኮ” የሚለው ተረት፣ በ19ኛው ክ/ዘመን በአውሮፓ ውስጥ እያቆጠቆጠ ከነበረው ካፒታሊዝም ጋራ በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ አፍሪካ እንደ ቅርጫ ሥጋ እንድትቀረማመት ምክንያት የሆነው የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት መሆኑ በጣም ግልጽ ነው፡፡ ርካሽ የሰው ጉልበት እና የጥሬ-ዕቃ አቅርቦት፣ ቅኝ-ግዛታቸው ሥርዓት በአፍሪካ እንዲዘረጋ ምክንያት ሆኗል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ለቅኝ ግዛት መፈጠር ዋነኛ ምክንያት የኢኮኖሚ ጥቅም ነበር፡፡ ይህ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ በቀጥታ ግቡን እንዲመታ ደግሞ፣ አውሮፓውያን ዓይናቸውን በጨው ታጥበው “ኋላ-ቀር” እና “ዘመናዊ” በሚል ስም በራሳቸው እና በ“ሌላ”ው (አፍሪካዊ) መካከል “ድብ-አካላዊ” ልዩነት (ontological difference) ፈጠሩ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ፣ አውሮ-አፍሪካውያን ኤሊቶች ራሳቸውንም ሆነ “ሌላ”ውን (አውሮፓዊውን) የሚገነዘቡት ከዚህ ፅንሰ-ሐሳብ አንፃር በመሆኑ፣ ድኅረ-ቅኝ ግዛት አፍሪካ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ካባን እንድትደርብ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ወዲህ፣ አፍሪካውያን የተቀዳጁት ፖለቲካዊ ነጻነት የይስሙላ እንጂ እውነተኛ የኢኮኖሚ ነጻነት አላስገኘላቸውም፡፡ ከቅኝ-ግዛት ዘመን በባሰ መልኩ፣ በድኅረ-ቅኝ ግዛት አፍሪካ ለከፍተኛ የኢኮኖሚ ብዝበዛ ተዳርገዋል፡፡ የፖለቲካ ነጻነት ሊኖር የሚችለው፣ እውነተኛ የኢኮኖሚ ነጻፃነት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በአፍሪካ፣ የአሻንጉሊት መንግሥታትን ሕልውና የሚያስጠብቁ አውሮፓውያን፣ አውሮ-አፍሪካውያንን እንደ እንስሳ በማሠልጠን ነው፡፡ እንደ እንስሳ ያሠለጠኑት ግለሰብ፣ ውሎ አድሮ ወደ “ዕቃነት” ይቀየራል፡፡ ምዕራባውያን፣ በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ላይ የሚያሳድሩት ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ፣ በቀላሉ ግቡን የሚመታው በእነዚህ ወሮበላ ግለሰቦች ሲሆን፣ በድኅረ-ቅኝ ግዛት አፍሪካ፣ ለሕዝብ ትክክለኛ ዕድገት አውሮ-አፍሪካውያን የሥጋት ምንጭ የሚሆኑት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ከሁሉ በላይ፣ የቅድመ-ቅኝ-ግዛት (pre-colonial) እና የቅኝ-ግዛት (colonial) ቅሪቶች “ውህድ” ያስከተለው ግራ መጋባት (misunderstanding)፣ በድኅረ-ቅኝ-ግዛት-አፍሪካ የእጅ አዙር ቅኝ-አገዛዝ እንዲዘረጋ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በአንድ በኩል፣ በቅድመ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ የነበሩ ባህላዊ ሥርዓቶች፣ በዘመኑ አፍሪካ (contemporary Africa) ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አሠራር/መዋቅር ውስጥ በትክክል እንዲሰርጽ አልተደረገም፡፡ ለረዥም ዘመናት የምዕራባውያንን ጠበብት አስተሳሰብ ተከትለው፣ የአፍሪካን ሕዝብ እምነት፣ ባህል እና ታሪክ እንደ “ኋላ-ቀር” መቁጠር እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡- የበታችነት ባሕርይ የተጠናወታቸው አውሮ-አፍሪካውያን ኤሊቶች፣ ነጮች የወደዱትን ነገር የመውደድ፣ የጠሉትን ነገር ደግሞ የመጥላት አባዜ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ነው፣ ምዕራባውያን “አሠልጣኞቻቸው” እስኪነግሯቸው ድረስ፣ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው የማያውቁት! በሌላ አገላለጽ፣ አውሮ-አፍሪካውያን አፍሪካን የማሠልጠን ተልእኮ ከሚለው የአውሮፓውያን ዘረኛ አስተሳሰብ ፈጽሞ ነጻ ሊወጡ አልቻሉም፡፡ ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ የአውሮፓውያንን ቅኝ-ግዛት ሕጋዊ ማድረግ ነው፤ “ቅኝ-ግዛት” እና “አፍሪካን የማሠልጠን ተልዕኮ” የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸውና፡፡ “It has been said that our civilizing mission alone can justify our occupation of the lands of uncivilized peoples.” (Placide Temples, 1969, pp. 171-172)

ይህንን አውነታ ወደ ጐን በመተው፣ ከአፍሪካ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፈጽሞ የማይገናኘውን የምዕራቡን ዓለም የዕድገት ፖሊሲ መከተል፣ የእጅ አዙር ቅኝ-አገዛዝን ከማስፈን ውጭ ለአፍሪካ አህጉር የሚያስገኘው ምንም ዓይነት ኢኪኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ የለውም፡፡ በቅኝ-ግዛት ምክንያት በአፍሪካ “ባህላዊ” ሥርዓቶች ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ፣ በቅኝ-ግዛት አፍሪካ ግራ-መጋባትን ያስከተለ ቢሆንም፣ አውሮ-አፍሪካውያን የማንነት ቀውስ ውስጥ የገቡት፣ ለአፍሪካ “ባሕላዊ” ሥርዓቶች ባላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ነው፡፡ የድኅረ-ቅኝ-ግዛት አፍሪካ አሰቃቂ ሁኔታ፣ ከዚህ ግራ-መጋባት ጋራ የተቆራኘ ነው ስንል፣ ይህንኑን ተጨባጭ ሁኔታ ለማሳየት ነው፡፡

ወደ ገፅ 29 ዞሯል

## ቃለ–ምልልስ



<<እስከ ዛሬ ሥልጣን ስለ ምናሸጋግርበት መንገድ አልሠራንም>>
አቶ የሺዋስ አሰፋ



<<የኢሕአዴግ ትልቁ ስሕተት አንድነትን ማፍረሱ ነው>>
አቶ ሀብታሙ አያሌው



<<ኢሕአዴግ የብጥብጥ መንገድን ትቶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚታረቅበትን መንገድ ማሰብ አለበት>>
አቶ ዳንኤል ሺበሺ

**የ<<አዲስ ገጽ>> 12ኛ ዕትም እንግዶች የነበሩት የቀድሞ የአንድነት ፓርቲ አመራሮችና በሽብር ወንጀል ተከስሰው ከታሰሩ በኋላ በቅርቡ ከእስር ተፈትተው የፍርድ ቤት ጉዳቸውን ውጪ ሆነው በመከታታል ላይ የሚገኙት አቶ ሃብታሙ አያሌው እና ዳንኤል ሺበሺ፣ እንዲሁም በተመሳሳይ መንገድ ታስሮ የተፈታው የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አቶ የሺዋስ አሰፋ መሆናቸው ይታወሳል፡፡ ሶስቱም ፖለቲከኞች ከኤልያስ ገብሩ ጋር አድርገውት የነበረውን ቃለ-ምልልስ የመጨረሻ ክፍል እንዲህ አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡-**

**በተቃውሞ ፓርቲ ውስጥስ ያለው ድክመት?**

የሺዋስ፡- አብዛኛው ችግር የራሳችን ነው፡፡ ብዙው ፐርሰንት የራሳችን ችግርና ራስ ወዳድነት ነው የሚያፈርሰን ብዬ አስባለሁ፡፡ የኢህአዴግ እጅ የለበትም ግን አልልህም፡፡ ቢኖርበትም አይገርምም፡፡ እኛ ልንቀይረው ስንሄድ እሱ ደግሞ ቦታው ላይ ለመቆየት ቢታገል የሚጠበቅ ነው፡፡ ዴሞክራሲ ምን እንደሆነና ተቻችሎ መስራት ምን እንደሆነ ያልገባው፤ በደንብና ፕሮግራም ልዩነት ስለሌለ አብረን ተዋህደን እንሰራለን የሚል ነገር የሌለው፤ የመጣበትን መንገድ ለመሄጃ መንገድ የሚያደርግ ስብስብ በተቃውሞ ውስጥ አለ፡፡

‹‹ትጥቅ ትግል አያዋጣም›› ብለኻል ይሉኛል፡፡ ‹‹ትጥቅ ትግል አያዋጣም›› ብል በመጀመሪያ የሚስቅብኝ ሕወሓት ነው፡፡ አዋጥቶትማ እዚህ ደርሷል፤ ግን አይጠቅምም፡፡ እንደ ሀገር አይጠቅመንም፡፡ ዘመኑ አልፎበታል፡፡ ጫማ ነው የምትለውጠው፡፡ ጥልፍልፍ የበረባሶ ጫማን በከስክስ ጫማ ለውጦ ሊረግጠን ይቀየራል እንጂ፤ ዴሞክራሲን አያመጣም፡፡ ‹‹ትጥቅ ትግል አያዋጣም›› አያዋጣም አላልኩም፤ ያዋጣል፡፡ ተባድነህ ብትለው ትቀይረዋለህ፤ ብዙም ጊዜ ላይወስድብህ ይችል ይሆናል፡፡ ግን የስርዓት ለውጥ አያመጣም፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚጠቅመው ሠላማዊ ትግል ብቻ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ለዚያ ደግሞ በቅድሚያ የሚሠሩ ስራዎች አሉ፡፡ መነጋገርና መግባባት ያስፈልጋል፡፡ ‹‹ኤልያስ ነጻ ሳይወጣ እኔ ነጻ አልወጣም›› ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ለትግል ጓደኛህ ቀድመህ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ ለሚደርስበት ነገር አንተ ቀድመህ ስታደርግ የቀረውም ሰው ይመጣል፡፡ የአንተ እንቅስቃሴ የሌላውንም ስሜት ይቀይረዋል፡፡

ራስህን መጀመሪያ ማስተካከል፣ ማዳመጥ፣ የራስህን ግለኝነት ማሸነፍ ያስፈልጋል፡፡ ሁሌ ሌላው ላይ ከማላከክ ወጥተን ወደራሳችን መመለስ ይኖርብናል፡፡ መንግስትም ሌላው ላይ ነው የሚያላክከው፡፡

ዘንድሮ በተከሰተው ድርቅና ረሃብ፣ ቢጠፋ ቢጠፋ ኤሊኖ ሰበብ ሆኗል፤ ጸረ-ሰላም ሀይሎች ሳይባል፡፡ ቀደም ብሎ ጎተራ ተዘጋጅቶ እህል ቢቀመጥ ኖሮ ሰው አይራብም ነበር፡፡ ኃላፊነት ቢሰማህ እኮ ሥልጣን ትለቅቃለህ፡፡ አምስት ሰው የተራበበት ሰው ‹‹እንዴት ይሄንን አላሰብኩም?›› ብሎ ስልጣን ይለቅቃል፡፡ ወደራሳችን ማየት አለብን፡፡ ብዙ ማስተካከልና ማረም ያሉብን ነገሮች አሉ፡፡

**<<የግንቦት 20 ፍሬ መራራ ነው>> ብለኻል። የተቃውሞ ፓርቲ ትግልም በውጣ ወረድ የታጀበ ነው። ሐሳብን በነጻነት የመግለፅ መብት ራሱ በገደል አፋፍ ላይ ነው የሚገኘው። ለሀገርና ለህዝብ የሚጣፍጥ ፍሬ ለማፍራት ምን መደረግ አለበት?**

ኤልያስ፤ ችግሮቻችን አንድ አይነት ናቸው፡፡ ከቴዎድሮስ ጊዜ እንኳ ብንነሣ ወንድሞቹን አፈር ድሜ አስበልቶ ነው ስልጣን ላይ የወጣው፡፡ ከዚያ ተክለጊዮርጊስ፣ ከዚያ አፄ ዮሐንስ በመሳሪያ ብዛት ድራሹን አስግብተው አፄ ዮሐንስን የሱዳን መሃዲስቶች ቢገድሏቸውም፤ ሌሎቹን እነሚኒሊክ እንደ ነገሩ አድርገው ወደ ስልጣን መጡ፡፡ ኃይለስላሴም ኢያሱን ከነአባቱ አጥፍተው፣ ደርግም አፄውን ገድሎ፣ ወያኔም የባሰ ሆኖ መጣ፡፡

ሥልጣን የምናሸጋግርበትን መንገድ እስከ ዛሬ አልሠራነውም፤ የለንም፡፡ አሁን ደግሞ ቆንጨራ የያዘ ይመጣና ያንን ጥሎ ወንበር ላይ ቁጭ ይላል፡፡ እንደ ሀገር በመጀመሪያ መስራት ያለብን ሥልጣንን በሰላማዊ መንገድ የምናሸጋግርበት መንገድ ማበጀት ነው፡፡ ሥልጣን መገራት አለበት፡፡ ሥልጣን መገልገያ መሳሪያ ነው እንጂ ማጥቂያ መሆን የለበትም፡፡ ሥልጣን ላይ እንደ ምንም ከተወጣ በኋላ ሀገርንና ህዝብን የሚያጠፉበት ደረጃ ላይ መድረስ የለበትም፡፡ ለምሳሌ፣ ጃንሆይ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲ የሚያሸጋግሩበት ጥሩ እድሎች ነበራቸው፣ አጠፉት፡፡ መንግስቱም ከ10ኛው የአብዮት በዓል በኋላ ጥሩ እድል ነበረው፡፡ መለስ ዜናዊ ከሆነ ጊዜ በኋላ እሱ ብቻ ሆነ ስልጣኑ ላይ፡፡ ብዙ ነገር ቀይሮ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲ ማሸጋገር ይችል ነበር፤ አላደረገውም፡፡ ቀጣይስ ይሄንን እንደ ዱላ ነው የምንቀባበለው? እዚህ ላይ "ኢትዮጵያን እወዳለሁ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ አገለግላለሁ" የሚል ሰው ማሰብ አለበት፡፡ ስልጣንን መግራት ይጠበቅበታል፡፡

**ሥልጣን እንዴት ይገራ?**

ቂሊንጦ እስር ቤት እያለሁ አንድ መጽሐፍ አንብቤያለሁ፤ "Why Nations Fail?" የሚል፡፡ የመጀመሪያው ሀገርን በትክክል ለማስተዳደር ተቋም እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በጣም ያሳቀኝ፣ ዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሔር የሚባል የምርጫ ቦርድ ኃላፊ ስራ ሲያልቅ ወደ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነርነት ሄደ፡፡ ምን ማለት ነው? ሰው ነው የሚመራው እንጂ ተቋሙ የለም ማለት ነው፡፡ የምርጫ ቦርድ የሚባል ስራ የለም፡፡ ሰውየው ግን ይፈለጋልና ወደዚያው ሄደ፡፡ በቀጣይ የእርዳታ ማስተባበሪያ ወደሚባለውም ይሄዳል ማለት ነው፡፡ የውጭ ሀገር ዲፕሎማት ሲባል ደግሞ ወደዚያ ያመራል፡፡ አሁን ሰው ነው የሚመራን፡፡ ሰውን በሕግ ካልገደብከው እንዳለው መረጃ እንደ ፈለገው ይሄዳል፡፡

ስልጣንን ለመግራት ተቋም መስራት አለብህ፡፡ ተቋምን መስራት፣ ማክበር ያስፈልጋል፡፡ የስልጣን ሽግግርን መዘርጋት፡፡ ምርጫ ጥሩ ነው፣ ምንም ዱላ ሳይኖር ሀብታሙ እና እኔ ተወዳድረን ‹‹እሱ ነው የተሻለው›› ከተባለ እሱ ይቀጥላል፡፡ ‹‹አንተ ነህ የተሻልከው›› ከተባልኩ እኔ እቀጥላለሁ፡፡ በዚህ መንገድ መሞት የለም፤ የሀብት መውደም የለም፣ እንዲህ የሚሆነው በእኔ መቃብር ላይ ነው ከሚልህ ጋር ምን ታደርጋለህ? ብሶት የወለደው ነው ከማለት በስተቀር፡፡

**ኢሕአዴግ በ25 ዓመት ውስጥ ለሀገርና ሕዝብ መሠረት የሆኑ ተቋማትን አልገነባምና ከእርሱ ምን ይጠበቃል? ይሄን እውን ማድረግ ስላልቻለ፤ አዲስ ሥርዓት አያስፈልግም?**

ከላይ እንደገለጽኩት፤ ሰው/ድርጅት የሌለውን አይሰጥም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቋማት እንዲፈጠሩ የሚሠራ ፓርቲ ካለ የራሱን ተቋም በቅድሚያ መገንባት አለበት፡፡ በኢህአዴግ በኩል ሁሉንም ራሳቸው ነው ጠቅልለው የያዙት፡፡ በተፎካካሪ ፓርቲ ውስጥም ‹‹እርሱ ከሌለ›› ሀገር እንደምትናድ አድርጎ የሚቆጠርበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ ውስጡ ተቋሙን የሚያከብር ድርጅት ያስፈልጋል፡፡ ድርጅት እንዲፈጠር ደግሞ መጀመሪያ አስተሳሰብን መለወጥ አለበት፡፡ ‹‹እኔ ጋር ጉድለት አለ›› ብሎ ራስን ማየት ያስፈልጋል፡፡

**በተነሱት ሐሳቦች ላይ እንደ አጠቃላይ መፍትሔ የምትለው?**

ሥልጣን ስትይዝ ይበልጥ ኃላፊነት ይኖርኻል፤ እድልም ጭምር። አፄ ኃይለስላሴ ፍፁም ሥልጣን ነበራቸው። መንግስቱም፣ መለስም። አንድ የህወሃት አባል በትግል ላይ እያለ ቢዋሽ፣ የሆነ የምትወስድለት ነገር አለ። አሁን አርጅተህና 70 ዓመት ሆኖህ እንዴት ትዋሻለህ? ዛሬ ለልጆችህ ያልሰራህላቸው ሥርዓት ነገ ሀገር ሲበጠበጥ እንዴት አይታይህም? በመንግስትና በኢህአዴግ በኩል ትልቅ ኃላፊነት አለ ብዬ አስባለሁ። ሥርዓትን መስራት አለብን። ተቋማቶችን ማስተካከል ያስፈልጋል። ማንም የማያሽከረክረው ምርጫ ቦርድ መሠራት አለበት። ፍ/ቤት፣ ሚዲያዎች በነጻነት መስራት አለባቸው። የተደጋገመ ውሸት እውነት ይመስላል። በኢህአዴግ በኩል፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል፣ ራስን ከመመርመር ጀምሮ ትልቅ ኃላፊነት አለ። ህዝቡ ቀድሞ ሄዷል። ‹‹ከህዝብ ቀድመዋል አፄ ሚኒሊክ ናቸው›› የሚባሉት። ከዚያ በኋላ ያሉት ህዝቡ እንደ ቀደማቸው ነው የሚነገረው። ብዙዎቻችን ኃላፊነት አለብን። ጨለምተኛ አይደለሁም። ጥሩ ነገር እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ። ‹‹ሲነጋ ሲል ይጨልማል›› በሚለው ሳይሆን፤ ሁሌም ህይወት ሂደት ናት። አንዱን ሳታልፍ ሌላው ላይ አትደርስም። ስለዚህ ወደዚያ የምናደርገው ጉዞ ነው። ያሉ ችግሮችን ማውጣት በጣም ጥሩ ነገር ነው። ካልወጣ አታውቀውም፣ ካላወጣህ አታስተካክለውም። እኔም የዚያ አካል ሆኜ ጥሩ ስርዓት እንደምንፈጥር ተስፋ አደርጋለሁ።

‹ግንቦት 20 አንድ ትርፍ አለው› ተብሎ ሊነሳለት የሚችለው የደርግን ስርዓት መቋጫ እንዲያገኝ ማድረጉ ነው።› በማለት የምታምንበትን ገልጸሃል። የተቃውሞ ፓርቲ ትግልም በውጣ ወረድ የታጀበ ነው። ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ራሱ በገደል አፋፍ ላይ ነው የሚገኘው። ለሀገርና ለህዝብ የሚጣፍጥ ፍሬ ለማፍራት ምን መደረግ አለበት?

ሐብታሙ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ፤ በንጉሱም፣ በደርግም የነበሩ ችግሮች ኢህአዴግ ከ25 አመታት በኋላም እንዲቀጥላቸው መፍቀድ አይገባም። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ። ዋናውና መሰረታዊው ጥያቄ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች ናቸው። የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ጥያቄዎች ለነገ የሚባሉ አይደሉም። ፈጣን ምላሽ ይጠይቃሉ። ኢህአዴግ እነዚህን መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ለማክበር ዝግጁ እንዳልሆነና አቅሙም እንደ ሌለው ከመቼውም ጊዜ በላይ ግልፅ የሆነ ይመስላል።

የምትፈልገውን ነገር የማግኘት፣ የመምረጥ፣ በህይወት የመኖር፣ የመናገር፣የመጻፍ… የመሳሰሉት መሰረታዊ መብቶች በተጣሱበት ምንም አይነት ጣፋጭ ፍሬ ሊገኝ አይችልም።

ኢህአዴግ ስልጣን ለማስጠበቅ ብቻ የሚከተለው በልማት ስም የህዝብን መብት የማፈን ስርዓት ሊያሰፍን ካልሆነ በቀር ሌላ ሊሰራልን አይችልም።

ጣፋጭ ፍሬ ለማግኘት ከሁሉ መቅደም ያለበት ሰብዓዊ ልማት ነው። ከልማቱ ጋራ ተያይዞ ከድህነት የመውጣት ጥያቄ ይመጣል። መጀመሪያ ኅሊና… ኅሊና ከሆድ መቅደም አለበት። የኅሊና ነጻነት የሚባል ነገር አለ። ኢህአዴግ ያልገባው ወይም እንዲገባው ያልፈለገው ይህ ነው። የምን ጊዜውም መከራከሪያው ሆድን በማስቀደም ላይ ነው። ‹‹ልማት ይቀድማል›› ይለናል። የኅሊና ጥያቄዎች ሳይመለሱ ሆድ መቅደም የለበትም። የስርዓቱ ሰዎች የገዛ ህዝባቸውን እየዘረፉ በረሃብ የሚቆሉትና የሚያፍኑት እኮ ለዚህ ነው፤ እነሱ ጋር የኅሊና ጥያቄ የሚባል ነገር የለም። በአፋቸው ዴሞክራሲና ልማት ተነጣጥለው አይታዩም ይሉሃል፤ በተግባር ግን ከዚህ የተለዩ ናቸው፤ መብት የጠየቀን ያስራሉ፣ ያሰድዳሉ፣ ይገድላሉ። ኢህአዴግ ከባድ የቁርጠኝነትና የማስፈጸም ችግር ያለበት ድርጅት ነው። ላለፉት 25 ዓመታት ነገሮች ሲሻሻሉና ትንሽ ዕድል ሲያገኙ አልታዩም፤ ከአመት አመት ወደ ባሰ ጨለማ እያመራን ነው። ኢህአዴግ ለመነጋገርና ለሪፎርም መዘጋጀት አለበት፤ ተቃዋሚውም። አለበለዚያ መጨረሻችን የፈራነው፣ እንደ ሀገር መፍረስ ይመጣል። መነጋገር፣ መደማመጥ የሁሉ መፍትሄ ነው። ግን ተስፋ የሚያሳጣው፣ ኢህአዴግ በየጊዜው እየባሰበት እንጂ እየተሻሻለ የማይመጣ ድርጅት መሆኑ ነው።

**እንዴት?**

ለማስታወስ ያኽል፤ በ83 እና 84 ዓ.ም ልጅ ነበርኩ፤ ምንም አላስታውስም። ግን አንብቤ እና ጠይቄ ከተረዳሁት፣ መሬት ላይ የነበረውም ነገር እንደሚያሳየው፣ ከ83-87 ዓ.ም ድረስ የሚዲያው ነጻነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ነበር ይባላል። የፈለከውን መናገር ትችላለህ፤ የፈለከውን መጻፍ ትችላለህ፤ ኢህአዴግ ለማፈንና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልት አልዘረጋም፤ ዴሞክራሲን ለማስመሰል ወይም ለመሞከር ይፈልግ ነበር። ጥቂት ቆይቶ ግን ወደ ተፈጥሯዊ የድርጅቱ ባሕርይ ተመለሰ። ስለዚህ ወደ አፈናው ሲሄድ፣ ምሁራኖቹን መጀመሪያ በጠላትነት መፈረጅ፣ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ ያለውን ነገር ማጽዳት፣ ሚዲያዎችን በሙሉ መቆጣጠር፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ወይም ሲቪል ማኅበራትን በመንግሥት ደጋፊዎች በመሙላት መቆጣጠር፣ የሃይማኖት ተቋማትን መቆጣጠር… ፖለቲካውን አረጋግቶ ለመምራት ሁሉንም ተቋማት ‹‹በእኔ ቁጥጥር ሥር ማድረግ አለብኝ›› ወደሚል ተግባር ሄደ። መሆን የነበረበት ግን ይህ ሳይሆን ተቃራኒው ነው። የዴሞክራሲ ተቋማትን በካድሬ መቆጣጠር ሳይሆን መፍትሄው ገለልተኛ ሆነው እንዲጠናከሩ ማድረግ ነበር።

መንግሥት ሊሄድና ሊመጣ ይችላል፤ ሲስተሙ ግን መቆም ነበረበት። ስለዚህ ኢህአዴግ ያተኮረው ሲስተም ላይ ሳይሆን የቁጥጥር ዘዴ ግንባታ ላይ ነው። እምነት የሚጣልበት ተቋም ተገንብቶ ቢሆን ኖሮ ላለፉት 25 ዓመታት ምርጫ ቦርድ አያከራክርም ነበር። ዛሬም የዴሞክራሲ ጥያቄ ሀገሪቷን ያልሆነ ችግር ውስጥ አይከታትም። የሰብዓዊ መብት ተቋም ቢገነባ፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በሚያወጣው ውጤትና በሚነግረን ነገር ላይ ልዩነት አይፈጠርም። የሚዲያ ተቋሙ (በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለው) አንድን ፓርቲ ከማገልገል ይልቅ፤ ሀገራዊ ሚናውን ሊወጣ የሚችል ነጻ የሚዲያ ተቋም እንዲሆን ማድረግ ቢቻል፤ ይሄ ሁሉ ሀገራዊ ቀውስ አይፈጠርም ነበር። እነዚህ ነገሮች በሌሉበት የምታደርገው ምንድን ነው? በኢህአዴግ ፕሮግራም ላይ ነጻ የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚል አለ።

በነጻ ገበያ እኩል መወዳደር የሚቻልበት ዕድል ግን የለም። ይልቁንስ እንደምናየውና እንደምንሰማው የመከላከያው ክፍል ተቆጣጥሮታል። እርግጥ ነው፣ አንድ መከላከያ ሀገርን ከመጠበቅ ባሻገር በልማት ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ይገባል። ነገር ግን፣ አጠቃላይ የግሉን ሴክተር በሙሉ ከውድድር በሚያወጣ መልኩ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ወደ መከላከያ መሰባሰቡ ተገቢ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ አቋም ይዘን ተከራክረናል። የግል ዘርፉ ነው መንግስትን መቆጣጠር ያለበት። መንግስት በገበያ ውስጥ ያለው ተሳትፎ ውስን መሆን አለበት። መንግስት ኢኮኖሚውንና የፖለቲካ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ አምባገነን ለመሆን ሰፊ ዕድል ይሰጣል። በዚህም የግለሰቦች ሚና ከፍተኛ ይሆናል። አየህ፤ ኢህአዴግ በሁሉም ነገር ቁልቁል ሄዷል የምልህ ለዚህ ነው። በጥቅሉ አንድ ፓርቲ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። አሁን ኢህአዴግ በዚህ ሂደት አልፎ እድገቱን ጨርሷል።

**ኢሕአዴግ ሀገርን ያፈራረሰ፣ በርሃብ የቀጣን፣ ዴሞክራሲንና ፍትሕን ያሳጣን፣ ነጻነትን ያፈነ፣ በፓርላማ የገባን አንድ ተቃዋሚ እንኳ ያስወገደ አሳፋሪ ድርጅት ነው**

**ስለዚህ መፍትሔው ምንድነው?**

ከዚህ በኋላ ኢህአዴግ ሪፎርም ሳያደርግ፣ የዴሞክራሲ አብዮት ሳያመጣ፣ በዴሞክራሲ መንገድ ለውጥ ሳያመጣ፣ በልማቱ ጉዳይ፣ በሰብዓዊ መብት ለውጥ ሳያመጣ እስካሁን በመጣበት መንገድ ለመቀጠል የሚችልበት ዕድል የለም። ይልቁንስ ወደ በለጠ ቀውስ ውስጥ ነው የሚገባው። ሪፎርም የማምጣት ዕድሉን መጠቀም አለበት። ለኢሕአዴግ መፍትሔው የሚበጀው ይሄ ብቻ ነው። ተቃዋሚ ጎራውም ለውድቀቱ ሁልጊዜ ኢህአዴግ ላይ ማላዘኑን ትቶ ወደ ራሱ ማየት ይገባዋል። ወድቀን ጠብቀን፣ ለምን ደረሱብን እያልን ማልቀስ የትም የሚያደርሰን አይመስለኝም። ወድቀን ባንጠብቃቸው ፈጽሞ ሊደርሱብን እንደማይችሉ ጥርጥር የለኝም፤ ከጥቂት ለእውነት የቆሙ ሀገር ወዳዶች በቀር፤ የተቃዋሚ ጎራ አዝሎ የነበረው ግሳንግስ በራሱ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የማይጠቅም፤ ከግል ከፍተኛ ፍላጎት መዝለል ያልቻለ ስብስብ እንደ ነበረ ግልፅ ነው። ይህ ሲባል የሚከፋው ሰው ይኖራል፤ ግን የሆነ ሰው ይከፋዋል ብዬ አስተያየት ከመስጠት ወደ ኋላ አልልም።

ለምሳሌ፤ አንድነት ፓርቲ በኔ ዘመን ሊቀ-መንበር ያደረገው ኢንጂነር ግዛቸውን ነበር። ኢንጂነር ግዛቸው ከኃላፊነት ሲነሳ ‹‹እኔ ከሄድኩ ፓርቲው ብትንትኑ ይውጣ›› ብሎ አንድነትን በትኖ ሄዷል። ኢንጂነር ግዛቸው አንድነትን በማፍረስ ከኢህአዴግ የሚለይበትን አንድም ምክንያት የሚጠቅስ ሰው አላገኝም። ኢህአዴግ አንድነትን ለማፍረስ የሠራውን ያህል ኢንጂነር ግዛቸውም ሠርቷል እነትዕግሥቱስ አንድነትን ለማፍረስ የተጫወቱት ሚና ከኢህአዴግ የሚለየው በምንድን ነው?! ኢህአዴግ መጥቶ አንድነትን ባያፈርሰው ኖሮ ግዛቸው፣ ትዕግሥቱ እና ሰፊው የሚባሉ ሰዎችን ይዘን ነበር የምንቀጥለው። ያ ስብስብ በርካታ ችግሮች የነበሩበት ስብስብ ነበር። ወርቅ በእሳት እንደሚነጠረው የፈተና ቀን ሲመጣ አብዛኛው ተበታትኖ ድራሹ ጠፋ። በእርግጥ ይህንን ለማድረግ የታወቀው የኢህአዴግ ሴራ አለ። ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ እንዳይፈጠር ፍላጎት አለው።

*ወደ ሚቀጥለው ገጽ →*

አንድነትን ማፍረስም ለኢህአዴግ ለነገ የሚባል ነገር አልነበረም። ምክንያቱም አንድነት ውስጥ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በደንብ የገባቸውና የተረዱ ምርጥ ምርጥ ኃይሎች ነበሩ። እኔም ወደ አንድነት ስገባ እነዚህን ሰዎች ዐይቼ ነው። እነዚህን ጥቂት እርሾ የሆኑ ሰዎችን ይዞ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ውስጥ የኢህአዴግን ሁኔታ ተቋቁሞ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት ነበረኝ። ነገር ግን ውስብስብ የሆነው የተቃዋሚው ችግር በቀላሉ የሚለቀን አልሆነም።

በፖለቲካ አቋማቸውና እውቀታቸው አንድም ጥያቄ የማይነሳባቸውን እከሌ እከሌ ብሎ ማንሳት ይቻላል። እኔና ዳንኤል ሺበሺ ወደ እስር ቤት ስንገባ ከአንድነት ፓርቲ በጣም ተስፋ የጣልኩባቸው ምርጥ ምርጥ ሰዎች ነበሩ። ለምሳሌ ተክሌ በቀለን የመሰለ ፖለቲከኛ፣ በላይ ፍቃዱን የመሰለ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ በቂ እውቀት ያለው ሰው፣ ግርማ ሰይፉን የመሰለ ወሳኝ፣ አስራት አብርሃ፣ አስራት ጣሴ፣ ሥዩም መንገሻ፣ ጸጋዬ አላምረው... ነበልባል የሆኑት ወጣቶች፤ እንደነዳግም፣ እስማኤል ዳውድ፣ ስንታየሁ ቸኮል፣ ዳዊት ሰሎሞን፣ ያሬድ አማረ፣ አለነ ማህጸንቱን የመሳሰሉ በርካታ ትንታግ ወጣቶች። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እድል ቢያገኙ፣ እንደ ኢህአዴግ በር ዘግቶ የሚያፍን ድርጅት ባይኖሮ የተሻለ ደረጃ የሚደረስበት እድል ነበረ። መጨረሻ ላይ እኮ እነአስራት አብርሃ፣ አናንያ ሶሪ፣ ስለሺ ሀጎስ፣ መሐመድ አሊ.... ሌሎችም በርካታ ተስፋዎች ወደ አንድነት መጥተው ነበር። እኛም ከታሰርን በኋላ ፓርቲው ሊቀጥል የሚችልበት ሰፊ እድል ነበር። በላይ ፍቃዱ ተክሌ፣ በቀለ ግርማ፣ ሰይፉ, እውቀትና ክህሎታቸውን ተጠቅመው ምርጥ አመራር እየሰጡ ለውጥ የሚያመጡበት ብሩህ ዕድል ነበረ፤ ነገር ግን ይህንን ኢህአዴግ ጠምዝዞ አክሽፎታል።

የኢሕአዴግ ትልቁ ስሕተቱ አንድነትን ማፍረሱ ነው። አንድነትን አፍርሶ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ጨለማውን የበለጠ አበረታው። እኛን አሰረ፤ አንድነትን አፈረሰ። እንደ ሀገር ቢታሰብ አንድነት ሊፈርስ አይገባም ነበር። አንድነት ‹‹በርታ!›› ሊባልና ሊደገፍ የሚገባው ድርጅት ነበር። ድክመቶችን እንዲያርም እድል ሊሰጠው የሚገባ ድርጅት ነበር።

አየህ፤ ኢህአዴግ ፈፅሞ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ብቁም ምቹም እንዳልሆነ ሁሉ፤ የተቃዋሚ ጎራ ስብስብም ባለብዙ ችግር ነው። ከብዙ ሆድ አደሮች ጋራ ተጃምለን ለጉዳት ተጋልጠናል፤ እናም መፍትሄው ሰከን ብሎ ወደ ራስ ማየት፤ ራስን መገምገም ነው። ከሁሉ በፊት ሀገር እናስቀድም፤ ሪፎርም በገኘነውም፣ በተቃዋሚውም የግድ ያስፈልጋል ባይ ነኝ።

በመጨረሻም፤ እኔ በአሁኑ ወቅት በከባድ የጤና ችግር ውስጥ እንዳለሁ የምታየው ነው። የሀገሬ ጉዳይ ቢያሳስበኝም፤ በደረሰብኝ ግፍ ስቃዬን እንዳዳምጥ ተገድጃለሁ። እናም ከብዙ ከሀዲዎች መካከል የነጠሩ የቀድሞ የአንድነት ኀይሎች እንደ ትላንቱ ዛሬም ስላልተለዩኝ አመሰግናለሁ። ለተክሌ በቀለ፣ በላይ ፈቃዱ፣ ግርማ ሰይፉ፣ ሥዩም መንገሻ፣ አስራት ጣሴ፣ አስራት አብርሃ፣ ገበየሁ፣ እስማኤል ዳዑድ፣ ሰባህ ሙባረክ፣ ፋሲካ አዱኛ፡ ኢዩኤል ፍስሐ፣ አስማማው ኀይለጊዮርጊስ፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ ዮናታን ወልዴ፣ ለታታሪው ጠያቂዬ ተፈሪ፣ ወዳጄ ማይክ መልዐከ... ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። ኤልያስም እንደ ወንድም አልተለየህኝም ምስጋና ይድረስህ። ከሁሉ በላይ ጠበቃ አምሓ መኮንን፤ ከግፍ እስር ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም ሕይወቴን ለማዳን እያደረግክ ላለኸው ሁሉ ከቤተሰቤ ጋራ ምስጋናዬን እቀርባለሁ። በስም ያልተጠቀሳችሁ፤ በሀገር ውስጥና ውጭ ያላችሁትን ሁሉ አመስግኛለሁ። ሰላም ለሀገራችን ይሁን!

**በ25 ዓመታት ውስጥ በብዙ ነገር ላይ ፍሬ አለማፍራቱን ገልጸኻቸዋል፤ ፍሬ እንዲያፈራ ምን መፍትሔ አለ?**

ዳንኤል፡- መፍትሔ የሌለው ችግር የለም። ሁልጊዜ ችግር ሲያጋጥም አውሮፕላን ትፈጥራለህ፤ ችግር ሲያጋጥም መኪና ትፈጥራለህ፤ ጨለማ ሲያስቸግር መብራት ትፈጥራለህ። እንደዛ እያደረግክ ለችግሮቹ መፍትሔ እየፈጠርክ ትሄዳለህ። ኦሮሚያ ውስጥ ችግር እናያለን፤ ጋምቤላ ውስጥም ችግር እናያለን፤ እንደ ገና ከዚህ በፊት በአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰ ችግር እናያለን። አሁን ኮንሶ ላይ ያለውን ችግር እናያለን፤ አርባ ምንጭም ላይ ችግር አለ። እኔ በታሪክ አርባ ምንጭ ከተማ ላይ ጦርነት ይፈጠራል ብዬ አስቤ አላውቅም። እንዲሁም ወደ ሰሜኑ ስትሄድ በወልቃይት ላይ በአማራ ተወላጆችና በአማራ ክልል ላይ ያለውን ችግር እናያለን። በአጠቃላይ በሀገራችን በተቃውሞ እየተናጠች ነው ያለችው። ህዝብ እየተቃወመ ነው ያለው። ‹‹የራሴ ናቸው›› ያላቸው ገበሬዎች በሙሉ ለመንግስት ጀርባ ሰጠዋል። የዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂ የግንቦት 20 ስርዓቱ ኢህአዴግ ነው። ህወሃት የሚባለው ኢህአዴግ ስሙን እንኳን አልቀየረም። ህወሃት ማለት የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት ማለት ነው። ይህ ስም እስከ መቼ ነው የሚቀጥለው?

ሄግል የሚባል ፈላስፋ የተናገረውን እዚህ ጋር ልዋስ፤ ‹‹ችግሩን የፈጠረ ጭንቅላት፤ መፍትሔ ሊፈጥር አይችልም›› ይላል። ኢሕአዴግ ሀገርን ያፈራረሰ፣ በርሃብ የቀጣን፣ ዴሞክራሲንና ፍትሕን ያሳጣን፣ ነጻነትን ያፈነ፣ በፓርላማ የገባን አንድ ተቃዋሚ እንኳ ያስወገደ አሳፋሪ ድርጅት ነው። ይሄ ሁሉ የግንቦት 20 ውጤት ነው። ወገኖቻችን የሞቱት፣ ምናልባት ደርግን በማሸነፍ ረገድ እንደ ጥሩ ጎን አድርገን ልናይ እንችላለን። ግን ከዚህ ባሻገር ያለው ነገር በጣም አሳሳቢ ውድቀት ውስጥ ነው ያለነው። ስለዚህ በግሌ ኢህአዴግ መፍትሔ ያመጣል ብዬ አላስብም።

ኢህአዴግ ማለት፣ በዚያ ውስጥ ያሉ ጥቂት የተጠቃሚዎች ስብስብ ማለት ነው። ርሃቡን ጨምሮ ይህንን ሀገሪቱ ላይ ተፈጠረ የሚባለውን ቀውስ የፈጠረው ሚንስትር ችግሩን አቅፎ ስለመልካም አስተዳደር ያወራል። ችግርን የፈጠረው አካል ደግሞ ችግሩን ሊፈታ አይችልም። ይህን አንጎል እዚህ ቁጭ አድርገህ ‹‹ኢህአዴግ ተደራደረኝ›› ብለህ መጮኽ፣ መለመን፣ የሚሳካ አይመስለኝም።

ነገር ግን፣ ከኢሕአዴግ ውጭ ያለ ዳያስፖራ አለ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አለ፤ የኢትዮጵያ ወጣት አለ፤ የተለያየ ቋንቋ የሚያወራው የማኅበረሰብ ክፍል አለ፤ ይህ ሁሉ ስለ ሀገሩ ማሰብ አለበት።

በሀገሪቷ ጉዳይ ላይ ስጋት ያለህ ይመስላል። ስጋትህ ምንድን ነው?

አዎን ስጋት አለኝ። ሥጋት፣ ጥርጣሬና ምኞት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ስጋት ሁል ጊዜም ምክንያታዊ ነው። ጥርጣሬ ደግሞ በምክንያትም፣ ያለምክንያትም ዝም ብለህ ልትጠራጠር ትችላለህ። ሀገሪቱ በጣም አደጋ ነገር ውስጥ ነች ብዬ እሰጋለሁ። ኢትዮጵያ መንታ መንገድ ላይ ነው ያለችው። የኢሕአዴግ ውድቀት ሀገሪቷን ሊያፈርሳት ይችል ይሆናል። የኢህአዴግን ውድቀት ተከትሎ አገሪቷን አንድ አድርጎና አሰባስቦ የሚመራ ኃይል ከሌለ ወይም እኛ ካልፈጠርነው፤ ችግራችን እጅግ በጣም የከፋ ይሆናል ማለት ነው። ስጋቴ በዚህ መልኩ እንዲታይልኝ እፈልጋለሁ።

ከልማት ጋር በተያያዘ፤ ከጥራትና ከሚወጣበት ገንዘብ አኳያ ከወሰደው ጊዜ አንጻር ሲታይ ራሱን የቻለ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። የጥራቱ ጉዳይ ዓለም ያወቀው ነገር ነው። ስለሀገሪቱ ጉዳይ ብዙ ነገር ተወርቷል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው መጽሔት ከነበረው ጦቢያ መጽሔት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ስለሀገሪቱ ጉዳይ አንስተናል። ስለኢትዮጵያ በአማርኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ኦሮሚኛ ቋንቋ ያልተጻፈ መጽሐፍ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ የለም። ብዙ ብዙ ተብሏል። አሁን ግልጽ ነው፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ተረድቷል።

**መፍትሔውስ?**

በመፍትሔ ደረጃ ኢህአዴግን ወደ ውጭ እናድርግ ማለት አይደለም። የሚፈልግ ከሆነ ሊነጋገርና ሊሳተፍ ይችላል። ይሄ ግን እስራቱን አቁሞ ማለት ነው። ግን ኢህአዴግ ይሄን ያመጣል ብዬ አላስብም። ምክንያቱም ወደ ታሪክ ስንመጣ፤ ኃይለሥላሴ ደርግ እስከሚቀብራቸው ድረስ ቤተ-መንግሥት ውስጥ እያሉ ዕድል ነበራቸው። ያንን እድል ሳይጠቀሙበት ቀርተው ነው በደርግ እጅ ላይ የወደቁት። ደርግን ብናይ፤ ሻዕቢያና ወያኔ በቅርብ አምቦና ደብረዘይት እስኪደርሱ ድረስ ‹‹አለን›› እያለ ነበር። ነገር ግን ከዛ በፊት የድርድርና የሚያስብበት ዕድሎች ነበሩት። ከጄነራሎቹም በኩል የሚቀርቡ ጥያቄዎች ነበሩ። መንግሥቱ ይህንን ሁሉ አሻፈረኝ ብሎ መጨረሻ ላይ ስደትን ኑሮው አድርጓል። ሀገሪቱንም ለእነዚህ ከራሱ ለማይሻሉ ሰዎች አስረክቦ ሄዷል።

ኢህአዴግን ብትወስድ፤ በ1993 ዓ.ም ቀውስ ውስጥ ገብቶ ነበር። እዚህ ሀገር ላይ ልክ እንደ ዛሬው አይነት ተቃውሞም ነበር። የዚያን ጊዜ ቆም ብሎ አስቦ፣ ነገሮችን የማየት እድል የነበረው ቢሆንም አልተጠቀመበትም። በድጋሚ በ1997 ዓ.ም እድሉን አልተጠቀመበትም። ዘንድሮም እንደዚያው። ቢያንስ ከታሪክ አንጻር፣ ሦስት ጊዜ አገራዊ ችግር ሲፈጠር ታይቷል። የብዙ መንግሥታትን፣ በተለይም የአፍሪካ ሀገራትን ስንመለከት፤ በጦርነትም ይሁን በምርጫ፣ ሦስት ወይም አራት ጊዜ ነው ዕድል የሚሰጣቸው። እነዚያን ዕድሎች ግን አንዳንድ ማስተዋል የሌላቸው መሪዎችና ፓርቲዎች አይጠቀሙበትም። ስለዚህ ይህንን ዕድል አልተጠቀመበትም ኢህአዴግ። አሁንም ይጠቀምበታል የሚል እምነት የለኝም።

**በመጨረሻ፤ ከእስር በኋላ የደረሰባችሁ ነገር አለ?**

አሁን ከተፈታን በኋላ ራሱ ብዙ ችግር እየደረሰብን ይገኛል። በባለቤቴና በግሌ ስልክ እንደገና የሚያስፈራሩን ሰዎች አሉ፤ ያውም ጠያቂ አስመስለው። እኛ ችግር የለብንም፤ እንዲህ የሚያደርጉትን ምንም አንፈራም። ኢህአዴግ የብጥብጥ መንገድን ትቶ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የሚታረቅበትን መንገድ ማሰብ አለበት የሚል እምነት አለኝ። የሀገሪቷን ኢኮኖሚና ሥልጣኑን በሙሉ ጠቅልሎ የያዘበት ሁኔታ ታያለህ። በእኛ እምነት ቴሌ፣ መብራት ኀይል፣ ውሃ ሀብት... ለግል ዘርፉ ሊደረጉ ይገባል። መንግሥት ታክስ ነው መሰብሰብ ያለበት፤ እንጂ ራሱ ነጋዴ፣ ራሱ አስመጪ፣ ራሱ አካፋፋይ፣ ራሱ ቸርቻሪ ሆኖ እስከ ታች ድረስ እየሰራ ሀገሪቱን መዝረፍ የለበትም። ሀብት በሙሉ በተወሰኑ ሰዎች እጅ ገብቷል። ከዚህም የተነሳ ነው ህዝቡ ደሃ ሆኖ የቀረው። ምናልባት አንድ ፐርሰንቱ ሀብታም ሊሆን ይችላ። ሌላው 99.9ኙ በሙሉ ደሃ ሆኖ የቀረበት ሁኔታ ነው ያለው። ስለዚህ መንግሥት ይህን ማስተካከል አለበት። ተቀዋሚዎችም ይህቺን ሀገር የማዘመን ኃላፊነት አለባቸው። ‹‹ሙስናን አጠፋለሁ›› ብሎ ተነስቶ ነበር። ግን ማጥፋት አልቻለበትም:::: በሙስና ከላይ ጀምሮ እነማን እንደ በሉ ይታወቃል። ይህን ማድረግ አይችልም። አንድ ሚሊየን የበላውን ትቶ፤ አንድ ሺኅ የበላውን ያሳድዳል። እሱ ሚሊየን ብር በልቶ ስዊዝ ባንክ ሀብቱን አከማችቶ፤ አንድ ሺኅ ብር የበላውን ደሃ እስር ቤት ሲያማቅቅ ይገኛል። ስለዚህ በዚህ አይነት ሁኔታ ኢህአዴግ ለውጥ ያመጣል ብዬ አላስብም።

አብርሃም ፈቃዱ



# ከግጥም ጋር በፍቅር የወደቀው ሐያሲ



…እሁድ ጧት አንድ ልማድ አጎልብቻለሁ፡፡ በሸገር ኤፍ.ኤፍ 102.1 በሚተላለፍ የእሁድ ጥዋት ፕሮግራም መዓዛንና የአብዱን ጨዋታ ካልጋዬ ሳልነሳ በካፌያቸው መታደምን፡፡ በግንቦት ሃያ ስምንቱ እሁድ ጧት ንጋቱና ወጣቱ መምህሬ ዳግም ነበሩ፡፡ ስለፕሬስ ነጻነትና በኢትዮጵያ እየተተገበረ ስላለው የሚዲያ ሁኔታ በሚል ውይይት እያደረጉ ነበር፡፡ በመሐል የማለዳ ትኩስ ዜናዎችን በማኅበራዊ ሚዲያ ለመቃረም ገጼን ከፈትኩ፡፡ መጀመሪያ የተመለከትኩት ዜና ግራ አጋባኝ፡፡ ግራ-ማጋባት ብቻ አይደለም እንዴት ዓይነት ቀልድና ድፍረት ይሆን እያልኩ አሰብኩ፡፡ ጠርጣሪም አይደለን? ደሞ የማን ክፉ ነው እንዲህ በማለዳ ዕዝራ ገጽ ላይ በክፉት የዘመተው በማለት ተገረምኩ፡፡ ገጹ ላይ የሰፈረው ጽሑፍ እንዲህ ይላል . . . . Abedlla Ezra has died yesterday afternoon. We are now taking his body from Butajera to Addis Ababa. It was a shock for all of us it just happened so quickly. Still can’t believe his gone. May his soul rest in peace. To all his beloved families & friends be strong; especially to his beloved only daughter @Mahlet Abdella; we are all here for your dear you have a hero father. (Got his fb through his phone). Jun 5, 2:18.

ከስር ያሉትን ዜናዎች ስመለከት ዜና እረፍቱ እውነት መሆኑን አረጋገጥኩ፡፡ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ዕዝራን ለመሸኘት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስትያን ደረስኩ፡፡ ጥቂት ሰዎች በዓይን ብቻ የማውቃቸው አፀዶቹ አጠገብ በሚገኝ ወንበር ላይ አረፍ ብለው ያወጋሉ፡፡ ባለፍኩባቸው አካባቢዎች ሁሉ ዶፍ ዝናብ እየወረደ ነበር ልክ ፈረንጆቹ "it’s raining cats and dogs" የሚሉትን ዓይነት፡፡ በተቃራኒው ዮሴፍ ቤተክርስትያን አካባቢ ያለው ደመና ገና ለመዝነብ የሚያኮበኩብና የዕዝራን ስንብት የሚጠብቅ ይመስል ነበር፡፡ መሐል ላይ በጥቂቱ ከማካፋት በስተቀር እስከፍጻሜው አልዘነበም፡፡ ሥነ-ሥርዓቱን ባልተከተለ መንገድም አንድ የቤተክርስትያን ጠባቂ መጨረሻ ላይ እያወከ ነበር፡፡ የቤተክርስትያኗን ግርማ የሚያኮስስ ተግባር ነውና የፈፀመው ይመለከተናል የምትሉ አስቡበት፡፡ በሽኝት ሥነ-ሥርዓቱ ወቅት አንጋፋው አበራ ለማን ጨምሮ ወጣት ጸሐፊያን ተገኝተዋል፡፡ በጥቅሉ ቤተሰቦቹን ጨምሮ ወደ መቶ የሚጠጋ ሰው ነበር፡፡

ሚዩዚክ ሜይዴይ ከዓመታት በፊት በኢምፔሪያል ሆቴል የመጽሐፍት ውይይት ባዘጋጀበት ጊዜ እዝራ ዳሰሳ አቅራቢና አወያይ ነበር፡፡ ያኔ ገና ያልበሰልኩ የሐይስኩል ተማሪ ብሆንም አቀራረቡ መንፈሴን ይዞት ተሰውሮ ነበር፡፡ ዕዝራን በዚህ ዓመት በአካል ሁለቴ ነው ያገኘሁት፤ መስከረም 10 ቀን 2008 ዓ.ም በገጣሚ በዕውቀቱ ስዩም ስብስብ ግጥሞች ላይ ወመዘክር ተገኝቶ የእሱ ብቻ የሆነውን ዳሰሳ በሰጠበት ዕለትና የካቲት አካባቢ መዘጋጃ ቤት የማንያዘዋልን 'እንግዳ' የሚለውን ትያትር በተመለከተበት ዕለት ነበር፡፡ በሰፊው ለመጫወት የማይመቹ መገናኘቶች ቢሆኑም ጥቂት ሐሳቦችን ነገር ግን የሚያበረቱ ቃላትን መግቦኛል፡፡

እዝራ አብደላ መሪሃም ከምትባል ኢትዮጵያዊት እናቱና መሐመድ ከሚባል የመናዊ አባቱ በ1950 ዓ.ም አንዋር መስጊድ አካባቢ ተወለደ፡፡ እናቱ ዕዝራ ብለው ሲጠሩት አባቱ ደግሞ አብደላ አሉት፡፡ እስከህልፈቱ ድረስ ሁለቱንም ስሞች ይጠቀም ነበር፡፡ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአፍሪካ አንድነት፣ በልዑል ወሰንሰገድና በተፈሪ መኮንን ተከታትሏል፡፡ ድግሪውን በባይሎጂ የመን ሰርቷል፡፡ ደራሲ እና ጋዜጠኛ አለማየሁ አበራ ለማ በሰኞ ምሽቱ የመታሰቢያ ፕሮግራም ላይ ስለዕዝራ ሲናገር የፊዚክስም ሊቅ ነበር ይሏል፡፡ ሳይንስን ጠንቅቆ ያውቅ እንደነበረና ዕዝራ የሰው ህመም እንደወረረሽኝ የሚጋባበት ሰብዓዊነቱ ከሌሎች በተለየ ጠሊቅ እንደነበረ ከመድረኩ በተደጋጋሚ ተነስቷል፡፡ "ዕዝራ ሁለት ሆነን ሁለት ምግብ ለመብላት አራት እንድናዝ ያደርግ ነበር" ይላል ደራሲ እና ጋዜጠኛ አለማየሁ ገላገይ፤ ምክንያቱም ከሚበሉት ይልቅ የሚተርፈው ስለሚበዛ በጓሮ በኩል ስለተቸገሩት ቸርነቱን ያለስስት ለማጋራት መሆኑን ይገልጻል፡፡

ማኅበራዊ ሚዲያዎች ማንነታችንን በጥቂቱም ቢሆን ከምንገልጽባቸው የአዲሱ ዘመን ሌላኛው መንገድ መሆን ከጀመሩ ሰነባበቱ፡፡ ዕዝራም የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ነበር፡፡ ለሁለት ዓመታት ገጹ ላይ ያሰፈረውን ጽሑፍ ወደ ኋላ በመጓዝ ተመለከትኩ - ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑት ስለግጥምና ግጥም በተከሸኑ ቃላት የተየበባቸው ነበሩ፡፡ ዕዝራ ከግጥም ጋር በፍቅር የወደቀ ስለመሆኑ የሚጮሁ ናቸው፡፡ አበቃቀሉን ያላስተካከለ ተክል ድጋፍ እንደሚያበጁለት ላልተቃኑና መቃናት ለሚገባቸው ወጣት ገጣሚያን ድጋፍ በመሆን መልካም አበባ እንዲያፈሩ የሚያተጋ ነበር፡፡ እንደ አበባ ለፈኩ ግጥሞች ደግሞ ምላሹ ወደነሱ በመጠጋት መዓዛውን በማሽተት ይረካል፡፡ በሱ ቋንቋ 'ተናዳፊ' በሚላቸው ግጥሞች ውስጥ ዓለሙን ያስውባል፡፡ አንድያ ልጁ ማህሌት ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ በታተመችው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ጋዜጠኛ አለማየሁ አንበሴ፤ ‹‹ስለግል ህይወቱ አውቃለው ትያለሽ?›› በማለት ላቀረበላት ጥያቄ "…ስለግል ህይወቱ ብዙ አላውቅም አንዳንድ ነገር ስጠይቀው እንኳ "ቆይ አንድ ቀን በሰፊው ቁጭ ብለን ነው የምነግርሽ" ይለኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን እንኳ የውስጡን በደንብ ሳይነግረኝ ነው ያረፈው" በማለት የአባቷን ‹‹የቆይ አንድ ቀን›› የጨዋታ ቀጠሮ ባለመስመሩ በቁጭት እንዲህ ባለ ሁኔታ ለጋዜጠኛው መልሳለታለች፡፡

ጋሽ እዝራ ስለ አንድያ ልጁ ማህሌት አብደላ በፌስ ቡክ ገጹ ነሐሴ 2007 ዓ.ም ላይ እንዲህ ጽፎ ነበር ‹‹ለልጄ ለማህሌት -ማቲሻ- ለምን ይሆን *ዝምታ* የኑሮን እልልታ የሚያረግበው ዕንቁጣጣሽም ሰምና ወርቁን እስከመቼ፣ ግራና ቀኝ እየገላመጠ በምናምን ይደብቀዋል አባትሽ›› አብደላ ዕዝራ ይላል ከስር፡፡ ባይሳካም ሁለቱም በየበኩላቸው ዝምታቸውን ለመካፈል ቀጠሮ ነበራቸው ከዚህ ባሻገር አገላለጹ የታመቀና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት መሆን ይጠይቃልና

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



ዮሐንስ ሞላ

# በመንገድ ላይ. . .

እንደ ሁሌው ሁሉ የኢሚግሬሽንና ፓስፖርት ቁጥጥር ደጃፍ ያሳቅቃል። እንደ እኛ ባለ አገር፥ እሱን ሳያልፉ "ልጓዝ ነው" የሚሉ የታደሉ ናቸው። በባዶ ሜዳ የቀደሙ ሁኔታዎችን እያስታወሱ፥ "አልፍ ይሆን/አላልፍ?" "ምን ይሉ ይሆን?" "ፓስፖርትህ/ሽ ተቀምቷል ይሉኝ ይሆን?" የሚል ሰቀቀን ስላለ፥ ምናልባትም የሕይወት ዘመን ትልቁን ጸሎት የሚያደርሱት ከአገር ለመውጣት ፓስፖርት ተቆጣጣሪ ደጃፍ ሲሰለፉ ሳይሆን አይቀርም። እንደሚጠበቀው እያጉተመተምን በሰላም አለፍን። ዋጋ አወዳድሬ እና ለማስታወቂያ ጊዜ ማማለያ ባዘጋጁት የአንድ ተጨማሪ ሻንጣ ጭነት ተማርኬ ትኬት ስለቆረጥኩ፥ በኤሚሬትስ አየር መንገድ ነበር የተሳፈርኩት። በጠራራ ጸሐይ ወጥተን፣ ጢያራ ተሳፍረን ዱባይ ዘለቅን።

የአውሮፕላኑ ዘናጭነት፥ ከዚህ ቀደም ከተሳፈርኳቸው ጋር ሲታይ፥ ለጉድ ነው። የተሳፋሪው ዓይነትና ስብጥርም ይገርማል። - ከ3 እዮሽ ጸጉር እስከ መላጣ ድረስ በስታይል የተቈጎረጎሩ እንስቶች ታጭቀዋል። (የስታይል ዝጉርጉርነቱም የአኗኗርና የቦታ ልዩነትን የሚያሳብቅ)። አየር ላይ እያለን ስልኬን ስነካካት 'wifi on air' እንዳለ ተገንዝቤ፥ አያያዝኩትና ሰፊውን ዓለም ከሰማይ ቁልቁል ማየት ተያያዝኩ። ረዘመ አጠረ፥ መንገድ ሆድ ስለሚያባባ "የሰማይ አሞራ ልጠይቅሽ ወሬ..." ብዬ በዮፍታሔ ግጥም ከአሞራዎቹ ጋር ማውጋት ባልችልም፥ በጎግል በኩል አጮልቄ "እንዴት አድረሽ ዋልሽ አገሬ?" ብዬ ማየቴም አልቀረም።

## ዱባይ አውሮፕላን ማረፊያ

መንገዳችን የ5 ሰዓት ገደማ ትራንዚት ስላለው የተንጣለለውን የዱባይ ተርሚናል ዞርዞር ብዬ ለመቃኘት የነበረኝ ሀሳብ፥ ገና 3 እርምጃዎችን ከመሄዴ በአንዲት ምስኪን "ወይኔ ጉዳችን" የሚል የጭንቀት ድምጽ ተደናቀፈ። "ሀበሻ ነው እናናግረው" የሚል የሌላ እህት ድምጽም ተከተለ። ዞር ብዬ ሳይ ወደ 50 የሚጠጉ ሴቶች ተደነባብረው ቆመዋል። ትንንሽ ልጆች (አስራዎቹ ውስጥ የሚመስሉ) ይበዛሉ። የገጠር ልጆች ይበዛሉ። ሻንጣቸው ከውጭ በባለቀለም የሱፍ ክር እና በጅማት ክር ከተወሰወሰ አንስቶ፣ በፌስታል ብቻ እቃቸውን የያዙ ሴቶች ይታያሉ። ተጀምሮ ግማሹ ያላለቀ ጸጉርም ይታያል። ድንገት "ኑ ቪዛችሁ ደርሷል" የተባሉ ይመስላሉ። ይገርማል!

"ወዴት ናችሁ?" አልኳቸው ከእነርሱ ባላነሰ ደንግጬ።

"ቤይሩት! በናትህ..." አሉኝ ድምጾች ተደራርበው። ዐይኖች ተቁለጭልጨው።

"አሁን በመጣው አውሮፕላን ነው የመጣችሁት? እስኪ ቦርዲንግ ፓሱን ልየው" ስላቸው

"አዎ" ብለው ፓስፖርታቸውን አቀበሉኝ። የአንዷን ተቀብዬ፣ ከውስጡ ቦርዲንግ ማለፊያውን ስመለከተው 10 ሰዓት ገደማ የሚጠጋ ትራንዚት እንዳለ ተገንዝቤ፤ የመረጃ ዴስክ ላይ ሄጄ አውሮፕላኑ የሚነሳበትን በር ጠየቅኋት። ነገረችኝና አብረን መሄድ ጀመርን። ከነበርንበት ሩቅ ስለነበር ከፊት እየመራኋቸው ጥቂት ሄደን፣ ዞር ብዬ ሳይ እጅብ ብለን የነበርነው በመስመር ተበትነናል። ድጋሚ ተሰባስበን መንገዳችንን ቀጠልን። በአማርኛ መግባባት የማይችሉ ይበዛሉ። "አደረስኳቸው" ሳይሆን "ነዳኋቸው" ለማለት በሚቀልና በሚያሳቅቅ መልኩ ከመሳፈሪያቸው በር አካባቢ አደረስኳቸው።

"መጫወቻ አደረጉን እኮ። አንተ ባትኖር ምን ይውጠን ነበር?" አለች አንዷ። በየቋንቋው ምስጋና ወረደልኝ።

"ችግር የለውም። እኔ ምንም አላደረግኩም። አሁንም ተጠባብቃችሁ ራሳችሁን ጠብቃችሁ ሂዱ። አደራ! እግዚአብሔር ይርዳችሁ።" ብያቸው ተመለስኩ።

ቀድሞ ወደነርንበት ስመለስ፥ "ውይ እግዚአብሔር ይስጥህ" የሚሉ ድምጾች ተቀበሉኝ። ከእነርሱ ጋር ቆመን ማውራት፣ ማማረርና "መጨረሻችን ግን ምን ይሆን?" መባባል ጀመርን።

"ምናለ የ1 ወር ስልጠና እንኳን ቢያደርጉላቸው?"

"ምስኪኑን ሁሉ ከገጠር አፈናቅለው የጅብ ሲሳይ ያደርጉታል። አሁን እነዚህ እንዴት ነው መብታቸውን ማስከበር የሚችሉት? እዚያ ሄደውስ እንዴት ነው ስራ የሚሄዱት? እንግዲህ እነዚህ ናቸው ከፎቅ ተወረወሩ፣ ውሃ ተደፋባቸው የሚባሉት።"

"ህገወጥ ነው እንዳይባል አውሮፕላን ተሳፍረው ነው የሚመጡት። ህጋዊ ነው እንዳይባል የሚረዳቸው የለም። ግራ የገባ ነገር..."

"ኢሚግሬሽን ካየሽ ይሄ ምንም ማለት ነው። እዛ ፓስፖርት ለማውጣት ተሰልፈው ስማቸውን እንኳን መጻፍ አይችሉም እኮ።"

"የብሄር ብሄረሰብ መብት ተብሎ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ይማሩ ተብሎ በአማርኛም እንዳንግባባ አደረጉን። ቋንቋ ማወቅ እኮ ከዚያ ባሻገር የመግባባት ስልጣኔንም ያዳብራል።"

"ምን ያድርግ ሰው በአገሩ መስራት እና መኖር ካልቻለ? ስንቱ ነው ለትምህርት ወጥቶ በዚያው የሚቀረው? ከነቁ መከራ። ካልነቁም መከራ። የነቃውን ግፈኛ ይገፋዋል። ያልነቃውንም ቁስ ይስበዋል።"

"አንዷት ዘመዴም እንዲሁ ልቧ ቆሞ ተነሳች። ብል ብሰራ እምቢ አለች። አንቺ አሜሪካ እየተሰደድሽ እኔን ታስቀሪያለሽ አለችኝ ጭራሽ። ይህን ያህል ነው የማይገነዘቡት ችግሩን።"

ሌላም ሌላም ብዙ ነገሮች ተወሩ።

በዚህ መሀል "እየሱሴ ምን አጠፋው?" የሚል ሲቃ የተቀላቀለበት ንግግር ሰምተን ዞር አልን። ፀጉሯን ሁለት እዮሽ የተሰራች፣ ሮዝ ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሰችና ኤርገንዶ ነጠላ ጫማ የተጫማች ምስኪን ሴት እጇን ደረቷ ላይ አጣምራ ደርቃ ቀርታ ስታለቅስ ተመለከትን።

"ምን ሆነሽ ነው?" አለቻት ከመካከላችን አንዷ

"ፓስፖርቴ ጠፋ።" ብላ ከነበረው በላይ እዬዬዋን አቀለጠችው። መቼም አባባይ እና "አይዞህ/ሽ" ባይ ሲኖር ሆድ መባባቱን ይጨምራል።

"የት? እስኪ በደንብ ፈልጊው" ተብሎ የጀርባ ቦርሳዋ ተዘረገፈ። የለም።

"አውሮፕላን ውስጥ ነው የወደቀብኝ። ሲነሳ ሲንገጫገጭ ነው።" አለች።

"ካወቅሽ አታነሺውም ነበር። ወይ ከጎንሽ አትጠይቂም?"

"አማርኛ በደንብ አልችልም። ሳወራት አልገባትም። በኋላ አነሳዋለሁ ብዬ ረሳሁት።" አለች። (እንዲህ በተስተካከለ አማርኛ አይደለም ያወራችን። ስጽፈው አስተካክዬው ነው።)

የመረጃ ዴስክዋን ሴት ቀርበን አወራናትና፥ "ቆዩ" ብላ ስልክ ደዋወለች።

"ይገኛል። እኛ ለምደነዋል። በየቀኑ ፓስፖርቷን የምትጥል ኢትዮጵያዊት ታጋጥመናለች። ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። ሁሉም ነቃ ያሉ አይደሉም። የት ለምን እንደሚሄዱም አላውቅም።" አለች።

የጠፋባትን ሴት እያጽናናን፣ እዛው ያገኘነውን አስረጅ እያጣቀስን ነገሩን መጫወት ቀጠልን።

ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ "ፓስፖርቷ ተገኝቷል አሁን ይዘውላት ይመጣሉ።" ብላ የምሥራቹን አሰማችን። ከአፍታ ቆይታ በኋላም አንድ ጎረምሳ፥ ይዞ መጥቶ አስፈርሞ ሰጣት። እኛም፥ ድጋሚ እንዳይጠፋ ከማስጠንቀቂያ እና ከብዙ አይዞሽ ጋር ተሰናበትናት። ጨዋታችን ግን ቀጠለ። ገረመኝ! ሁሉም የሚያወራው ጉድ አለው።

"አንድ ቅጠል ነበር እንደ እኔ የከፋው

የሆዴን ብነግረው የአፉን ቅጠል ተፋው።" የሚለውን የመንገድ ላይ ጥቅስ አስታወስኩ።

## ሰማይ ላይ

የጋሽ አሰፋ ጫቦን "የትዝታ ፈለግ" መጽሐፍ እያነበብኩ በየመሀሉ ኢንተርኔት እየተጠቀምኩ ነበር መንገዴን የገፋሁት። ያዛለቁኝን የአዴል እና የሮናን ኪቲንግ አዳዲስ አልበሞችም ነበሩ። የኢንተርኔቱን ነገር ሳስብ አየር መንገዳችን ነው ቀድሞ የመጣብኝ። መቼስ፥ ሰው አገር እና ሰው እጅ ላይ የሚያዩትን ሁሉ ከአገር ጋር ማነጻጸር አይቀር። ፀሐዩ መንግስታችን ደግሞ፣ እንኳን በሰማይ 'ዋይ ፋይ' ሊያመቻች ቀርቶ፣ የምድሩንም ድርግም ቢያደርገውና፥ ከምንለውም በላይ፣ እንደነ ሰሜን ኮሪያ 'ዋይ ዋይ' እያልን ብንኖር ደስታው ነው።

ፌስቡክን እና ሌሎች የማኅበረሰብ ድረገጾችን እንደጦር ፈርቶ ሕግ በማርቀቅ የተጠመደ፣ ደግሞ ከእነርሱ ላይ ሰው እየለቀመ የሚያስር፣ ከሰማይ ላይ ሲሆን የድንጋይ እሩምታ ሊዘንብበት እንደሚችል ማሰቡ አይቀርም። ለአፍታ በምናብ እልም አልኩ። የፌስቡክ ወዳጆች ከአውሮፕላን ላይ ሆነው በሚጽፏቸው ነገሮች ምድር ላይ ቃላት እና ሀሳቦች ውርውር እያሉ ሲያሸብሩ አስቤ ፈገግ አልኩ።

## ፌስቡክ ላይ

ጎራ ብዬ ካንዱ ገጽ አንዱ ገጽ ስዟዟር፥ 'ጀርመን ፍራንክፈርት፥ በአቶ ጌታቸው ረዳ ላይ የቀረበው ተቃውሞ ሙሉው ቪዲዮ ይህን ይመስላል።' የሚል ጽሁፍ ተከትዬ ቪዲዮውን ተመለከትኩት። ፈገግ ማለቴ አልቀረም። ወዲያው፥ ከወራት በፊት በዚሁ በ‹‹አዲስ ገጽ›› መጽሔት በሰጡትና በሁለት ዙር (5ኛ እና 6ኛ እትሞች ላይ) ቀርቦ በነበረው ቃለመጠይቃቸው ላይ ከብዙ መንተባተብና ላይ ታች ማለት ጋር፥

"ኢትዮጵያን ለማፍረስ አንድ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ሙሉ ሀገር በግማሽ ቀን ቀውጢ በሚደረግበት ዘመን፤ ሥልጣን ላይ የወጡ ሰዎች ለምን 40 ዩኒቨርሲቲዎች መቋቋም አለባቸው ብለው እንደሚያምኑ ነው የማይገባኝ። ሀገር አደንቁረህ የመግዛት ፍላጎት ካለ፣ ለምን ሁከትን ታበዛለህ? ኢሕአዴግ አድሃሪ ድርጅት ቢሆን ኖሮ ለምን ዩኒቨርሲቲዎችን ያስፋፋል? ለምንድን ነው

ወደ ገፅ 30 ዞሯል



ቃልኪዳን ኃይሉ

# ብሉይ ወይም ሐዲስ ኪዳን?

ድሮ ገና ክርስትናው በተጀመረበት ዘመን ሁለት ጎራዎች ነበሩ፤ አይሁድ ዘመም ክርስቲያኖች እና ‘ኖስቲኮች (gnostic) የተባሉ በሁለት ፅንፍ የቆሙ፤ በቃላት፣ በምግባር፣ በግብር፣ በአካሄድ፣ በአኗኗር፣ በአነዋወር የሚጠዛጠዙ፣ የሚተቻቹ፣ የሚጣሉ፣ የማይስማሙ::

አይሁድ ዘመም ክርስቲያን የሚባሉት ሐሳባቸው ልክ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት እንደ ነበረው ዘመን በኦሪት የታዘዘውን ነገር ሁሉ እንዳለ፣ አንዳች ሳይቀር፣ በክብር ሊፈጸም ይገባል ባዮች ነበሩ:: ክርስቶስ መጣ ተብሎ ስለምንድነው ያባታችን የሙሴ ሕግ የሚጣሰው ብለው ይቆረቆራሉ:: በወንጌል ስብከት እያመኑ ከአሕዛብ (ከጣኦት አምልኮ) ወደ ክርስትና የሚመለሱትን ሰዎች እንደ ኦሪቱ ልማድ ካልተገዛችሁ፤ ይህን ብሉ፤ ይህን አትብሉ የሚለውን በአጠቃላይ የሙሴን ሕግ ካልጠበቃችሁ፣ መዳን አትችሉም ባይ ነበሩ::

‘ኖስቲኮች የተባሉት ደግሞ በተቃራኒው ከእግዚአብሔር ለሙሴ የተሰጡትን መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስነት አካል እንኳ እስኪያስወጧቸው ድረስ ጠሏቸው:: የኦሪት ሕግ ከመጥላታቸው የተነሣ ቀዳሚት ሰንበትን (ቅዳሜ) እንኳ ይጾሙ ነበር:: የ‘ኖስቲኮች ዋና ምኞትና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ከአይሁዳዊነት ነጻ የሆነና የጸዳ “ክርስትና” ነበር:: በኦሪት የተነገሩት የመስዋእት፣ የጦርነት፣ ማኅበራዊና ግለሰባዊ ትእዛዛትን በዘመኑ የተፈጸሙት ነገሮች ከአሕዛብ ወደ ክርስትና ለሚመለሱት ሰዎች እንቅፋት የሚሆኑ እና ለኅሊናቸው የሚከብዱ፤ የማይመጥኑ ሸካራዎች፤ ጭካኔ የበዛባቸው ናቸው ብሎ ማሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ከማሰብ ዘለል ባለ ሁኔታ ብሉይ ኪዳንን እንዳለ ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ ፍላጎት ነበራቸው:: ይህ አስተሳሰብ ስንት ሺኅ ዓመት አስቆጥሮ ድጋሚ በሀገራችን መንፀባረቅ ጀምሯል::

አንዱ ሐዲስን እቀበላለሁ ሲል፤ ሌላው ደግሞ የለም እኔ ብሉይን እቀበላለሁ ብሎ ይነሣል:: ከዚያ በኋላ ምኑ ቅጡ? የሚመስላቸውን ይጨምራሉ፣ ይቀንሳሉ:: አንዱ ፅድቅ ነው ያለውን ሌላው ኩነኔ ነው ይላል፤ ከወዲህ የጣኦት ምስል ነው ሲል ከወዲያ ደግሞ የክብር መግለጫ መገለጫ ነው ይሉታል፤ ከዚህ ኀጢአት ነው፣ ነውር ነው፣ ለእግዚአብሔር አይገባውም ሲሉ፤ ከዚያ ደግሞ ይገባዋል፣ እንዴውም ያንስበታል ይላሉ:: እንደ ባቢሎን አናጢዎች መደማማጥ የለም፤ የሚሰሙት መስማት የሚፈልጉትን፤ የሚረዱት ለእነርሱ የሚመቻቸውን ብቻ ነው:: የአንዱ ወገን ትውፊት፣ ታሪክ፣ እውቀት፣ ቋንቋ እና አስተምህሮ ለሌላኛው ከቶ አይዋጥም:: አንዱ የራሱ የሆነ ነገር ባይኖረው ይፈጥራል እንጂ ፈጽሞ ከሌላኛው መመቻመች፣ መስማማት አልፈጠረበትም::

ሁሉም ፅንፈኛ ሁሉም ባለጥግ ነው:: የሚሰማው ጆሮ የሚሻ እንጂ የሚያዳምጥ፣ የሚያስውል ኅሊና ያልፈጠረበት ነው:: ለ‘ኖስቲኮች ብሉይ አርጅታለች፤ ብሉይ ዘመኑን ያልዋጀች ኋላ ቀር፤ በድሮ በሬ የምታርስ ነች:: ስለዚህም ማደስ ይፈልጋሉ:: እደሳው ደግሞ አይሁድነትን ፍቆ ሙሉ ለሙሉ ሐዲስን ማንገሥ ነው፤ መንገዱን ብሉይ ጠርጋለች፤ ግን ምንም ዓይነት እውቅናም ሆነ ቦታ ‘ኖስቲኮች ሊሰጡ አልፈቀዱም::

ሐዲሶች ብሉይን ካልታደሰ ብለው ተነሥተዋል:: ብሉዮችም እዚህም ቤት እሳት አለ ብለው ቆመዋል፤ ‘ኖስቲኮች አሽቀንጥረው የጣሉትን ብሉይንና አስተምህሮውን አይሁድ ዘመሞች ማንነታችን፣ እኛነታችን ብለው ፈለጉት፤ በተቃራኒው ደግሞ የ‘ኖስቲኮችን ማንነት ጠሉት፤ ከዚያም እኛ አንታደሰም፤ ከፈለጋችሁ እናድሳችሁ አሉ:: የተቆመለት ዓላማ ቀርቶ፣ በእልህ ዳርና ዳር ቆመው ይጠዛጠዛሉ::

ብሉይ ኪዳን የራሱ የሆነ ትምህርት አለው:: በብሉይ ውስጥ ያሉት ታሪኮችና ገድሎች በራሳቸው የራሳቸው እውቀት፣ አስተምህሮ፣ የሰዎች መውደቅና መነሣትን ያሳያሉ:: እንደ ‘ኖስቲኮች አመለካከት ግን የሰውን አእምሮ የሚያሻክሩ፤ ከማመን ወደ አለማመን የሚያመጡ ናቸው:: ብሉይ ኪዳን ላይ ሰዎች የሠሩት ገድልም ሆነ ውድቀት በሐዲስ ተደግሟል፣ ተፈጽሟል::፡ እንዴውም ሐዲስ ኪዳን በራሱ ከኦሪት የሚያስማማ እንጂ የሚጣረስ አይደለም:: ኢየሱስ ራሱ ‹‹እኔ ኦሪትን ልሽር ሳይሆን ላጸና፣ ልፈፅም ነው የመጣሁት›› ነው ያለው::

ሐዲስና ብሉይ በፍጹም የሐሳብ መጣረስና ግጭት የለባቸውም:: ብሉይ ለሐዲስ ጥርጊያ መንገድ ነው:: ብሉይ አትግደል ያለ እንደ ሆነ ሐዲስ አትቆጣ ይላል፤ ብሉይ ወዳጅህን እንደ ራስህ ውደድ ያለ እንደ ሆነ ሐዲስ ጠላትህን ውደድ ይላል፤ ብሉይ ዝሙት የከለከለ እንደ ሆነ ሐዲስ ጭራሽ አትመኝ ይላል፤ ብሉይ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደደው ካለህ ሐዲስ ግራህን ቢመታህ ቀኝህን ስጠው ይልሀል… ብሉይ ከሐዲስ እርስ በርስ አይጣረስም:: ይልቁንም የሚስማሙ፣ የሚግባቡ እና የማይጣረሱ ናቸው::

አንድ ተብሎ አይደል ሁለት የሚባለው፤ ብሉይ ተነብቦ ነው ወደ ሐዲስ የሚዘለቀው፤ ወጣትነት ታልፎ ነው ጎልማሳ፣ እንዲሁም እርጅና የዕድሜ እርከን ላይ የሚደረሰው:: ፊተኛና ኋለኛ፤ አዲስና መጤ፤ ልጅ አዋቂ፤ ያለፈ ያሁን፤ የሀገር ልጅ የሌላ ሀገር ሰው፤ የድሮ የዘንድሮ ብሎ መከፋፈል ምንድነው? መነጋገር፣ መወያየት፣ መደማመጥ፣ መስማማት የጸብ፣ የችግር፣ የጭንቀት፣ ያለመቻቻል፣ ያለመግባባት፣ ያለመማጠን መፍቻ ቁልፍ ነው::

አይሁድ ዘመም ክርስቲያኖች ሆኑ ‘ኖስቲኮች ቁጭ ብለው ቢነጋገሩ፤ የቱ ጋር ነው ችግሩ ቢሉ፤ ከመሠረታችን ውጭ የተቀረው ምኑ ይስተካከል ቢሉ ኖሮ ጉዳዩ ከወተት የነጣ፤ ከበረዶ የነጻ ነበር:: ግን እንዲህ ጽንፍ ይዞ መለያየቱ፤ ሩቅ ለሩቅ መተቻቸቱ፤ ከዛና ከዚህ መወራወሩ አላማው መንፈሳዊነትን ይዞ መንፈስን ማገልገል፣ መገልገል አይደለም:: ከዚያ ይልቅ መንፈሳዊ ቦታ ላይ ግለሰብን ለማክበርና የግለሰብ ሐሳብ ለማስከበር የሚደረግ ሽኩቻ ነው:: በጭቅጭቁ፤ በመለያየቱ፣ በመነቃቀፉ መኻል የሚጠቀሙ ሰዎች፤ ዝነኛ የሚሆኑ ግለሰቦች ድርጅቶች፣ ማኅበሮች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ ብሎጎችና ብሎገሮች፣ የተረሱ ልዩነቶች አሉ:: ፅንፍ ዓላማው ይህ ነው::

በጭቅጨቅ፣ በንትርክ፣ በንዝንዝ… መኻል በልቶ ማደር፤ ታውቆ መኖር፤ ታሪክ መጻፍ፤ ተፈርቶ መታየት አለ:: ፅንፍ ውስጥ ሆድና ሥልጣን ነው ያለው:: ወንበር፤ ሥልጣን፣ ቦታ፣ ጥቅም… ካለ መለያ ገልብጦ ‘ኖስቲኮች አይሁድ ዘመም፤ አይሁድ ዘመሙም ‘ኖስቲኮች የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም:: ብቻ ይመች፤ ብቻ አንድ ነገር ጠብ ይበል:: ካልሆነ ግን ወይ ፍንክች ያባ ቢለዋ ልጅ፤ የዛሬን ብለቅ ያንዘርዝረኛ ነው:: ጫፍና ጫፍ ይዞ መከፋፈል መለያየት ይቅር:: ሁሉም በሕጉ እና በሥርዓቱ ቢሆን መልካም ነው:: አለመግባባት ያለ እና የሚኖር ቢሆንም፤ ቁም-ነገሩ አለመግባባቱን፣ ችግሩን፣ መለያየቱን ወደ መግባባት፣ መስማማት፣ አለመለያየት ማምጣት ነው::

ሌላው ሀገር ይወቅልን ብሎ ገመናን ባደባባይ ማስጣት፤ ቡራ ከረዩ፤ ያዙኝ ልቀቁኝ፤ ፍቱ እሰሩኝ ማለት ራስን ለፈራጅ፣ ለጋዜጣ፣ ለመጽሔት፣ ለብሎግ፣ ለፌስቡክ መስጠት ነው:: ፈራጅ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ፌስቡክ፣ ብሎግ ደግሞ ይጠቀምባችኋል እንጂ አይጠቅማችሁም፤ ዓላማውን ያሳካባችኋል እንጂ ዓላማችሁን አያሳካልችሁም፤ ፈርዶ ለፈራጅ ይሳጣችኋል እንጂ አይፈርድላችሁም፤ ፍትሕ ማግኛ ዓላማ ማስረጫ ትሆናላችሁ እንጂ አላማችሁ ግቡን አይመታም:: ፈቃደኝነቱ ካለ መስማማት ይቻላል፤ ቀናነቱ ካለ ብሉይና ሐዲስ ተደምረው ነው መጻሕፍ ቅዱስ የተባለው:: አንዱ ለአንዱ ምስክር ነው፤ ብሉይ እንዲህ ይሆናል አለ፤ ሐዲስ ሆነ፣ ተፈጸመ አለ:: ስለዚህ የሚፈለገው የእናንተ ቀናነት ነው፤ የራሳችሁን ሀሳብ ከምታብላሉ ቃሉን ብታብላሉ፤ መገናኛውን እንጂ መለያየውን ባንፈልግ መልካም ነው::

መጣያ በሌላው ጉዳይ ከተጣለን በምን እንታረቃለን? አንዴ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሓቅ ስለመንፈሳዊነት ተጠይቀው እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹እኔ መንፈሳዊነትን በኩሬ ነው የምመስለው… እናንተ መንፈሳውያን ቀድማችሁ መጠጣት አለባችሁ፤ ከዚያ ሰው እናንተን… ነው የሚጠጣው፤ በፍቅር በመተባበር እና በመከባበር አርአያ ሁኑ::››



**ተስፋዬ ሲ.**
tes983398@gmail.com

# “እንደ-ራሴን እንደ መፍትሔ”

የፍትሐ ነገሥት አምስተኛ አንቀጽ ቁጥር አንድ መቶ ስልሳ አራት ትንሣኤ በዋለ ከሃያ አምስተኛው ቀን/በርክበ ካህናት ዕለት/ እና ከጥቅምት አስራ ሁለት ቀን ጀምሮ በዓመት ሁለት ጊዜ የጳጳሳት ጉባኤ ይካሄድ ይላል። ይህ የጳጳሳት ጉባኤ መንፈስ ቅዱስ እየራቀው በከፍተኛ ጭቅጭቅና እሰጥ አገባ የተሞላ መሆን ከጀመረ በርካታ ዓመታትን አሳልፏል። በዘንድሮው ርክበ ካህናት ተጀምሮ ከጥቂት ቀናት በፊት የተጠናቀቀው የጳጳሳቱ ጉባኤም እንደተለመደው በንትርክ ያለፈና የእግዚአብሔር እርዳታ የተጠየቀበት ሳይሆን የመንግሥት እገዛና ድጋፍ በግልጽ የተለመነበት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳይ ላይ መንግሥት ምክሩን የለገሰበት ሆኖ አልፏል።

ቤተ ክርስቲያን ላይ አሁን እንደሆነባት ያለ ክፉ ነገር መቼም አጋጥሟት አያውቅም። ለዓለማዊም ለመንፈሳዊም ሕግ ተገዢ ያልሆኑ ፓትርያርኮች በሚያሳዩት እንቢተኝነት ዘንድሮም አባቶቿ እርስ በእርስ መስማማት አቅቷቸው ቄሳርን ሸማግሌ አድርገው ተሸማገሉ አሉ። ዓለምን በመንፈሳዊም በዓለማዊም ጥበባቸው የሚመሩ አባቶች መፍለቂያ የሆነች ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿ ዛሬ ላይ በጎቼን ማስማራትና መምራት ስላቃተኝ ቄሳር ሆይ እባክህ ጥበቡን ግለጽልኝ ብለው ተማጸኑ ተባለ። ለሕገ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ለእኒ ቄሳር ፊትና ቃል መገዛትን መምረጥ የመንፈሳዊ መሪዎቻችን የሞራል ልዕልና ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ማሳያ ነው።

ስድስተኛው ፓትርያርክ በሚፈጥሯቸውና በፈጠሯቸው ሕገ-ወጥ ተግባራት የተነሳ መንግሥትን ለሽምጋይነት ከመጥራቱ በተጨማሪ በርሳቸው አማካኝነት ለተፈጠሩ ስህተቶች ማረቂያና ወደፊት ለሚከሰቱ ሕገ-ወጥ ተግባራት መጠበቂያ ይሆን ዘንድ የዘንድሮው የጳጳሳቱ ጉባኤ እንደ-ራሴን መሾም እንደመፍትሔ አስቀምጦ አልፏል። እንደ-ራሴነት ‹‹ፓትርያርኩን የሚረዳ የሚያግዝ›› የሚል የጋራ አዎንታዊ ትርጉም ቢኖረውም በፓትርያርክ አባ ማትያስ ግን ፈጽሞ አልተወደደም። ርሳቸውን የሚተካ ከእርሳቸው በላይ የሆነ አካል ተደርጎ ነው የተወሰደው፡፡ በጉባኤው ላይም በዋናነት የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የተፈለገው በዚህ ጉዳይ ላይ ነው።

ሕገ ቤተ ክርስቲያን ስለ እንደ-ራሴነትና ስለ እንደ-ራሴ ምንም ባይልም ቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትርያርኮቿን በተመለከተ ችግሮች ሲያጋጥሟት እንደ መፍትሔ እንደ-ራሴን ትሾማለች። እንደ-ራሴነት በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ በተለያየ ጊዜና ወቅት ልዩ ልዩ መልኮችን በመያዝ ተስተናግዷል። የመጀመሪያው እንደ-ራሴነት የተሰጠው ለአቡነ ቴዎፍሎስ ሲሆኑ የፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ እንደ-ራሴ ሆነው ነበር የተሾሙት፡፡ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ በተደጋጋሚ ከንጉሡ ጋር ባለመስማማት መንበራቸውን ጥለው ወደ ደብረ ሊባኖስ መሄዳቸው እና የጤናቸው ሁኔታ ነበር በወቅቱ እንደ-ራሴ እንዲሾምላቸው ምክንያት የሆነው። ሌላኛው እንደ-ራሴ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልእ ሲሆኑ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሐይማኖት ከገዳም በመምጣታቸውና በገዳማዊ ባሕሪያቸው ምክንያት ለዓለም አቀፉ ግንኙነት ባዳ ስለሆኑ በዚህ ጉዳይ ርሳቸውን እንዲረዱ ነበር የተሾሙት። አምስተኛው ፓትርያርክም አባ ጳውሎስ ወደ መንበራቸው በመጡ ሰሞን የአገሩን ሁኔታ እንዲያላምዷቸው በጉባኤ ተወስኖም ባይሆን ሊቀ ጳጳስ አባ ባስልዮስ የተሰኙ አባት እንደ-ራሴ ሆነዋቸው ነበር። ባለፉት ፓትርያርኮች እንደታየው ከጤናና ከአለም አቀፍ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ለፓትርያርኮቻችን እንደ-ራሴ ሲሾም ቆይቷል።

በስድስተኛው ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ላይ እንደ-ራሴ መሾም ያስፈለገው ከምን አኳያ ነው? ከጤናቸው ጋር በተያያዘ ነው? ለአገሪቷ ሆነ ለዓለም አቀፉ ጉዳይ እንግዳ ስለሆኑ አስተዳደሩን ስላልቻሉበት ነው? ወይስ ከአባቶች ጋር ተስማምተው መስራት ስላልሆነላቸው እና ሕገ ቤተ ክርስቲያኑን ስላላከበሩ ነው? የወቅቱ ፓትርያርክ ላይ ለምን እንደ-ራሴ ጳጳስ መሾም አስፈለገ የሚለውን ለመመለስ ያለፉት የፓትርያርኩን ሦስት ዓመታት መለስ ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ለፓትርያርኩ እንደ-ራሴ ጳጳስ የሚያሾም ይህን ያህል የከፋ የሚባል የጤና እክል አልገጠማቸውም። አባ ማትያስ ከሦስት አስርት አመታት በላይ ከኢትዮጵያ ውጭ በመቆየታቸው ለቤተክህነቱ ፖለቲካና ቢሮክራሲ ባዕድ ናቸው። የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብ አቅም መጨመር ተከትሎም ለመጣው ሙስናና ብልሹ አሠራር እንዲሁም ፖለቲካው ለወለደው የከፋ ዘረኝነትም እንግዳ ናቸው። አባ ማትያስ ባልነበሩባቸው ዓመታት በተከሰቱ በርካታ አዳዲስ አሉታዊ ጉዳዮች ላይ የርሳቸው በተግባር የተፈተነ በዓለማዊ ዕውቀትም የታገዘ የአስተዳደር ብቃት አለመኖር፤ ቤተ ክህነቱን አይን ላወጣ ፖለቲካዊ ቅኝ ተገዢነት ከመዳረጉ በላይ መንፈሳዊነትን ከድጡ ወደ ማጡ ከቶታል።

ፓትርያርኩ የዚህ ዓይነት ቀውስ ውስጥ እንዴት ገቡ? ለምንስ ላለፉት ሦስት ዓመታት የቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ አጀንዳ ሆኑ? ለዚህ ጥያቄ ከላይ ያነሳኋቸው ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው በዙሪያቸው የከበቧቸው አማካሪዎቻቸው በተለይ ደግሞ ሕገ ወጥ የሆነውን የፓትርያርኩን ልዩ ጽ/ቤት እየመራ የሚገኘው፤ ከብጹአን አባቶች፣ ከሕገ ቤተ ክርስቲያን፣ ከመመሪያና ከደንቦች ውጭ የተለየ ቀረቤታ ያለውና የፓትርያርኩም የቤተ ክህነቱም ኪሳራ እየሆነ የሚገኘው ልዩ ፀሐፊያቸው ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ለፈጠሩት ችግርና ቤተ ክህነቱ ለሚገኝበት የከፋ ሁኔታ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል (ለነገሩ ርሳቸውም ዘግይቶም ቢሆን የልዩ ፀሐፊያቸው ጉዳት የገባቸው ይመስላል፤ ለዚህም ይመስለኛል በቅርቡ እንደሚያነሱት ቃል የገቡት። ያንሱት አያንሱት በጥቂት ቀናት ውስጥ እናያለን)።

የአቡነ ማትያስ ችግር ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ተስማምቶ አለመስራት፣ ለሕገ ቤተ ክርስቲያን ለመመሪያዎችና ለደንቦች አለመገዛት፣ በጣት ከሚቆጠሩ ግለሰቦች ውጭ ከሌሎች ራሳቸውን አግልለውና ከልለው መኖር፣ እንደ አባት የልጆቻቸውን ችግር ቀረብ ብሎ አለማዳመጥና ከፍረጃ በፀዳ መንፈስ አለመቅረብ ይመስለኛል። በዚህም አለ በዚያ የጳጳሳቱ ጉባኤ ይህንና ሌሎች ችግሮቻቸውን በጥልቀት መርምሮ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ቤተ ክርስቲያኒቱን በብቃት መምራት ስላልቻሉ መፍትሔ ብሎ እንደ-ራሴ ጳጳስ/አጋዥና ረዳት/ እንዲሾምላቸው በመወሰን ደንብና መመሪያን የሚያዘጋጅ ኮሚቴ አዋቅሯል። እንደ-ራሴ መሾሙ ዘለቄታዊ መፍትሔ ያመጣል አያመጣም የሚለው በሂደት የሚታይ ቢሆንም በጊዜያዊነት ግን ፓትርያርኩን የቤተክህነቱ ኪሳራዎች ከሆኑት አማካሪዎቻቸው ይነጥላል፣ ምክራቸውና ውሏቸውም ከአቻዎቻቸው ጋር እንዲሆን ያደርጋል።

የእንደ-ራሴውን ጉዳይ በሚመለከት የተቋቋመው ኮሚቴም በሚያዘጋጀው መመሪያና ደንብ ላይ የሚሾመው እንደ-ራሴ ጳጳስ የእድሜ ልክ ከመሆን ይልቅ እንደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አሥኪያጅና የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ በጊዜ ገደብ ቢቀመጥ፣ ብሔሩ ላይ ሳይሆን ስብእናው እና የአስተዳደር ችሎታው ላይ ትኩረት ቢደረግ መልካም ነው።

ተመራጩ እንደ-ራሴ ሊቀጳጳስም ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነቱ በተለያየ መንገድ መስዋዕትነት የሚከፍል፣ የዘመኑን ፖለቲካዊ ጫናዎች መቋቋም የሚችል፣ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር እየመከረ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ማእከላዊነቱን የጠበቀ መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን፤ ዘረኝነትን፣ ሙስናንና ኑፋቄን የሚያስወግድ በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኒቱን ወደ ቀደመ ክብሯ መልሶ ዘመናት የሚያሻግር እንዲሆን የብዙዎች ምኞትና ሕልም ነው።

*ከጽዮን ምሕረት ለኢትዮጵያ*

# ‹‹አዋጅ... ከገፅ 9 የዞረ

**የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመከላከል ተብሎ የወጣው አዋጅ መካከል አንቀፅ 14 እና 15 በአነጋጋሪነታቸው ይጠቀሳሉ። አንቀፅ 14ን (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በወንጀል ህግ አንቀፅ 257 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ በህብረተሰቡ መካከል የፍርሃት ስሜት፣ አመጽ፣ ሁከት ወይም ግጭት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ ጽሁፍ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል፣ ድምጽ ወይም ማንኛውንም ሌላ ምስል በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት ያሰራጨ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።) እንመልከተው።**

አዋጁ ላይ መልሴን ከማስቀመጤ በፊት አዋጁ ለምን እንደወጣ የራሴን ምልከታ ላስቀምጥ:: በኦሮሚያ በተከሰተው ተቃውሞ ጊዜ የመንግሥት ተቋማት ድረ-ገፆች ‹‹ሀክ ተደርገዋል›› ተብሎ በኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ደብረፅዮን አማካኝነት በፓርላማ ሲነገር ነበር:: ከእሳቸው ንግግር በኋላ ነው ይህ አዋጅ ወጣ ተብሎ ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ መነጋገሪያ የነበረው::

ኢትዮጵያ ‘የኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅ’ አያስፈልጋትም ማለት አይቻልም:: ነገር ግን ማንን ዒላማ አድርገው ነው አዋጁን የሚያወጡት ብሎ መጠየቅ ይገባል:: የወጣው ግን የፀረ-ሽብር ሕግ ማን ላይ ነው ዒላማ ያደረገው? አንድን ባንክ በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካይነት ለመዝረፍ ለሚሞክሩ ሰዎች ይሄ አዋጅ ያስፈልጋል:: አዋጁንም የጠነሰሱት እንደዚህ ዓይነት ውጫዊ ዘራፊዎችን ለመከላከል በሚል ነው:: ነገር ግን መሀከል ላይ አንቀፅ 14ን ጣሉበት:: ሌላኛው የወንጀለኛ መቅጫው አንቀፅ 257 (መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር) ማለት ነው:: በንግግር፣ በሥዕል፣ ወይም በጽሑፍ አማካኝነት ሕዝብ ላይ ደረሰ የሚባለውን ሁከት የሚፈጥር ነገር ፍቺ ሊሰጠው የሚችለው በማነው? በእኔ አረዳድ አንቀፅ 14 በራሱ የሕዝብን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ነው::

ሌላው መነሳት ያለበት ነገር ‹‹ይሄ የኮምፒዩተር ወንጀል ነው፣ ይሄ እብሪተኛ ነው›› ብሎ የሚለየው የትኛው ገለልተኛ ተቋም ነው? የሚለው ነው:: ሆን ተብሎ የሶሻል ሚዲያ ተጠቃሚውን ለማጥቃት የወጣ አንቀፅ ነው:: ያልተመቻቸውን ጽሑፍ ‹‹እከሌ ሕዝብን ለመቀስቀስ፣ ለማሸበር ይህን ጽፏል›› ብለው ለመወንጀያነት ለመጠቀም ነው:: በጥቅሉ አንቀፅ 14 የሰብዓዊ መብት አክቲቪስቶች፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ አራማጆችን ታሳቢ አድርጎ የወጣ አንቀፅ ነው ብዬ አስባለሁ::

**አንቀፅ 15 የስፓም ኢ-ሜይሎችን ማሰራጨት**

የስፓም ኢ-ሜይሎችን ማሠራጨት የተለመደ ነው:: በእርግጠኝነት ይህ የሕግ አንቀፅ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የመልዕክቱ ዓይነት ታይቶ እንደሚሆን አልጠራጠርም:: ኢ-ሜይሉ ፖለቲካዊ ኪሳራ የሚያደርስ ከሆነ እና ያ ሰው ከምህዳሩ እንዲጠፋ ከታሰበ በዚህ አንቀፅ ተጠያቂ ያደርጉታል:: በርግጥ እኛ አገር ላይ ወንጀል የሚፈለግብህ ከተያዝክ በኋላ ነው:: የተቃውሞ ፖለቲካ መልዕክት እስካላስተላለፍክ ድረስ ይህን አንቀፅ ዞር ብለው ያዩታል ብዬ አላስብም:: [አንቀፅ 15/1 እንዲህ ይላል፡- ማንኛውም ሰው ምርትን ወይም አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ መልዕክቶችን በአንድ ጊዜ ወደ በርካታ የኢሜል አድራሻዎች ያሰራጨ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና በመቀጮ ወይም ወንጀሉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል::]

**የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. አቋምን የሚገልፁ ከሆነ 50 አይደለም 10,000 ስፓም ኢ-ሜይሎን ብታሰራጭ ልትከሰስ አትችልም እያልክ ነው? [በርግጥ ‹‹ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.ን ምረጡ›› ብለው ለብዙሐን ያለፍላጎታቸው የሚልኩ ሰዎች ይጠየቃሉ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ይመስላል።]**

በትክክል!!!

**ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. በሚመራት ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም የኮምፒዩተር ሥርዓት ተጠቃሚ ግለሰብ ጠንካራ ምስጢር ቁጥር (በቁጥር፣ በፊደልና በተለያዩ ልዩ ካራክተሮች የተቀናጀ) ቢኖረው፣ ፀረ-ቫይረሶችን ቶሎ ቶሎ እያደሰ ሥራ ላይ ቢያውል ወይም ሌሎች የጥንቃቄ አማራጮችን ቢጠቀም ከብርበራ ሊያመልጥ የሚችልበት ዕድል ሊኖረው ይችላል?**

‘ሃኪንግ ቲም’ የሚባል አንድ የጣሊያን ተቋም አለ:: የድርጅቱ ደንበኞች የተለያዩ አምባገነን መንግሥታት ሲሆኑ የአካውንት መበርበሪያ ፕሮግራሞችን ይሸጥላቸዋል:: እንደምታውቀው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማይቻል ነገር የለም:: የማይነበብ ዳታ (encrypted Data) ቢሆንም እንኳን የመስበሪያ መንገድ አይታጣለትም:: ኢትዮጵያ የዚህ ድርጅት (hacking team) አንዷ ደንበኛ መሆኗ በአንድ ወቅት በወጣ ዝርዝር ላይ ተጋልጧል:: መንግሥት ተቀጣሪ ባለሙያው የሚፈልገውን አካውንት መስበር (hacking) ካልቻለ ሚሊየን ዶላሮች በመክፈል ለውጪ አካል ሰጥቶ አካውንት ያስበረብራል:: የ‘ሃኪንግ ቲም’ ዳታ ቤዝ ተሰብሮ የደንበኞች ዝርዝር ከወጣ በኋላ ጭራሽ ‹‹ሊነበቡ የማይችሉ ጭብጦችን ሳይቀር እንዲነበቡ አደርጋለሁ›› በማለት ሥራቸውን ቀጥለዋል:: ይህ ለሰብዓዊ መብት አራማጆች አደጋ ነው፤ ለአምባገነኖች ደግሞ ትልቅ ጥቅም ይሰጣቸዋል::

**የፀረ-ሽብር ሕጉ በፀደቀ በቀናት ልዩነት ውስጥ እነ ውብሸት ታዬ፣ ርዕዮት ዓለሙና ሌሎቹም እንዲታሰሩ መደረጋቸው ይታወሳል። ‘የኮምፒዩተር ወንጀል አዋጅ’ መውጣትን ተከትሎ በቅርቡ ምን የሚፈጠር ይመስልሃል?**

እንዳልከው አንድ አዋጅ የሚያወጡት ከመሬት ተነስተው ሳይሆን ማጥቃት የሚፈልጉት ሰው ሲኖር ነው:: ለአንድ ሰው [ለአቶ ስዬ አብርሀ] ተብሎ በአንድ ቀን ‹‹ሙስና ዋስትና ያስከለክላል›› የሚል አዋጅ ያፀደቀች አገር ነች::

ስለዚህ ይህም የታወቀ ነው:: ኦሮሚያ ውስጥ ሕዝባዊ አመፅ አለ:: ብዙ ዜጋ ጋዜጠኞች ያንን አስመልክተው ብዙ መረጃዎችን ወደ ማኅበራዊ ሚዲያው እያመጡ ነው:: እነሱን ለመቆጣጠር ይሄ አዋጅ ያግዘናል ብለው አምነዋል:: ይሄ አዋጅ ወጥቷል ብሎ ብዙ ሰው ፍርሃት አድሮበት ራሱን ሳንሱር እንዲያደርግ የወጣ አዋጅ ነው:: ይሄን ‹‹ተላልፏል›› ያሉትን ደግሞ ለሌሎች ትምህርት ይሆናል ብለው ወደ እስር ቤት መላካቸው አይቀርም:: ከአዋጆች በኋላ ደግሞ ሁሌም የሚታሠሩ ሰዎች አይጠፉም:: ዮናታን ተስፋዬ (የቀድሞ የሰማያዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ) የታሰረው በፌስቡክ በጻፋቸው 11 ጽሑፎች መሆኑ መረሳት የለበትም:: እስር ቤት እያለሁም በሽብር ተከሰው የሚመጡ ሰዎች ፌስቡክ ላይ የጻፏቸው ‘ስታተስ አፕዴቶች’ ማስረጃ ሆነው ሲቀርቡባቸው ዓይቻለሁ::

**ከዚህ አዋጅ በኋላ ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ ምን ይፈጠራል ብለህ ታስባለህ? ‘የብዕር ሥም አርበኝነት’ ይነግስ ይሆን?**

ብዙ ሰዎች መፍራታቸው አይቀርም:: በብዕር ስም የሚደረግ እንቅስቃሴ ደስ አይለኝም፤ ዋጋውም ከፍ ያለ ነው ብዬ አላስብም:: ነገር ግን ዜጎች ራሳቸውን ከእስር መከላከል እስካለባቸው ድረስ አማራጭ አድርገው የሚወስዱት የብዕር ስም መጠቀምን ሊሆን ይችላል:: የብዕር ስም የሚጠቀሙ ሰዎች ኃላፊነት ይሰማቸዋል ብዬ አላስብም:: ዞን ዘጠኝ ውስጥ ብዕር ስም የማንጠቀመው ‹‹ኃላፊነት እንዲሰማን ያደርግም›› በሚል ነው::

አንድ ሕግ ወጣ ተብሎ መሸሽ አያስፈልግም:: ሽሽህ ማለት ሀሳባቸው ተሳካላቸው ማለት ነው:: የሰብዓዊ መብት አራማጆችም ሆኑ ጋዜጠኞች ኃላፊነት በተሰማው መንገድ ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፃቸውን መቀጠል አለባቸው ብዬ አስባለሁ፤ አዋጁ ምቾት ነሺ መሆኑን ሳልዘነጋ::

**ከእሥር መልስ ጠፍተሀል ምን እያደረክ ነው?**

[ሳቅ] ፍርድ ቤት እየተመላለስኩ ነው:: [ክሳቸው ያልተቋረጠ የዞን 9 ጦማሪያን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ለሰኔ 28 እንደቀጠራቸው ይታወቃል::] የፍርድ ሂደቱ ስላልተጠናቀቀ ነፃ ሆኖ ሕይወትን ለመቀጠል አስቸጋሪ ነው:: እስካሁን ራሴን የማስበው እንደታፈንኩ አድርጌ ነው:: ድርጊቶቼ ሁሉ መንግሥትን አስቀይሞት ሌላ ነገር ይከተልብኝ ይሆን እንዴ? እያልኩ እያሰብኩ ነው የምንቀሳቀሰው:: እዚህ አገር ከእሥር ስትፈታ እንዳትንቀሳቀስ በእግርህ ላይ ትልቅ አሎሎ ተደርጎ ነው፤ ይህም የአፈናው አንዱ ማሳያ ነው::

**የዞን ዘጠኝ ስብስብን መንግሥት አስሮ አጎላቸው (እውቅና ሰጣቸው) እንጂ ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ልጆች አልነበሩም የሚሉ አሉ። ምን ትላለህ?**

ትክክል ነው! በጣም የሚገርምም ጥያቄ ነው:: [ይስቃል] በቅንፍ ሳቀ ማለትህን እንዳትረሳ [ይኸው አረሳሁም!] ከሠራነው በላይ የማይመጣጠን መስዋዕትነት ከፍለናል:: ብዙ የእሥራት ስቃይ (ቶርቸር) ደርሶብናል:: ቤተሰቦቻችንም ተሰቃይተዋል:: ‹‹እዚህ አገር የሚታሠር ጠፍቶ ነው ወይ እኔ የታሰርኩት?›› ብዬ ራሴን ጠይቂያለሁ::

‹‹መንግሥት አሥሮ እውቅና ሰጣቸው›› የሚለው የሰው ውሳኔ ነው:: ከተፈታን በኋላ መንገድ ላይ ሰላም የሚለን በዝቷል ስለዚህ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.ን እናመሰግናለን:: [ኃይለኛ ሳቅ] ባንታሠር በሥራችን እንጎላ ነበር ብዬ አስባለሁ:: ‹‹ምን ሠሩና ነው?›› የሚሉ ሰዎችን እኔም እሰማለሁ::

# የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

## ከአምሐ መኮንን የሕግ ቢሮ ጋራ በመተባበር፤

## በሆቴል ሎቤሊያ ያዘጋጀው የዐውደ ጥናት ክንውን ሪፖርት

**የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከአምሐ መኮንንና አጋሮቹ የሕግ ቢሮ ጋራ በመተባበር፤ ‹‹በወንጀል ጉዳዮች የፍትሐዊ ዳኝነት መመዘኛዎች፤ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ተግባራዊ እይታ" በሚል ርዕስ የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት፣ በሚያዚያ 29 ቀን 2008 ዓ.ም ላይ በሆቴል ሎቤሊያ አካሂዶ ነበር። የዚህን ዐውደ ጥናት ክንውን ሪፖርት፣ የአምሐ መኮንንና አጋሮቹ የሕግ ቢሮ እንደሚከተለው አቅርቦታል። በዐውደ ጥናቱ ላይ ከአንድ በላይ ምሁራን የጥናት ጽሑፎቻቸውን አቅርበዋል፡፡ ለዛሬ የምናቀርበው የአቶ ጌታሁንን የጥናት ጽሑፍ ነው፡፡**

ዐውደ ጥናቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የፍትሓዊ ዳኝነት አሰጣጥ ሂደት በጣም ቁልፍና የመጨረሻውን ውጤት የመወሰን አቅም ካላቸው አንዱ መሆኑን የገለጹት አቶ ጌታሁን፣ ወደ ርዕሰ-ጉዳያቸው ከመግባታቸው በፊት ስለ ሰብዓዊ መብቶች መግቢያ ነጥቦችን ሰንዝረዋል፡፡ የሚዛናዊ ዳኝነትን ሕገ-ፍልስፍና (Jurisprudence) እንደሚያብራሩ አስረድተዋል፤ ሚዛናዊ ዳኝነት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ሰፊ፣ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለውና ዝርዝር ፅንሰ-ሐሳብ ነው በማለት፤ እነዚህ መመዘኛዎች (Standards) በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ያሉበትን ደረጃ ለመፈተሽ ሕገ-ፍልስፍናውን በሚገባ መረዳት እንደሚገባ ለተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

የፍትሓዊ የወንጀል ዳኝነት መመዘኛዎችን በሚመለከት በአፍረካ ያለው ሥርዓት ውስንነቶች ያሉበት ሲሆን፤ የአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤቶች ግን የዳበረ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡ የሚዛናዊ ዳኝነት ችግሮች ደግሞ አፍሪካ ውስጥ በብዛት የሚስተዋሉና የዳበረ ሕገ-ፍልስፍና የሌለበት ቢሆንም፤ ትንሽ የማይባሉ መሻሻሎች እየተመዘገቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሰብዓዊ መብት ጥበቃን ስንመለከትም ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ ሥርዓቱን ማየት፤ ጠቃሚ ልምዶችን ለማግኘትና በሀገራችን ያለው ነባሪዊ ሁኔታ ከዓለም አቀፋዊ መመዘኛው እንዲጣጣም መደረግ ያለባቸውን ተግባራት ለመለየት ይጠቅማል ብለዋል፡፡

የሰብዓዊ መብት ሥርዓትን ስንመለከት፤ ሁልጊዜም ቢሆን አራት ነገሮችን ከግምት ማስገባት ይገባል፡፡ የመጀመሪያው በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ያለው የፖሊሲ ማዕቀፍ፤ ሁለተኛው በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፍ መሰረት የሚወጡ ህጎች፤ ሶስተኛው ፖሊሲውን እና ህጉን ለማስፈፀም የተደራጁ ተቋማትን ለዚህ ሥራ ያላቸው ብቃት እና ዝግጁነት፤ የመጨረሻው ደግሞ በተግባር እየተሠራ ያለው ሥራ ነው፡፡ እነዚህን ተመልክተን ትክክለኛውን የሰብዓዊ ሥርዓት ምስል ማግኘት እንቻላለን፡፡ የሀገራችንን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር መመልከት ካለብን ዓለም አቀፋዊ ሥርዓቱንና ህገ-ፍልስፍናውን፤ ሀገራችን ያለውን የፖሊሲ፣ የሕግ፣ የተቋማትና ተግባራዊ ሁኔታ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

የሕግ አገዛዝ (rule of Law) በሕግ ከመገዛት (rule by law) የሚለይ መሆኑን ሲያብራሩ፤ ህጎቻችን ይህ ቀረሽ ባይሆኑም፣ ተግባራዊነታቸው ግን አጠያያቂ ነው፡፡ በአጠቃላይም የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓት በአንድ ሀገር ውስጥ የወንጀል ፖሊሲ ሕግና ተቋማትን እንዲሁም የተቋማቱን ሥራ እንቅስቃሴ ያጠቃልላል፡፡ እንደ መግቢያም ሰብዓዊ መብቶች ለሰው ልጆች የተሰጡ (Entitlements of human beings) ሲሆኑ፤ የሰው ልጆች ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ የሚጎናፀፏቸውና ልዩ ጥበቃ የሚሹ ናቸው ብለዋል፡፡

የሰብዓዊ መብት መገለጫዎችም ሁሉን አቀፍ እንዲሁም ለሁሉም በእኩልነት ተግባራዊ መሆናቸው የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የሁሉም የሰው ልጆች የጋራ ታሪክ መሆኑን፤ የባሪያ ንግድና የጅምላ ጭፍጨፋ የተፈጸመባቸውን ጊዜያት አስታውሰዋል፡፡ እነዚህን ጥሰቶች ለማረምና መንግሥታት አዎንታዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው አብራርተው፣ በአሁኑ ሰዓት የሰብዓዊ መብቶች ሰፊ የሕግ ማዕቀፍ ያላቸው ሲሆኑ፤ ከሰብዓዊ መብት ፅንስ-ሀሳብ ሦስት ደረጃዎች፣ ኖርማቲቭ ስታንዳርድ (Normative Standard) ማስቀመጥ የመጀመርያው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ የአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ፕሮቶኮል ግለሰቦች በግልም አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን ሲገልጽ፣ ይህን ግን ተግባራዊ ለማድረግ የአፍሪካ መንግስታት ዜጎቻቸው ይህንን አቤቱታ ለማቅረብ ይችላሉ የሚል ስምምነት ማስቀመጥ (Deposit) ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁንና እስካሁን ድረስ በአህጉር ደረጃ ከ55 የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ሰባቱ ብቻ ይህንን ስምምነት አስቀምጠዋል፡፡ ኢትዮጵያ ፕሮቶኮሉን አልፈረመችም፡፡ የአፍራካ ኅብረት ማቋቋሚያ ስምምነትን ስንመለከት ግን የኅብረቱ ዋና ዋና መርሕ ከሚባሉት የሕግ-የበላይነት፣ ተጠያቂነት እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ እነዚህ በአጠቃላይ መርህ የማስቀመጥ (Norm Setting) ሥራዎች መሆናቸውን እንረዳለን ብለዋል፡፡

ሁለተኛው የተቋማት ግንባታ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱ ተቋማት አሉ፤ በአህጉር ደረጃም ሆነ በሀገር ደረጃ ተቋቁመዋል፡፡ ሶስተኛውና አስቸጋሪው ተግባራዊነቱ ነው፡፡ የተዘበራረቁ ተሞክሮዎች አሉ፡፡ ለአብነትም አንድ ዛምቢያዊ ፕሮፌሰር ያሉትን ሲጠቅሱ፤ ‹‹የአፍሪካ መንግስታት አፍሪካዊ ከሆኑ ስምምነቶች ይልቅ፤ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ለመፈረም ይፈጥናሉ፤ የፈረሟቸውን ስምምነቶች ግን ተግባራዊ አያደርጉም፡፡›› ይላሉ ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት በተመለከተ፤ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችን፣ በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ስቃይን (Torture) ለማስወገድ የወጣውን ስምምነት፣ የአፍሪካ ኮሚሽን ቻርተርን እና የመሳሰሉትን ሕግጋት በሀገራችን የተሰጣቸውን ዋጋ (Value) ማየት ይገባናል ብለዋል፡፡ ፍርድ ቤቶቻችንና አስፈፃሚው አካል እነዚህን ህጎች አውቀው እየተረጎሟቸውና እያስፈፀሟቸው ነው? የሚለው አጠያያቂ ነውም ብለዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በአህጉር ደረጃ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች እድገት ስንመለከት፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር፣ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፓለቲካ መብቶች ስምምነትን፣ የሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችና ◿

በአፍሪካ ደረጃም የአፍሪካ የሰዎችና ሰብዓዊ መብቶች ቻርተር ይገኙበታል፡፡ ሀገራችንም ለፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ነክ ለሆኑ ስምምነቶች መከበር መንግሥት ኀላፊነት ያለበት ሲሆን፤ በአጠቃላይ ስብዓዊ መብቶች የተለያዩ ክፍፍሎች ማለትም የግልና የቡድን፣ የሲቪልና የፖለቲካ፣ የማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ብለን መከፋፈል እንችላለን ብለዋል፡፡

ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር በመርህ ደረጃ የመንግስት ኀላፊነት ሲሆን፤ ዜጎችም የራሳቸው አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ይሁንና መንግስት በዋናነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ተቋማትን ማደራጀት፣ ሕግና ሥርዓት ማስከበርና ሚዛናዊ የሆነ የፍትህ ሥርዓት መፍጠር፣ መብቶችን ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ ህገ-መንግስቱም ይህንን ያስቀምጣል፡፡ ሕግና ሥርዓት ማስከበር የመንግስት ኃላፊነት ሲሆን፤ መንግስት ይህንን ሲያደርግ በተለይ ሰብዓዊ መብቶችን በሚያከብር መልኩ መሆን እንዳለበትና ይህንን የሕግ ማስከበር ሥራ እንደ ሽፋን በማድረግ የሚፋጸሙ የመብት ጥሰቶች ተገቢነት የሌላቸው መሆናቸውን የሰሜን አየርላንድን ተሞክሮ በመጥቀስ አስረድተዋል፡፡

በወንጀል የሚጠረጠርን ሰው የምንዳኝበት ሥርዓትም ተገማች፣ ግልፅ፣ የተፃፈ፣ ተቀባይነት ባለው የሕግ ሥርዓት የሚመራ ሊሆን ይገባል፡፡ የአፍሪካ ሀገራትም የሚዛናዊ ዳኝነት ስርዓታቸው ችግር ያለበት ነው፡፡ እንደ ማሳያም የቀድሞውን የናይጀሪያ ፕሬዚዳንት ስለ ዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ተጠይቀው የአፍሪካ ሀገራት ስለ ተቋሙ የተዛባ አመለካከት ያላቸው ቢሆንም የመንግስት ባለስልጣናትን ተጠያቂነት ለማምጣት ጠቃሚ መሆኑን አስረድተዋል ብለዋል፡፡ የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱን ተገማችና ተዓማኒነት ያለው ለማድረግ ተቋማቱ ያለውን አመለካከት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ሚዛናዊ ዳኝነት ስለተከሳሽነትና ተጠርጣሪ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ተአማኒነት ያለው የፍትህ ሥርዓት መገንባትን ይጠይቃል፡፡ አጥፊ የሚጠየቅበትና ንፁህ ሰው ያለ አግባብ የማይቀጣበትን ሥርዓት መዘርጋት ይጠይቃል፡፡ ይህ ነው የሚዛናዊነቱ መገለጫ፡፡ ይህም በሕግ የሚያምን ማህበረሰብን ለመገንባት ይጠቅማል፡፡ ለወንጀል ፍትህ አስተዳደርና ለዴሞክራሲ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ከክርክር በፊት (pre-trial)፣ በክርክር ሂደት (during trail) እና ከክርክር በኃላ (post- trial) የተጠርጣሪነት ቃልን ከመስጠት ጀምሮ እስከ ጥፋተኝነት ውሳኔ ድረስ ሚዛናዊ ዳኝነት ሊጠብቅ ይገዋል፡፡ በጥቅሉ የሚዛናዊ ዳኝነት የመጫወቻ ሜዳውን ማስተካከልን ይጠይቃል፡፡

የሚዛናዊ ዳኝነት አንዱ መገለጫ ተከሳሹ ንፅህናውን እንዲያስረዳ ሳይጠበቅ ንፁህ አይደለህም ብሎ የሚከራከር አካል እንዲያስረዳ ማድረግን ሲጠይቅ፣ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከክርክር በፊት የሚደረጉ ነፃነትን የማሳጣት ሂደቶች (pre-trial detention) ማስወገድ ወደማይቻልበት ዝቅተኛ ደረጃ (to a level that is unavoidable) ማድረስ የሚገባ ይሆናል፡፡ ተጠርጣሪን ከማሰር ሌላ አማራጮችን መጠቀም የዚህ ነጥብ መገለጫ ነው፡፡ ይህም በዋስትና መልቀቅን፣ የይግባኝ መብትን ማክበርን ይጠይቃል፡፡ በበቂና ከዚያም በላይ ምክንያቶች ለትክክለኛ ፍትህ ካላስፈለገ በስተቀር የተጠርጣሪ ዋስትናን መንፈግ ተገቢነት አይኖረውም፡፡

ሌላኛው የሚዛናዊ የወንጀል ፍትህ አሰጣጥ መመዘኛ በራስ ላይ አለመመስከር ሲሆን ከሳሽ ጠንካራ ማስረጃዎችን ከተከሳሽ ቃል ውጭ ባለ መልኩ ማስረዳት ይገባዋል፡፡ ይህም ከተከሳሽነት የእምነት ቃል ውጭ ባሉ ማስረጃዎች ላይ በመመስረት አጥፊዎችን ተገቢ ቅጣት መስጠት ይገባል ከሚል መነሻ የመነጨ ነው፡፡ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓቱን ተገማች ከምናደርግባቸው መንገዶች አንዱ የክርክር ሂደቱን በተቻለ መጠን እንዳይንዛዛ ማድረግ ሲሆን አላስፈላጊ ትዕዛዞችንና የመሳሰሉትን ከግምት ማስገባት ይገባል፡፡ እንደ ማሳያ ለአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በቀረበ አንድ ጉዳይ አንድ ተጠርጣሪ ክስ (charge) ሳይደርሰው ለሁለት አመት ታስሮ ይህ ምክንያታዊ ያልሆነ ማጓተት (un reasonable delay) ነው ያለው ሲሆን ምንም አይነት መነሻ ምክንያት (prima facia evidence) የሌለው ከሆነ ደግሞ ጊዜው አጭር ቢሆንም እንኳ ተቀባይነት የለውም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠርጣሪ ራሱን ለመጠበቅ (to defend himself) የሕግ ባለሙያ ድጋፍ ማግኘት፣ በመረጠው ጠበቃ በመንግስት ወጪ መደረግ አለበት የሚል ሲሆን፣ በአውሮፓና በአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ቻርተሮች ላይ አንድ ተጠርጣሪ በአንድ የወንጀል ጉዳይ ከተጠረጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከጠበቃ ጋር የመመካከር መብት ያለው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ እንደ ምሳሌም በአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት በሰሜን አየርላንድ 48 ሰዓት ከጠበቃ ጋር ያልተገናኘ ተጠርጣሪ በጠበቃ የመታገዝና የሚዛናዊ ዳኝነት መመዘኛ የሚጋፋ ነው የሚል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

የዓቃቤ ሕግ ክስ ግልፅና የማያሻማ፣ የተጠረጠረበትን የወንጀል ድርጊት ማቋቋሚያዎች የሚያሳይ ሆኖ መዘጋጀቱ ለተጠርጣሪው የመከላከል መብትን ለማስከበር ይጠቅማል፡፡ ግልፅ ችሎት ሌላው መመዘኛ ነው፡፡ በዚህም ሚዲያዎችና ህዝብ ታዳሚ እንዲሆኑ ዳኛው ችሎት እየዳኘ ራሱን ችሎት ላይ እንዲቀመጥ የሚያደርግ አሰራር ነው፡፡ ህገ-ፍልስፍናውን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ቻርተሮች በሰፈረው መልኩ የሚሰጠው ብያኔዎችና የዓለም አቀፍ አህጉር አቀፍ ሰብአዊ መብት ተቋማትና ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ብያኔዎችና ህገ-ፍልስፍናዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የፍርድ ቤቶች ነፃነትና ገለልተኝነት በሚመለከት መንግስት የዳኝነት ስልጣንን በየጊዜው በሚያወጣቸው ህጎች በመሸራረፍ ለአስፈፃሚውና ለከፊል ዳኝነት (quasi judicial) አካላት መስጠቱ የፍርድ ቤቶችን ገለልተኛነት ይጋፋል የሚሉ ምሁራን አሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎችም በማናቸውም መልኩ በሕግ አውጪውና አስፈፃሚ በኩል መከበር ይኖርባቸዋል፡፡

ነፃ የሕግ ድጋፍን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚያስገድዱት ጉዳዩና በተለይ የነፃ አገልግሎት ሥራ ከእያንዳንዱ ጠበቃ የሚጠበቅ ከመሆኑ አንፃር፤ የሙያ ማህበራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የፍርድ ቤቶችን ገለልተኛነት በሚመለከት፣ የአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የአፍሪካ መንግስታት በየጊዜው የዳኝነት ሥልጣንን በተለያዩ ህጎች እየቀነጫጨቡ ለአስፈፃሚው ተቋም መስጠታቸው የዳኝነት ነፃነትን ይገፋል የሚል አቋም ወስዷል፡፡

በኢትዮጵያ በጣም ልምድና ብቃት ያላቸው የሕግ ባለሙያዎች እያሉ ነገር ግን አማካሪዎች ከውጭ ሀገር መጋበዙ ሙያውን እንዲቀጭጭ አድርጎታል፡፡ የፌዴራል የፍትህ ተቋማት በጋራ ያወጡት የለውጥ ሠነድ በቢፒአር ያለውን ነባራዊ ሁኔታ (AS IS) እና መሆን የሚገባውን (TO BE) በሚመለከት የተሠሩ ሥራዎች አሉ፡፡ ለውጡን ስናየው ግን አዝጋሚ ነው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ሙከራዎች ቢኖሩም በአንፃሩ ግን የሚሰጡ ውሳኔዎችን ስናይ በየጊዜው እየጨመረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከተለመደው የዳኝነት ሂደት በተጨማሪ መሻሻል ይታያል፡፡ ጠበቆችም በክርክራቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በመጥቀስ ሲከራከሩ ፍ/ቤቶች በዚሁ አግባብ መወሰን የተጀመረ ሲሆን፤ የቅጣት አወሳሰን መመሪያው መዘጋጀቱ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ላይ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

የክስ ቻርጅን በሚመለከት የግልፅነት፣ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችን አሟልቶ ያለማቅረብና የተንዛዛና ቴክኒካል ቃላት የበዙበት ክስ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ ተከሳሾችም ከአቃቤ ሕግ ጋራ ተከራክረው ሚዛናዊ ዳኝነትን ለማግኘትና ተነፃፃሪ መረጃን የማግኘት ሃይላቸውን ስናይ አስቸጋሪ ነው፡፡ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮም በሰውም ሆነ በማቴሪያል በሚገባ ያልተደራጀ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምንም እንኳ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፀደቀ የነፃ ሕግ ድጋፍ ስትራቴጂ ቢኖርም አተገባበሩ ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

ገለልተገኛ የሆኑ የቁጥጥር ተቋማት (Independent monitoring institutions) ደካማ መሆንም ለፍትህ ሥርዓቱ አለመጠናከር እንደ ምክንያትነት ይወሰዳሉ፡፡ ለምሳሌ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሲቋቋም በርካታ ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት ወስደው የተሳተፉ ሲሆን፤ የነበረው ተስፋ እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ያለውን አፈፃጸም ስናይ ግን ደካማ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሙያ ማህበራት አስተዋፅኦም እንዲሁ ደካማ ደረጃ ላይ ነው ያለው፡፡ በተግባር በወንጀል ፍትህ ሥርዓት ሂደቱም በተጠራጣሪው የእምነት ቃል ላይ የተንጠለጠለ መሆኑን ማስረጃን ሙያዊ ብቃት፣ ታክቲክ እና ቴክኒክ ተጠቅሞ የማሰባሰብና ሰብዓዊ መብትን ያከበረ የምርምራ ሂደት ላይ ባመዘነ መልኩ የሚሰበሰብ ያለመሆኑ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

(ይቀጥላል፡፡)

**‹‹የአፍሪካ መንግስታት አፍሪካዊ ከሆኑ ስምምነቶች ይልቅ፤ ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ለመፈረም ይፈጥናሉ፤ የፈረሟቸውን ስምምነቶች ግን ተግባራዊ አያደርጉም**



ደረጀ ታደሠ

# የቃና ቲቪ አብዮትና የፈጠረው ስጋት

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ አንባቢያን! እንዴት ናችሁ? የመዝናኛውስ መስክ እንዴት ይዟችኋል? ምርጫችሁ ፊልም፤ ድራማ አልያም ሙዚቃ ከሆነ ሀገርኛ አማራጮች በርከት ብለዋልና እንኳን ደስ ያላችሁ! በተለይ ሳምንታዊ ወይም ዕለታዊ በሆኑ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ዘና ማለትና አንዳች ቁም ነገር መቅሰም (ቁም ነገር ካለው ማለቴ ነው) ለምትወዱ አማራጩ ሰፊ ሆኗል፡፡

በርግጥም ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች በመላው ዓለም ሰፊ ተቀባይነት ያላቸውና እጅጉን ተወዳጅ የሆኑ መዝናኛዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት፤ ከሁለት በላይ የሆኑ የታሪክ ክፍሎችን ይዘው፤ በጠንካራ ምክንያትና ውጤት የተያያዙ ሴራዎችን አሰናስለው የሚቀርቡ በመሆናቸው ነው፡፡ የገፀ-ባህሪያቱን የዕለት ተዕለት የህይወት ውጣ ውረድ ልብ አንጠልጣይ በሆነ መንገድ ማቅረባቸው የተወዳጅነታቸው ሌላው ምስጢር ነው፡፡

ይህን መንደርደሪያ ሀሳብ በዚሁ ላብቃና ወደ ዋናው የጽሑፌ ሀሳብ ልለፍ፡፡ ይሄውም ከመጋቢት ወር አጋማሽ ጀምሮ በሰፊው መነጋገሪያ ሆኖ የከረመው የቃና የቴሌቪዥን እና የኪነ-ጥበብ ማኅበራት ተቃውሞ ነው፡፡ ‹‹ቃና ቲቪ›› እራሱን በማስተዋወቅ ለወራት ከዘለቀ በኋላ መጋቢት 26/2008 ዓ.ም የሚጀምራቸውን የውጭ ሀገራት ትርጉም ተከታታይ ፊልሞች ማስተዋወቁን ቀጠለ፡፡ በተባለው ቀንም ፊልሞቹን ማቅረብ ጀመረ፡፡

በአሁን ሰዓት ቃና ቲቪ የሚያቀርባቸው ተከታታይ ድራማዎች በአጠቃላይ ሰባት ያህል ሲሆኑ እነዚህም ከህንድ፣ ከብራዚል፣ ከጣልያን፣ ከቱርክና ከደቡብ ኮርያ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ድራማዎቹ በአማርኛ ተተርጉመው የገጸ-ባህሪያቱን የከንፈር እንቅስቃሴ በመከተል እና ቀጥተኛ የቋንቋው ተናጋሪ መስለው እንዲታዩ በማድረግ የቀረቡ ሲሆን ይሄውም በሙያው አጠራር ሊፕ ሲንክ ደቢንግ (Lip-sync dubbing) በመባል ይጠራል፡፡ ይህ አሰራር በመላው ዓለም የሚተገበርና ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው፡፡ ቃና ቲቪ ይህንኑ ለመስራት ስድስት ያህል የተደራጁ ኦውዲዮ ቪዡዋል ስቱዲዮዎችን ሰርቷል፡፡ ከዚህም ሌላ ከስልሳ በላይ የቴአትር ጥበባት ምሩቅ ባለሙያዎችንና ሌሎች በርካታ ባለሙያዎችን ቀጥሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ታዲያ በዚህ ሰፊ ዝግጅት ስራውን የጀመረው ቃና ቲቪ ከሚያቀርባቸው የውጭ ሀገራት ትርጉም ድራማዎች አንፃር (አልያም በሌላ ባልታወቀ ምክንያት) ከኪነ-ጥበብ ማኅበራት ተቃውሞ እንደገጠመው ይታወቃል፡፡ እነዚህ ማኅበራትም የሙዚቀኞች ማህበር፣ የጋዜጠኞች ማኅበር፣ የፕሮዲውሰሮች ማኅበር፣ የሰዓሊያን ማኅበርና አላቲኖስ የፊልም ሰሪዎች ማኅበር ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ የደራሲያን ማኅበር የነበረ ቢሆንም ከጋዜጣዊ መግለጫው በኋላ እራሱን ከተቃውሞው አግልሏል፡፡

በአጠቃላይ የማኅበራቱ ተቃውሞ፤ “ቃና ቲቪ የሚያቀርባቸው ድራማዎች ትውልድ ይበርዛሉ፤ ስደት ያበረታታሉ፤ በቀኝ ያልተገዛች ሀገራችንን ያስደፍራሉ፤ ቀኝ ገዢዎችን በተዘዋዋሪ ያመጣሉ፤ የሀገራችንን ፊልሞች እና ባለሙያዎች ቅርስነት ያጠፋሉ፤ ባህልና ቋንቋ ይበርዛሉ፤ ማንነታችንን ያጠፋሉ፤ የትውልዱን ልብ በምዕራባውያን ፍቅር እንዲሸነፍ ያደርጋሉ፤ ለሀገራችን ፊልምና ፊልም ሰሪ አስጊ ናቸው፤ በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን የማይገልጹ እና የሚያጠፉ ናቸው” የሚል ነበር፡፡

ለእነዚህ የማኅበራቱ የተቃውሞ ነጥቦች ካለው ኅብረተሰባዊ እውነታ እና ቃና ቲቪ ከሚያቀርባቸው ድራማዎች አንፃር ጥያቄያዊ ሀሳቦችን በተናጠል እናንሳ፡፡

ለተቃውሞ የቀረቡት ነጥቦች፤ ድራማዎቹ “ትውልድ ይመርዛሉ፣ ባህል ይበራዛሉ” የሚል ጥቅል ይዘት አላቸው፡፡ ይህም አሁን ያለው ትውልድ ‹‹የራሱን ባህል እና ማንነት ትቶ ድራማዎቹ የተሰሩባቸውን ሀገራት ባህል ይወርሳል›› የሚል አንድምታ አለው፡፡

ከጅምሩ ድራማዎቹን የሰሯቸው የየሀገራቱ ባለሙያዎች የራሳቸውን ባህልና ማንነት በድራማዎቹ ማንጸባረቅ መቻላቸውን መረዳት ትልቅ ነገር ነው፡፡ የሀገራችን “ባለሙያዎች” ይህን ማወቅ ብቻ ሳይሆን በስራቸው ውስጥ ይህንኑ መተግበር እንዳለባቸው ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

ከዚህ በተረፈ፣ እስከ ዛሬ ድረስ በርግጥም ትውልድ ሊበርዙ የሚችሉ ነገሮች በራሳቸው አባላት እና በሌሎች አካላት ሲተገበሩ ወይም ሲሰሩ እነዚህ አካላት የት ነበሩ? የሀገራችንን ማኅበረሰብ ማንነትና ባህል የማይገልጹ እና የማይመጥኑ ፊልሞች፣ መጽሐፍት፣ ሙዚቃዎች፣ የቲቪ ፕሮግራሞች …ወዘተ ሲሰሩ እና ሲቀርቡ ማኅበራቱ የት ነበሩ?

በትክክል ትውልድ ሊበርዙ የሚችሉ



ሙዚቃዎች ግጥም እና ዜማቸው ተኮርጆ ሲቀርብ የነዚህን ማኅበራት አንደበት ምን ተያዘ? የህንድና የአሜሪካን ፊልሞች ከነምናምናቸው በየጓዳ ጎድጓዳው ተተርጉመው ለገበያ ሲቀርቡ ምነው አንድ የተቃውሞ ድምፅ አልተሰማ? መጽሐፍት ከነጉዳቸው ተተርጉመው፤ ፍልሞች በቀጥታ ተኮርጀው ሲወጡ፤ ከዚህም በላይ ለኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ፊፅሞ መቅረብ የሌለባቸው ነገሮች በኢቢሲ በሚቀርቡ ተከታታይ የቲቪ ድራማዎች ሲቀርቡ እነዚህ ማኅበራት የት ነበሩ?

ታዲያስ ከነዚህ ነገሮች በላይ ትውልድ ሊበርዝ የሚችል ነገር ምን አለ? ቃና ቲቪ ገና በቅጡ ማቅረብ ሳይጀምር ለተቃውሞ ያስቸኮላቸው ነገር ምንድን ነው? በርግጥ ይህ የቴሌቪዥን ጣቢያ በዚሁ ስራው ብቻ ይቀጥል የሚል ሀሳብም ሆነ አቋም የለኝም። ተተኳሪ ተደራሲውን (Target audience) በቀጥታ የሚመለከቱ ስራዎችን ማቅረብ ቢችል የተሻለ እንደሆነ አምናለሁ። ይህንንም ጣቢያው ከሁለት ዓመት በኋላ የሚተገብረው መሆኑን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በአንድ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ለሚቀርብ የመዝናኛ ፕሮግራም መናገራቸውን ሰምቻለሁ።

ያም ሆነ ይህ፤ ከህፃን እስከ አዋቂ የማኅበራዊ ድረ-ገፅ ተጠቃሚ በሆነበት ዘመን፤ በየሀገራቱ የተከናወኑ ነገሮች ሰከንድ ሳይፈጁ በሚሰሙበትና በሚታዩበት የሉላዊነት ዘመን አንድ የቲቪ ጣቢያ የሚያቀርባቸው ድራማዎች ብቻ "ባህል እና ቋንቋ ይበርዛሉ" ብሎ ለተቃውሞ መነሳት የሚያስኬድ አይደለም። በተጨማሪም ልቅ የሆኑ ነገሮችን የያዙ ቪሲዲዎች በየጎዳናው በሚሸጡበት ሀገር በቃና ቲቪ የሚቀርቡ ትርጉም ድራማዎች "ባህል ይበራዛሉ" ብሎ መቃወም የሚዋጥ አይደለም።

በሌላም በኩል፤ የተቃውሞው ትኩረት ትርጉሙ ላይ ከሆነ በርግጥም እስከ ዛሬ ድረስ ተተርጉመው ያነበብናቸው መጽሐፍት ሁሉ ተተርጉመው መቅረባቸው ስህተት ነው ማለት ነው። በየቴአትር ቤቱ ተመድርከው ያየናቸው ድንቅ የሆኑ ትርጉም ተውኔቶች በአሁኑ ተቃውሞ መሰረት "ባህል የሚመርዙ፣ ቋንቋ የሚበርዙ" ናቸው ማለት ነው። በበኩሌ ፈፅሞ በዚህ አልስማማም። ምክንያቱም ዓለም አቀፋዊ ጭብጥ ይዘው ተተርጎመው በቀረቡ መጽሐፍት እና ተውኔቶች ብዙ መማርና ማወቅ ችለናልና ነው።

በተጨማሪም ተቃውሞው የውጭ ሀገራት ተከታታይ ድራማዎች በቲቪ ስለመቅረባቸው ከሆነ፤ እጅግ የዘገየ ከንቱ ጩኸት ብዬዋለሁ። ምክንያቱም የሀገሪቱ ብቸኛ የቲቪ ጣቢያ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኢቢሲ ዘወትር አርብ ያቀርብ ከነበረው "ታላቅ ፊልም" በሳምንት ሶስቴ ደጋግሞ እስከሚያቀርባቸው ተከታታይ የሜክሲኮ ድራማዎች ድረስ ምን ተቃውሞ ተሰማ? ለምንስ ይሄን መቃወም አልተቻለም? ወይስ ኢቢሲ ሳይሆን ቃና ቲቪ ነው "ለባህል ወረራ" ምክንያት የሚሆነው? (ነገሩ የባህል ወረራ የመባል አቅም ካለው ማለቴ ነው)።

## የቃና ቲቪ ድራማዎች

የቃና ቲቪ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንደገለጹት ከሆነ አሁን የሚያቀርቧቸውን ሰባት ድራማዎች ለመምረጥ ከሁለት መቶ በላይ የተለያዩ ሀገራት ተከታታይ ድራማዎችን ገምግመዋል። ይህም ዓለም አቀፋዊ የሆነ ጭብጥ የያዙና በጥበባዊ ፋይዳቸው ከፍ ያሉ ድራማዎችን መርጦ ከማውጣት አንፃር ብዙ እንደለፉ ያሳያል። በርግጥም ድራማዎቹ እንደ ባለሙያም ሆነ እንደ ጥበቡ አድናቂና ተከታይ ሆነን ብንመለከታቸው ብዙ ሊያስተምሩን የሚችሏቸው ጉዳዮች አሏቸው።

ከዚህ በተረፈ ድራማዎቹ በርካታ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ማሸነፍ የቻሉ ስራዎች ናቸው። ለዚህም ጥሩ ማሳያ ይሆነን ዘንድ ሁለቱን እንመልከት።

"ጥቁር ፍቅር" በሚል ርዕስ እየቀረበ ያለው እና በዋና ወይም መነሻ ርዕሱ "Kara para Ask" የተሰኘው የቱርክ ተከታታይ የቲቪ ድራማ በ "TV series awards 2014" ላይ ቀርቦ የ "Best drama series" ሽልማትን መቀዳጀት ችሏል። እንደዚሁም "Best series of the year 2014" ሽልማት ዘርፍን አሸንፏል። በዚሁ ድራማ የ "ኡመር"ን ገጸ-ባህሪ የሚጫወተው Engin Akyurek "ምርጥ ወንድ ተዋናይ" (Best Actor) በሚል፤ እንዲሁም የ "ኤሊፍ"ን ገፀ-ባህሪ የምትጫወተው Tuba Buyukustun "ምርጥ ሴት ተዋናይ" (Best Actress) ሽልማትን መቀዳጀት ችለዋል። በተጨማሪም ይህ የቱርክ ድራማ በሌሎች ዘጠኝ ሀገራት ቋንቋዎች ተተርጉሞ መቅረብ ችሏል። (የኛው አማርኛ አስረኛ መሆኑ ነው)

ከደቡብ ኮርያ የተወሰደው እና "ፍለጋ" በሚል ርዕስ እየቀረበ ያለው ድራማ "Missing you" የሚል እንግሊዝኛ ትርጓሜን ይዞ በሰባት የተለያዩ ሀገራት ቋንቋዎች (ከአማርኛ ውጪ) ተተርጉሞ የቀረበ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ከስምንት በላይ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ሽልማቶችን መውሰድ ችሏል። ለምሳሌ ያህል ይህ ድራማ በ "2012 K-drama star awards" ላይ ቀርቦ የ "ሊ ሲዮን" ገጸ-ባህሪን የምትጫወተው "ኪም ሶዩን" ምርጥ ወጣት ሴት ተዋናይ (Best young actress) ሽልማትን፤ እንዲሁም የ "ሀን ጂንግ ዉ" ገፀ-ባህሪን የሚጫወተው "ዮ ጂን ጎ" ምርጥ ወጣት ወንድ ተዋናይ (Best young actor) ሽልማትን መቀዳጀት ችለዋል።

በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ድራማዎች ዓለም አቀፋዊ ጭብጥ (Universal theme) ይዘው የተሰሩ ናቸው። ይህም ፍቅርን፤ ጥላቻን፤ ቤተሰባዊ ግንኙነትን፤ ወንጀልን …ወዘተ የሚመለከት ነው። እነዚህ ጭብጦች ታዲያ በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢቀርቡ የተመልካቹ ጉዳይ መሆን የሚችሉ ናቸው። በጥሩ ሁኔታ እስከተሰሩ ድረስ ለታዳሚያቸው አንዳች ጠብ የሚያደርጉት ነገር አያጡም።

ለተቃውሞ ከተነሱት ሀሳቦች ውስጥ "ስደትን ያበረታታሉ" የሚል ያለ ሲሆን ይህም በጣም አስገራሚ ነው። ተቃዋሚዎቹ ድራማዎቹን በአግባቡ ሳያዩ ለተቃውሞ መነሳታቸውን ያመለክታል። ይህን የተቃውሞ ሀሳብ "የውበት እስረኞች" (በዋና ርዕሱ "La Guerrera" ወይም በእንግሊዝኛ "The brave woman") በሚል የተሰራው ድራማ ውድቅ ያደርገዋል። ይህን ድራማ ያየ ስደትን ይጠየፍ እንደሆን እንጂ የሚበረታታበት ምንም ምክንያት የለም።

ያም ሆነ ይህ፤ እንቃወማለን ብለው ሳያስቡት ቃና ቲቪን በሰፊው አስተዋውቀውታል፡ ፡ ይህም በቂ መረጃ ሳይዙ ለተቃውሞ መነሳት የፈጠረው ነው። ገና ለገና ተመልካች ከሲኒማ ይጠፋል ብሎ በመስጋት የማይሆን ነገር መስራት እና ስሜታዊ ሀሳብ ማቅረብ ከነዚህ ማኅበራት የሚጠበቅ አይደለም። ተመልካች የሚመጥነው ወይም ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አይነት ስራ በሲኒማ እስካላገኘ ድረስ ቃና ቲቪ ምንም አቀረበ ምን ከሲኒማ መሸሹ አይቀርም። እናማ እራስን መፈተሽ እና ወደራስ መመለስ ይገባል።

> **ገና ለገና ተመልካች ከሲኒማ ይጠፋል ብሎ በመስጋት የማይሆን ነገር መስራት እና ስሜታዊ ሀሳብ ማቅረብ ከነዚህ ማኅበራት የሚጠበቅ አይደለም። ተመልካች የሚመጥነው ወይም ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አይነት ስራ በሲኒማ እስካላገኘ ድረስ ቃና ቲቪ ምንም አቀረበ ምን ከሲኒማ መሸሹ አይቀርም። እናማ እራስን መፈተሽ እና ወደራስ መመለስ ይገባል**

## የቃና ቲቪ ግድፈቶች

በርግጥ ቃና ቲቪ የውጭ ሀገራት ተከታታይ ድራማዎችን ተርጉሞ ማቅረብ መብቱ ቢሆንም ለሚፈጥረው ኅብረተሰባዊ ጫና በጽኑ ሊያስብበት ይገባል። አብዛኛዎቹ ድራማዎች የሚቀርቡባቸው ሰዓታት በተለይ ተማሪዎችን "ስራ ፈት" ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸውና ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

ከዚህ ሌላ፤ የቃና ቲቪ ጉድለት ሆኖ ያገኘሁት፤ የአማርኛው ድምፅ ትወና እና የሚታዩት ገፀ-ባህሪያት አካላዊ ገፅታ በተወሰነ መልኩ የማይገጥም መሆኑ ነው። ይህ የገፀ-ባህሪያቱን ስብዕና ጭምር የሚመለከት ሲሆን በድምፅ ተዋንያን (Type cast) አመራረጥ ላይ ብዙ እንዳልተሰራ ያሳያል። በርግጥ ይህን ችግር በዚህ ሰዓት ማስተካከል የሚከብድ ቢሆንም ሊታሰብበት ይገባል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላው ችግር፤ ተመሳሳይ የሆኑ ድምፆችን በአብዛኛዎቹ ድራማዎች ላይ መስተዋሉ ነው። ጣቢያው በርካታ ባለሙያዎችን በስሩ ከመያዙ አንፃር ይህ ስህተት የሚጠበቅ አይደለም።

ቃና ቲቪን ከታዘብኩባቸው ነገሮች ውስጥ ሌላው ፕሮግራም፤ ድራማ እና ማስታወቂያ የሚያቀርብበትን መንገድ ነው። ፊልም የሚያሳዩ የአረብ ቻናሎችን አቀራረብ መንገድ እና ይዘት በቀጥታ መከተሉ እራሱን ችሎ ከሚንቀሳቀስ የቴሌቪዥን ጣቢያ የሚጠበቅ አይደለም። አዲስ እና እራስ ገዝ እንደመሆኑ መጠን የራሱን አቀራረብ መንገድ መከተል ይኖርበታል።

በተጨማሪም ቃና ቲቪ ኢትዮጵያዊ እንደመሆኑ መጠን እና የሀገሪቱን ጥበብ ከማሳደግ አንፃር አሁን በሚያቀርባቸው ድራማዎች ጥራት ልክ የተሰሩ ሀገርኛ ድራማዎችን የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለበት ልብ ሊለው ይገባል።

(በቀጣይ ህትመት ስለድራማዎቹ ጽሑፍ እንደማቀርብ ከወዲሁ ለመግለጽ እወዳለሁ)

መልካም ጊዜ!

ግርማ ካሳ



# ጠቡ የሻዕቢያ እና የሕወሃት እንጂ የሕዝብ አይደለም!

ሰሞኑን በሰሜኑ የአገራችን ግዛት ጦርነት ተቀስቅሷል። አስመራም፣ አዲስ አበባም ያሉ ገዢዎች ጦርነት መደረጉን ማመን ብቻ ሳይሆን "ይሄን ደመሰስን፣ ይሄን ያህል ገደልን" እያሉ በመማጸደቅ ላይ ናቸው። አለም የትናየት ደርሳለች፣ ትላንናት እኛ እየረዳናቸው ነጻ የወጡ የአፍሪካ አገራት እንኳን የትናየት ደርሰዋል፣ እኛ አሁንም መግደልን እንደ ጀብዱ አድርገን እናወራለን። አንዳንድ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ከሻዕቢያ ጋር የሚደረግን ጦርነት ከአንድ የዉጭ አገር ወራሪ ጋር እንደሚደረግ ጦርነት አድርገው ነው የሚያዩት።

በእኔ እይታ ይህ የተሳሳተ አመለካከት ነው። በሻዕቢያ እና በኢሕአዴግ መካከል የሚደረገው ጦርነት ከኢትዮጵያ ህዝብ እና ከኤርትራ ህዝብ ጥቅም ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። ጦርነቱ፣ በዜጎች ደም የሰከሩ፣ የሁለት አምባገነን ቡድኖች ጦርነት ነው። የነርሱ ጣጣ ነው። ለጥቅማቸው፣ ለስልጣናቸው ሲሉ የሚያደርጉት። ምንም እንኳን ላለፉት 25 አመታት ኤርትራ በፖለቲካ አስተዳደር፣ በሻዕቢያ እና በሕወሃት ሴራ፣ ከኢትዮጵያ ብትለይም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እና የኤርትራ ህዝብ ግን በመንፈስ የተለየ ህዝብ አይደለም። በታሪክ፣ በባህል፣ በስጋ፣ በኃይማኖት እርስ በርሱ የተሳሰረና የተዋለደ ወንድማማች ህዝብ ነው። እግዚአብሄር ፈቅዶና ህዝቡ በትግሉ በርትቶ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስታት በአስመራና በአዲስ አበባ ቢመጡ እንደገና ተስማምቶ ሊዋሃድ የሚችል ህዝብ ነው። ብዙዎቻችን ላለፉት 25 አመታት ከነበረው ፖለቲካ የተነሳ፣ ሻዕቢያን ከህዝቡ መነጠል አቅቶን፣ ሻዕቢያ ላይ ችግር ስላለብን፣ ኤርትራውያን ላይ በጅምላ እንፈርዳለን። ይህ ሌላ ትልቅ ስህተት ነው። እስቲ ስለ ኤርትራ ህዝብ ትንሽ ላካፍላችሁ። የሰማሁትንና ያነበብኩትን ሳይሆን ያየሁትንና እና ያለፍኩበትን። የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበሩኩኝ ጊዜ የማስታወሰውን። (ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆና የመጨረሻዎቹ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች ነበርን)

ኤርትራ፣ አስመራ ሲባል ብዙ ጊዜ ወደ አይምሯችን ከሚመጡት ነገሮች ጥቂቶቹ፣ ግፈኛው ሻዕቢያ ሲሆን ሌላው ደግሞ ብዙ ጊዜ በፖስት ካርድ ላይ የምናየው፣ ዘንባባዎች በዳርና በዳር ያሉበት መንገድ በመሃከሉ የሚያልፈው፣ ፒያሳ ወይንም ኮምፖሽታቶ የሚባለውን ሰፈር ነው። በዚያ መንገድ ብዙ ኬክ ቤቶችና ቡና ቤቶች ነበሩ። ትዝ ይለኛል በአምሳ ሳንቲም አንድ ኬክና ምን የመሰለ ካፑቺኖ እናዝ ነበር። በተለይም ሲመሽ ከመብራቶቿ ጋር ከተማዋ በጣም ታምር ነበር። (በነገራችን ላይ አሁን አስመራ ያኔ የነበራት ውበት የላትም። የተንኮታኮተችና ያረጀች ከተማ ሆናለች። የቀድሞው የክፍለ ሃገር አወቃቀር ብንመለከት የትግራይ ክፍለ ሃገር ቢያንስ አራት፣ ጎንደር ሁለት፣ ጎጃም ሁለት፣ ወሎ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች እያንዳንዳቸው ሲኖራቸው፣ ኤርትራ የነበራት፣ እኛ የተማርንባት አንዱ ዩኒቨርሲቲ ተዘግቷል። ከከተማዉ ውበት ባሻገር የማልረሳውና በውስጤ የተተከለ አንድ ሌላ ነገር ቢኖር የሕዝቡ ፈሪሃ እግዚአብሄርነትና ደግነት ነበር። እስቲ አንዳንድ ያጋጠሙኝን ላጫውታችሁ።

አንድ ቀን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወዳለው ካፍቴሪያ እራቴን ለመብላት እየሄድክ ሳለ ጓደኞቼ አገኙኝና «አትሄድም እንዴ?» አሉኝ። «የት?» አልኳቸው። «ንግደት» አሉኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ያንን ቃል የሰማሁት። ጓደኞቼ ነገሩን ያውቁ ነበርና ምን እንደሆነ በኋላ አስረዱኝ። ያን ቀን በአስመራ በሰሜን ምዕራብ በኩል ቪላጆ የሚባል ሰፈር፣ የሚካኤል ይሁን የገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አለ። (የቱ እንደሆነ አሁን አላስታወስም)። የዚያ ቤተ ክርስቲያን ታቦት የሚወጣበት ቀን ነበር። ታዲያ ቤተ ክርስቲያኗ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ታቦቱ በነገሰበት ቀን ግብዣ አድርገው በአካባባው ያሉትን ሁሉ ይጋብዙ ነበር። ይሄ ስርዓት ነው እንግዲህ ንግደት የሚባለው። ያኔ መኪና የለንም። በእግራችን ከአንድ ሰላሳ ደቂቃ በኋላ በቪላጆ ደረሰን። አራት ተማሪዎች ነበርን። በሰፈሩ ስንሽከረከር «ኑ ግቡ» ብሎ የሚጠራን ሰው አጣን። ለካ ኑሮ በጣም ስለተወደደ እንደድሮ በየመንገዱ እየቆሙ «ብሉልን ጠጡልን» ማለት ቆሟል። «መቼም የዩኒቨርሲቲ ካፍቴሪያ ምግባችንን ትተን ባዶ ሆዳችንን አንመለስም» ብለን ወደ አንዱ ቤት አመራንና አንኳኳን። «እንኳን አደረሳችሁ?» ስንል፣ አንዲት ያኔ ወደ አርባ አመት የሚጠጋት እናት፣ በእጇ አንድ ሕጻን ልጅ ታቅፋ ወጣችና «ግቡ፣ ግቡ» አለችን በፈገግታ። የቤቱ በር ጠባብ ነበር። ጎንበስ ብለን ገባን። የነበረችዋን ጠረቤዛ ከበብናት። በትልቅ ትሪ እንጀራ ቀረበልን። ሴትየዋ ድስቱን አመጣችና ወጡን እንዳለ እንጀራው ላይ ደፋችው። ብዙ ጊዜም አልፈጀብንም ትሪውን ጠረግነው። ከዚያም በትላልቅ ጣሳዎች ጠላ አመጣች። ለእኔ ውሃ ተሰጠኝ። ምን ልበላቹህ ምን የመሰለ መስተንግዶ ተደረገልን።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራ ነዋሪዎችን ሳስብ፣ ያቺን ሴት አስባለሁ። ለእግዚአብሄር ፍቅር ስትል፣ እንግዳን በደስታ የምትቀበል! ችግረኛ ናት፣ ነገር ግን ከፊቷ ውስጣዊ ሰላም ያላትና ሰውን የምትወድ ትልቅ ሴት ነበረች! ያኔ በትግርኛ አልነበረም ያናገርናት። «የኔ ዘር ናቸው» ብላ አልነበረም ያስተናገደችን። ነገር ግን፣ ትልቅ ሴት በመሆኗ እንጂ።

የማያልፍ ነገር የለምና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችንን አጠናቀን የምረቃችን ቀን ደረሰ። ባጽእ (ምጽዋ) በሕዝባዊ ኃርነት ኤርትራ ግንባር ሥር ከወደቀ በኋላ በምጽዋና በአስመራ መሃከል ከሚገኝ አንድ የከፍታ ቦታ፣ «ግራፒ» እንለው የነበረ ከሩቅ የሚተኮስ መድፍ በየጊዜው አስመራ ከተማ ላይ ያርፍ ነበር። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ መብረሩን አቁሞ ነበር። የጦር አይሮፕላን ግን ማረፉን አላቆመም። በወቅቱ ደግሞ ሕወሃት በትግራይ ጥቃቶች ያደረግ ስለነበረ ከአስመራ አዲስ አበባ ያለው መንገድ ሙሉ ለሙሉ ተዘግቶ ነበር። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስለማይበርም ቤተሰቦቻችን ለምርቃታችን ከአዲስ አበባ ሊመጡ አልቻሉም። ስለዚህ የምርቃ ሥነ-ሥርዓታችን ብዙ አልጓጓንለትም ነበር።

የምርቃታችን ሥነ-ሥርዓት ቀን በወንዶች ሽንት ቤት ዉስጥ ትልቅ ፈንጂ ፈነዳ። ያን ሰዓት ትልቅ ድንጋጤ በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ለጥቂት ደቂቃዎች ተፈጠረ። ወዲያው ሻዕቢያ የደስታ መግለጫ መልዕክት ማስተላለፉ ነው ብለን ቀልደን አለፍን። ከሩቅ በሚተኮስ መድፍ በግራፒ ተምሮ በፈንጂ መመረቅ ይሉታል ይሄ ነው። ያ ቀን ከፈንጂ ፍንዳታው ሌላ የማልረሳው፣ በጣም ልቤን የነካና ከኤርትራ ሕዝብ ጋር ዘላቂ ፍቅር እንዲኖረኝ ያደረገ አስደናቂ ነገር ሆነ። ቤተሰቦቼ ከአዲስ አበባ ስላልመጡ የምረቃ ልብሴን አውልቄ ወደ ዶርሚተሪ ለማምራት እየተዘጋጀሁ ሳለ ድንገት፣ አንዲት ሴትዮ አበባ ይዘው ብቅ አሉ። ትዬ ዘይዳ ነበሩ። ትንሽ እንደቆየው ደግሞ አንዲት አሮጊት ሴትዩ ሌላ እቅፍ አበባ ይዘው መጡ። አደይ ጸሃይቱ ነበሩ። ሁለቱም አይተዋወቁም። በአራት አመት የአስመራ ቆይታዬ የተወዳጀኋቸው እናቶች ናችው። ያኔ ብቻዬን የሆንኩኝ መስሎኝ ነበር። ግን ከአንድም ሁለት እናቶች እንደ እናቴ ሆነው አበባ ይዘው በምረቃዬ ተገኙ። እነዚህ ሁለት እናቶች ዶሮ አርደው ቤታቸው ድግስ አዘጋጅተው ነበር። ሁለቱም ወደ ቤታቸዉ እንድመጣ ፈለጉ። ግራ ገባኝ። በኋላ አንዳቸው ጋር ምሳ ሰዓት፤ ሌላኛዋ ጋር ደግሞ ሲመሽ ለእራት ሂጄ ከጓደኞቼ ጋር የተዘጋጀልኝን ድግስ ተካፈልኩ።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራን ሕዝብ ሳስብ ትዬ ዘይዳና አደይ ጸሃይቱን አስባለሁ። እነዚህ እናቶች በስጋ እናቶቼ አይደሉም። እንደነርሱ ትግሬ አይደለሁም። እንደነርሱ የኤርትራ ተወላጅ አይደለሁም። ነገር ግን የእነዚህን እናቶች የዋህነት፣ ፍቅርና ያላቸውን ፈሪሃ እግዚአብሄር የሞላባቸው ትልቅ ሴቶች ናቸው። ደጎችና ለዘር ቦታ የማይሰጡ። እግዚአብሄር ባሉበት ቦታ ይባርካቸው። የመጨረሻ አመት ተማሪ እያለን በአንድ ሃይ ስኩል፣ ለሶስት ወር ማስተማር ነበረብን። ባርካ ተብሎ በሚታወቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመደብኩኝ። የተመደብኩበት ክፍል አስተማሪ ክፍሉ በጣም ረባሽ ክፍል እንደሆነ አስጠነቀቀኝ። በጣም ፈራሁ። ነገር ግን ማስተማሩን ስጀምር አስተማሪው ከነገረኝ የተቃረነ ሁኔታ ነው ያየሁት። ተማሪዎቹ በጣም የሚያዳምጡ፣ በአክብሮት ከተያዙ ብዙ ሊሰሩ የሚችሉ ሆነዉ ነበር ያገኘኋቸው። አስተማሪያቸውም ብሆን ጓደኞቼም ሆነው ነበር የተለያየነው። ያኔ ከተማዋ ችግር ላይ ነበረች። እንደዚያም ሆኖ ግን ከፊታቸው፣ ከሁኔታቸው ያየሁት ፍቅርንና ደስታን ነበር። አስመራን ሳስበ፣ የአስመራን ሕዝብ ሳስብ፣ ያኔ ወርቃማ ዩኒፎርም ለብሰው የማስተምራቸውን፣ ያዳምጡኝና ሳስረዳቸው ፊቴን ያዩ የነበሩትን የባርካ

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

ጽጌሬዳ ጎንፋ



# የማታ ታክሲዎች ባሕርይ

እኛ ሰፈር ለመኖር ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ትዕግሥት ነው… ብዙ ትእግስት… ርቀቱንና የትራንስፖርት እጥረቱን ያገናዘበ ትዕግሥት… ከ10 ዓመታት በፊት ከምሽቱ 1 ሰዓት ካለፈ ከለማዳ ጅቦች ጋር እየተጋፋን… በጋሪ ተጉዘን አስፋልት የለ… ኮብል ስቶን… ብቻ ጭቃ እያላቆጥን ቤታችን እየገባን… ውሃ በጀሪካን፣ በአህያ ጭነን… በክረምት የዝናብ ውሃ በአሸንዳ እየደቀንን ልብሳችንን እያጠብን… ኤሌክትሪክ ከስንትና ስንት ሜትር ርቀት በቀጭን ሽቦ ቀጥለን (በወር ለአንድ አምፖል 10 ብር እየከፈልን)… ስልክ ከጎረቤት ሱቅ እየተጠራን… ያቀናነው ሰፈር እንደ መልማት ሲጀምረው… ታክሲ ገባ! "እፎይ" ስንል የቤት ኪራዩ ርካሽነት ያማለላቸው የመሀል ከተማ ተከራዮች ወደኛ ፈልሰው ወረሩን… ደኅና!

እየዋለ እያደረ ጫካው እየተመነጠረ… ሜዳ ተራራው ሳይቀር… የጤፍ እርሻ የነበረው ሁሉ በማኅበር እየተመራ በካሬ እየተሸነሸነ ለባለሀብት ተቸበቸበ… ፎቁ፣ ሱፐር ማርኬቱ፣ ቡቲኩ፣ ገበያው ደራ… ዐይናችን እያየ ሰፈራችን ከአናሳ የመኖሪያ መንደርነት ወደ ቀለጠ ከተማነት አደገች፣ ተመነደገች… ጥሩ!

ለእኛ ለቆርቋሪዎቹ ታዲያ ምን ተረፈን? ምንም!… ድሮ ድሮ ጎረቤቴ የጓደኛዬ ቤት… እዛጋ የነ ጋሽ እንትና ቤት… በስተግራ ደግሞ የነ እትዬ… ከሱ አልፎ ረጅም ኮባ ያለበት ጊቢ.. ቀጥሎ ኀይለኛ ውሻ ያለበት… ከሱ ቀጥሎ የወንድሜ ጓደኞች ቤት… እልፍ ብሎ መኪና ያላቸው… በቃ በዚህ ምልክት ሁሉም ሰው እርስ በርሱ ይተዋወቃል፡፡ አሁን በየቀኑ አዲስ ፊት ነው… በየጊዜው የማላውቀውን ሰው ነው… ሰው ሁሉ ይንቀዋለላል፡፡ አይረጋም… የተከራዩትን ቤት ግፋ ቢል ከ6 ወር በላይ አይቆዩበትም፡፡ ለሰፈራችን የሚበቃ ትዕግሥት ያጥራቸዋል መሰል… እቃቸውን በአይሱዙ ጭነው ሲወጡ እና ሲገቡ እናያለን… እኛስ አንዴ እግራችንን ተክለን ሥር ሰደናል… ወደየትም ውልፍት የለም… ትዕግሥታችንን ከዕለት ወደ ዕለት እያዳበርን፣ እያፋፋን መኖር ነው፡፡

*

በቀደሙት ዓመታት በማታ ትምህርት ሰበብ ሁል ጊዜ ማለዳ ለሥራ ወጥቼ፣ ማታ ማታ እየተጓዝኩ ቤቴ እገባ ነበር… አሁን አሁን ደግሞ በአንዳንድ ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክንያት… አልፎ አልፎም ሆነ ብዬ በጊዜ የማላገኘውን ታክሲ ሲመሽ እጠብቀዋለሁ… ከምሽቱ ሦስት ሰዓት በኋላ እነሱ ብቻ በፈለጉበት ቦታ እና ሰዓት የሚገኙ ታክሲዎች እጓዛለሁ - ቀጥሎ ካስተዋልኳቸው የእነርሱ ባሕርይ ጋራ…

### ጨኸት

አዳዲስ ዘፈኖችን ብዙ ጊዜ የምሰማው የማታ ታክሲዎች ውስጥ ነው፡፡ አማርኛም ሆነ የሌላ ቋንቋ… የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ በጣም በጩኸት ይከፈታል፡፡ ከታክሲዋ አካል አፈትልኮ ባገኘው ቀዳዳ እየሾለከ በየመንገዱ የሚሰራጭ ጩኸታም ዘፈን… ሜሞሪና ፍላሽ ባይኖር ራዲዮ የምሽት ፕሮግራሞችን በጩት ያሰማሉ…. "የት ደረስሽ?" የሚል አሳቢ ከቤት ቢደውልም "እዚህ ነኝ" ለመባባል መደማመጥን የሚያውክ… ጩኸት አንዱ ባሕሪያቸው ነው፡፡

### ታሪፍ

የ2.5 ብሩን መንገድ 5 ብር ቢሉ፤ የ5 ብሩን መንገድ 10 ቢያደርጉት፤ ሃይ ባይ የለባቸውም… ለተቃውሞም ለድርድርም መናገር የጀመረ "መውረድ መብትህ ነው ለላዳ ታክሲ 100 ብር ትከፍል የለም?" ሊባል ይችላል:: እሱም "እውነትም" ብሎ የተጠየቀውን ይከፍላል… እንዲያውም ውዝግቡን የጠሉ ረዳቶች ከመነሻው ሒሳብ ሳይሰበስቡ ጉዞ አይጀመሩም… አንዳንዶቹ ደግሞ ጭለማን ተገን አድርገው ከመልሱ ጋር ከጥቅም ውጭ የሆነ ብር ቀላቅለው ይሰጣሉ… የግራና የቀኝ ቁጥሩ የማይገናኝ… ሲከፋም ግማሽ ጎኑ 5 ብር ከከግማሽ 10 ብር ጋር ካለ ወገኑ ተጣብቆ ሊደርሳችሁ ይችላል…

ሌላው ደግሞ እነዚህን የአንድ ብር ሳንቲሞች እስካሁን እንደ ብር ለመቁጠር ተቸግሬአለሁ… እኛስ በቦርሳችን እንሸከማለን…(እንኳን ብር ስንት ነገር ተሸክመናል…) በኪሳቸው የሚይዙት ወንዶች ግን ለቀኝ እና ለግራ ኪስ እኩል እኩል ከፍለው ካልያዙ እንደ ጦር ጉዳተኛ ሚዛናቸውን ስተው በአንድ ጎን እያዘነበሉ መሄዳቸው አይቀርም፡፡

### መደራረብ

አንድ ጊዜ ሆነ ብዬ ቆጠርኩ፡፡ 12 ሰው የመጫን አቅም ያለው ታክሲ ውስጥ… ሹፌርና ረዳቱን ጨምሮ 25 ሆነን ሰፍረንበታል… (ሴቶች እና ሕፃናት ሳይቆጠሩ… ሴቶችና ሕፃናት የማይቆጠሩበት ምክንያት ስላልተሳፈሩ ነው… ሕፃናትም 4ኛ ዙር እንቅልፋቸው ላይ ይሆናሉ… የሴቶቹን ግን እንጃ - እንደ እኔ የሚያስመሽ ጉዳይ የላቸው ይሆናል… ወይም በዛ ሰዓት ሩቅ ሰፈር ከመሄድ ቅርብ ዘመድ ቤት እያደሩ ይሆናል… ወይም ባለ መኪኖች ሆነው ይሆናል… ግምት ነው እንግዲህ… ብዙ ጊዜ ከምሽቱ 3 ሰዓት ተኩል በኋላ የምሳፈርበት ታክሲ ውስጥ ብቸኛ ሴት ሆኜ ራሴን አገኘዋለሁ…

### ማቆራረጥ

ይገርመኛል፡፡ መንገዱ ሁሉ አቋራጭ አለው… ከየትም ተነስተው የትም ለመድረስ አቋራጭ መንገድ ይጠቀማሉ… ችሎታ ነው መቼም… በየመኖሪያ መንደሩ በየኮብል ስቶኑ… እያቆራረጡ ይደርሳሉ፡፡

### ፍጥነት

መንገዱም ነፃ ስለሚሆንላቸው መጋለብ ነው፡፡ ከሱ እኩል በሚፈጥኑ አይሱዙና በሲኖ ትራክ መኻል ለመኻል ሰንጥቀ የተሳፈርኩበት ሚኒባሱ ሽው ሲል ዐይኔን እጨፍናለሁ፤ ጆሮዬን በኢርፎን እደፍናለሁ… ንስሀ እገባለሁ፤ የቀረበችዋ የእግዚአብሔር መንግሥት ከመድረሷ ቀድሜ እየሄድኩ ይመስለኛል… ክንፍ አብቅዬ የምበር ይመስለኛል… ራእይም ይመስለኛል… ብቻ ብዙ ነገር ይመስለኛል… በዚህ ጊዜ "እረ ቀስ ብለህ አሽከርክር" ማለት… ዘበት… ጭራሽ ነዳጅ የመስጠት ጉልበት ያጎናፅፈዋል መሰል… ይብስበታል፡፡ ያኔ፣ ቀኑን ለሰራዊት፤ ለሊቱን ለአራዊት የሰጠህ… የአራዊቱን ሰኣት ወስደህ የሰራዊቱን ሰዓት በሰላም አምጣልኝ ብዬ እፀልያለሁ፡፡

## የድኅረ . . . ከገፅ 15 የዞረ

በሌላ በኩል፣ በድኅረ-ቅኝ-ግዛት ዘመን አፍሪካ፣ ከምዕራቡ ዓለም የወረስናቸው ባሕላዊ ዕሴቶች፣ የአፍሪካዊነትን መንፈስ የሚያጠነክሩ ሳይሆኑ፣ ለህልና-ባርነት የሚዳርጉ ናቸው:: ከሁሉ በላይ፣ የምዕራቡ ዓለም ግዙፍ የመገናኛ ብዙኃን እና የፊልም ኢንዱስትሪ ተቋማት፣ ከአፍሪካ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፈጽሞ የማይገናኙትን ነገሮች በአፍሪካውያን አእምሮ ውስጥ በማስረጽ፣ ለዘመኑ የአፍሪካ አንገብጋቢ ጉዳዮች ትኩረት እንዳይሰጥ በስፋት እየሠሩበት ነው:: አውሮፓውያን፣ አፍሪካን በእጅ አዙር ቅኝ-አገዛዝ ለመግዛት የሚጠቀሙበት ቀላሉ ዘዴ አፍሪካውያንን በህልና-ባርነት ሥር ማድረግን ነው:: አብዛኛው አፍሪካዊ፣ ከዕድሜ ልክ እንቅልፉ ነቅቶ፣ ለእውነተኛ የኢኮኖሚ ነጻነት የማይታገልበት ምክንያት ይኼው ነው:: ውጤቱም፣ በአፍሪካ በአጠቃላይ፣ በኢትዮጵያ በተለይ እየታየ ያለውን የሀብት-ዝርፍያ እና የኢኮኖሚ ብዝበዛ ማመቻቸት ነው::

በከተማ አካባቢ ተደላድለው በመኖር የምዕራቡን ዓለም ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊስ የሚያስፈጽሙ አሻንጉሊት አውሮ-አፍሪካውያን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በገጠር የሚኖሩ የድሆችን አስቃቂ ሁኔታ መቀየር አይችሉም:: ጃክ ዎድስ በትክክል እንደ ታዘበው፡- "የእጅ አዙር ቅኝ-አገዛዝ የወል መልኮቹ ማለትም ኢኮኖሚያዊ እና ወታደራዊ መልኮቹ በሦስተኛው ዓለም የሚካሄደውን ብዝበዛ አስታማማኝ ለማድረግ እና ለማባባስ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ሆነው ተዘጋጅተዋል… በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን በምዕራብያውያን ቁጥጥር ሥር ያሉ በርካታ ተቋማት ሚና በምንገመግምበት ጊዜ ‹የሚያብለጨልጭ ነገር ሁሉ ወርቅ አይደለም› የሚለው አባባል ትክክለኛ መሆኑን እንገነዘባለን… ወታደራዊ ውል፣ ወታደራዊ ኅብረትና የጦር ሠፈሮች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የሚገለገሉባቸው ዓይነተኛ መሣርያዎች ናቸው::" (Jack Woddis, 1976፡ pp., 95, 111, 118–ትርጉም- ሰለሞን አድምቄ) ዞረም ቀረ፣ አፍሪካ እውነተኛ የኢኮኖሚ ነጻነት ሊኖራት የሚችለው፣ የአውሮ-አፍሪካውያን የዕድገት ፖሊስ አስተሳሰብ በማፈራረስ ብቻ ይሆናል:: ስለዚህ ነው፣ የእጅ አዙር ቅኝ-ግዛት አከርካሪን ለመስበር፣ በአፍሪካውያን አስተሳሰብ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ጊዜ የማይሰጠው:: ይህንን በተመለከተ በቀጣዩ ክፍል 9 እንመለስበታለን::

ቸር እንሰንብት!

## ከግጥም . . .

ከገፅ 19 የዞረ

ለመረዳት ቸግሮኛል፡፡ ማህሌት ብዙ ታዋቂ መሆኑን እንደማታውቅና አባት ለልጁ የሚያደርገውን አጉድሎባት እንደማያውቅም ተናግራለች፡፡ የማህሌት እናት ቤተልሄም ፀጋዬ ትባላለች፡፡ በአንድ ወቅት ዕዝራና ቤቴልሔም ሰነዓ አብረው መኖር ጀምረው ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ አንድያ ልጁ ማህሌትን በኢትዮጵያዊ ባህል እንድታድግ ከመፈለጉ የተነሳ ከጋሽ አበራ ልጆች ጋር እዚሁ እንድታድግ ትቷት ወደ የመን አቅንቷል፡፡ ቤቴልሄም በአርባዎቹ መጀመሪያ የምትገኝ ስትሆን ኑሮዋም በስዊድን ነው፡፡ ከዕዝራ ጋር በትዳር የቆዩትም ለአምስት ዓመታት ነበር፡፡ ዕዝራ ተፈጥሮን አድናቂና ነጻ ሰው ነበር፡፡ ለውብ ግጥም ብቻ ሳይሆን ለውብ ሴትም ልቡ ይሸፍት ነበር፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሱ ቀድም ብሎ ከአንዲት የመናዊት ወጣት ጋር መኖር ጀምሮ ነበር፡፡ በመጨረሻም ኑሮውን እዚህ ከመሰረተ በኋላ ተለያይተዋል፡፡ ነብይ መኮንን ከዕዝራ በኋላ "ማነው እንድገጥም የሚጎተጉተኝ? ማነው ግጥምህን አንብብልኝ እስኪ የሚለኝ?" እያለ ሐዘኑን ለመድረኩ አጋርቷል፡፡ ዕዝራ ለአንጋፋና ወጣኒ ገጣሚዎች ደወል በመሆን ሰማየ ሰማያትን እንዲቀዝፉ የምድርን ማኅበራዊ ውኽንብር እንዲያስሱ የሚያተጋ የሥነ-ጽሁፍ አድባር ነበር፡፡ ጋሽ አበራ ለማ የእሁዱን የሽኝት ሥነ-ስርዓት ወደኋላ እያሰበ የሰኞ ምሽት የመታሰቢያ ፕሮግራም ላይ የተገኘውን ሰው በመመልከት "ዛሬ ለእሁዱ ካሳ ነው" በማለት ገልጧል፡፡

ጋሽ አበራ ከ36 ዓመት በፊት በየመን ሰነዓ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበርን ወክሎ ዕዝራ በየመን ተማሪ ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተዋወቁና በጋዜጣ ላይ ሒስ መስጠት የጀመረውም በ1975 በአዲስ ዘመን በባህል አምድ ስር በራሱ በጋሽ አበራ 'ህይወትና ሞት' በሚለው አጫጭር ልበ-ወለድ መሆኑን አስታውሷል፡፡ ዕዝራ ከማረፉ ከአንድ ወር ከአስር ቀን በፊት በፌስቡክ ገጹ የባለቅኔ ደበበ ሰይፉን የህልፈት ዕለት በማሰብ "...በአካል ራቀን እንጂ አዕምሮውን ስላወረሰን ዛሬም ህያው ነው ጊዜ ደበበን ለመፋቅ አለኸለኸ እንጂ አቅም የለውም" እያለ ቁጭቱን አስፍሮ ነበር፡፡ በደበበ ሰይፉ ስራዎች ላይ ተጠምዶ የምርምር ውጤቱን በመጽሐፍ ሊያበረክትልን እየተጋ እንደነበርም ወዳጆች ተናግረዋል፡፡

አለማየሁ ገላጋይ ስለዕዝራ ሲናገር ከሰራው ይልቅ ሊሰራ ያሰበውና የጀመረው ብዙ እንደነበር እየተብሰከሰከና ከፈጣሪ ጋር እየተዋቀሰ ምሬቱን ገልጧል፡፡ ጋሽ አበራም የመን ሰነዓ ያለውን ቤት ስንብረብር የምናገኘውን አናውቅም በማለት የበለጠ እንድንጓጓ አደርጎናል፡፡ ዕዝራ በነብይ መኮንን 'ስውር-ስፌት' መጽሐፍ ውስጥ የምትገኝን 'ከሞት ጋ ቀጠሮ' የምትሰኛዋን ግጥም በጽሐፉ ሲዳስስ "ሰው እድሜውን ጨርሶ ከነምርኩዙ እመቃብር አፋፍ ቢደርስ አፈሩን ገለባ እንዲያደርግለት እንመኛለን፡፡ ገና አቅምና ዕድሜ ተርፎት ድንገት በሞት ሲነጠቅ እንሸማቀቃለን" ነበር ያለው፡፡ ይኸን ያለው ከአንድ ዓመት በፊት መሆኑ ነው፡፡ ለካ ዕዝራ በጀርባ በኩል ከሞት ጋር እያወጋ ነበር፡፡ ዕዝራ - ግጥምን ውድ በሆኑ ቃላት እያየሰ የሚቀኝ የኢትዮጵያ የሂስ አባት ነበር፡፡ በጥሞና ውስጥ ሆኖ ስራዎቹን ሊያበረክትልን ህልም ነበረውና እኛም ይህንን በማጣታችን እጅግ እንሸማቀቃለን፡፡ ባህር ማዶ ለሚገኝ አንድ ወዳጄ በመስከረም ወር ወመዘክር ተገኝቶ ዳሰሳውን ለመታደም የተኮለኮለውንና በሽኝቱ ወቅት የነበረውን የሰው ብዛት ባወጋሁት ጊዜ እንዲህ ነበር ያለኝ . . "Read about the true poet death. It is like this since mankind started writing" እውነት ይሆን'ዴ?

## ጠቡ . . .

ከገፅ 28 የዞረ

ተማሪዎችን አስታወሳለሁ፡፡

እርግጥ ነው፣ ብዙ የሚያሳዝኑ ነገሮች በአስመራ አይቻለሁ፡፡ እርግጥ ነው፣ ከተማዋ ያኔ መለስተኛ ጦር ግንባር ነበረች፡፡ እርግጥ ነው፣ በየጊዜው ሳይታሰብ በሻዕቢያ የሚተኮስ መድፍ ባልተጠበቀ ቦታ ያርፍ ስለነበረ ብዙ ሰዎች አልቀዋል፡፡ እርግጥ ነው፣ በደርግ ወታደሮች የተሰሩ ብዙ ግፎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ፣ የሕዝቡ ፍቅር አሸንፎኝ ነው የጦር መሳሪያ በተሸከመ የጦር አይሮፕላን፣ መሳሪያ ላይ ተቀምጬ ከተማዋን የለቀኩት፡፡ አሁንም ለአስመራ ትልቅ ፍቅር አለኝ፡፡ አሁንም አስመራን ከአዲስ አበባ ቀጥሎ እንደከተማዬ ነው የማያት፡፡ አሁንም ያንን ሕዝብ እንደ ሕዝቤ ነዉ የማየው፡፡ አሁንም ኤርትራውያንን ከተቀረው ኢትዮጵያዊ እንደተለዩ ተደርጎ ሲታይ አያስደስተኝም፡፡ በዚህ ምክንያት ነው የኤርትራን መገንጠል አጥብቄ የተቃወምኩት፡፡ አሁንም የምቃወመው፡፡ ለዚህ ነው፣ ከመረብ ደቡብ ይኖሩ የነበሩ ወደ ኤርትራ፣ ከመረብ ሰሜን ይኖሩ የነበሩ ደግሞ ከኤርትራ በግፍ እንዲባረሩ መደረጉ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነዉ የምለው፡፡ ለዚህ ነው፣ የባድመ ጦርነት የወንድማማቾች የእርስ በእርስ ጦርነት እንጂ ከውጭ ኃይላት ጋር የሚደረግ ጦርነት አይደለም የምለው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ መንቃት አለበት፡፡ የኢሕአዴግ መንግስት በባድመ ጦርነት እንዳደረገው አሁንም ኢትዮጵያውያንን ለመገበር እየተዘጋጀ ያለ ይመስላል፡፡ በኦሮሚያ፣ በጎንደር በመሳሰሉት ቦታዎች እንዳየነው፣ ህዝባችን በኢሕአዴግ ታጣቂዎች የሚታረደውና የሚገደለው አንሶ፣ እንደገና ከሻዕቢያ ጋር በሚደረግ ጦርነት የሚማገድበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ለኢሕአዴግ የጦርነት ጡሩምባ ጆሮውን ይደፍን ዘንድ እመክራለሁ፡፡ ሕወሃት/ኢሕአዴግ ለአገርና ለሕዝብ አስባለሁ፣ ለአገርና ለሕዝብ ደህንነት እቆማለሁ የሚል ከሆነ፣ አገር ማለት መሬቱ ሳይሆን ህዝቡ ነውና ህዝብን መጀመሪያ ያክብር፡፡ በሌላ በኩል ለዴሞክራሲ ቆመናል እያሉ፣ አለም በወንጀለኛነት የሚፈልገው የአረመኔው የኢሳያስ አፈወርቂን አገዛዝ መደገፍና እድሜውንም ለማራዘም ደፋ ቀና ለሚሉ ተቃዋሚ ነን ባዮችም፣ መልዕክት አለኝ፡፡ የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን የሚቃወም፣ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሚነቀፍና በሻዕቢያ የተዘጋጀ ፔቲሽኖችን ኢትዮጵያውያን እንዲፈርሙ አንዳንድ እንደ ግንቦት ሰባት ያሉ ድርጅቶች የቅስቀሳ ዘመቻ መጀመራቸው በጣም የሚያሳፍር ነው፡፡ ሻዕቢያ በአሁኑ ወቅት የኤርትራ ህዝብ ጠላት ነው፡፡ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ነው፡፡ ሻዕቢያ የሰብዓዊነት ጠላት ነው፡፡ ከሻዕቢያ ጎን በቆምን ቁጥር በሻዕቢያ እጅ ለሚፈሱ ደሞች ሁሉ ተጠያቂ ነው የምንሆነው፡፡ በመሆኑም ከሻዕቢያ ጋር የምናደረገውን ዳንኪራ በአስቸኳይ ማቆም አለብን፡፡

## በመንገድ

ከገፅ 20 የዞረ

መዳ-ወላቡ፣ ዋቸሞ፣ ስማቸውን ሰምታችኋቸው የማታውቋቸውን ተቋሞች ለምን ራስ ምታቱ እንዲሆኑ ፈቀደ? ለዴሞክራሲ ያለህ ተነሣሽነት ዩኒቨርሲቲ በማስፋፋት ካልተገለጸ - በምንም ሊገለፅ አይችልም፡፡" ያሏት ነገር ነበር ትዝ ያለችኝ፡፡ በወቅቱ ነገሩ አብግኖኝ ስለነበረ ሳያቸው ሁሉ አስታውሰዋለሁ፡፡

ገና ከመነሻው፥ የዩኒቨርስቲዎቹን መስፋፋት ጉዳይ ከሁከት ማብዛትና ራስ ምታት ከመሆን ጋር አያይዘውት፣ ዩኒቨርሲቲ ማብዛት ለዴሞክራሲ ያለ ተነሳሽነት መገለጫ ነው ይላሉ፡፡ ይህንን ቃል መጠይቃቸውን ከሰማሁ ጊዜ አንስቶ "ዴሞክራሲ ማለት የእኔ ልጅ" የሚል መጣጥፍ ቢጻፍ ብዬ አስብ ነበር፡፡ ይኸው ፍራንክፈርት ላይ የደረሰባቸውን ተቃውሞ ተመልክቼ፥ ድጋሚ ትዝ አለኝ፡፡ ስለትምህርት ጥራት እና ስለዜጎች አእምሯዊ ብልጽግና፣ ስለፍትሀዊ ምርጫ፣ ስለሀሳብን የመግለጽ ነጻነት፣ ስለሰዎች ተዟዙሮ የመስራት መብት፣ በጤና፣ በኢኮኖሚ እና በባህል ላይ ያሉትን መገለጫዎች ሁሉ ተተንትኖ ቢጻፍላቸው ተመኘው፡፡ ...'ኮርኒያ ኮርናስሜ ናስሜ ናስሜ' እያልኩ፡፡ ግን መች ስለማያውቁት ሆኖ?

ከዚያው ከፌስቡክ ሳልወጣ የፋና ብሮድካስቲንግ ገጽ ላይ ዘው ስል፥ የኤርትራና የኢትዮጵያን ጅምር ጦርነት በተመለከተ በወጣው የአቶ ጌታቸው ቢሮ መግለጫ ላይ፥ "የኤርትራ መንግስት በራሱ ህዝብ ላይ የሚያካሂደው አስከፊ ጭቆናና የመብት ጥሰት፥ በሰው ዘር ላይ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን በመንግስታቱ ድርጅት ሪፖርት መጠቀሱ ቀውስ ውስጥ ከቶታል፡፡" መባሉን ተመልክቼ እንደልማዴ ፈገግ አልኩ፡፡ ጠየቅኹም "የእነርሱስ ምን ሊባል ነው? ..."የራስ ፊስ አሪቲ ነው"? ወይስ "አመድ በዱቄት ይስቃል"?"

በዚህ ፈግጌ ሳላባራ ሌሎች ገጾች ላይ ስዟዟር፥ "አሰብን እናስመልሳለን" የሚሉ የኮካዎችን ጽሑፎች ተመልክቼ እንዳዲስ "ወይ ጉድ" አልኩ፡፡ "አሰብ የእኛ ናት" ብለው እንደአጀንዳ የያዙት ተቃዋሚዎችን 'ጸረ ሰላም ኃይሎችና አሸባሪዎች' በማለት ሲፈርጅ የነበረ እና፥ ነገሩን ለማለባበስ 'የራሳቸው ወደብ ሳይኖራቸው ያደጉ አገራት አሉ' በማለት ለሕዝብ ሲደሰኩር የከረመ፥ "አሰብን እናስመልሳለን" ሲል ከመስማት በላይ ሌላ ምን የኪራይ ሰብሳቢነት ስሜት ይኖራል? ራዕዩንስ እንዴት ደፍረው ይቀረጥፉታል? ብዬ ፈገፍ አልኩ፡፡ በማምታታት በዝሆኖች ልፊያ የዋሃን ወደሞት እንዲነዱ ነጋሪት እየተጎሰመ ነው፡፡

### 'ለምለሚቷ አገሬ'

መድረስ አይቀር ደረስንና እንደልማዴ በሰው አገር ልምላሜ ቀናሁ፡፡ የሰው ሀገር በታየ ቁጥር ትዝ የሚለን የለምለሚቷ አገራችን ጉዳይ "አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል"ን እና "መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ"ን ያስታውሰናል፡፡ የአፈሩ ገራገርነትና፣ የአየሩ መልካምነት ሲታይ ደግሞ ስንፍናችንን ይበልጥ ያጎላውና፥ ያንገበግባል፡፡ ሌላው የትራፊክ መንገድ አጠቃቀም ጉዳይ ነው፡፡ አሽከርካሪዎቹ ያላቸው ስርዓት፣ ትዕግስትና መናበብ ሲታይ ለአገር ይመኙታል፡፡

ሌላው ሳይጠቀስ መታለፍ የማይገባው ነገር፥ የቆሻሻ አወጋገድ እና የአካባቢ ንጽህና ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉም ሰው በሀላፊነት ከሚሳተፍባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ የአካባቢን ልምላሜ መጠበቅ፣ የትራፊክ መጨናነቅን ማቅለል፣ እና ንጽህና፥ ከኑሮ መሻሻል ጋር ሊሻሻሉ የሚችሉ ቢሆኑም፥ ከድህነትና ከሀብት ጋር የሚያያዝ ቀጥተኛ ነገር የላቸውም፡፡ ከግንዛቤ ስፋትና ከአመለካከት ለውጥ ጋር እንጂ!

ሰላም!

## የወቅቱ . . .

ከገፅ 7 የዞረ

አቀፉ ፍርድ ቤት በአፍሪካ ያለው ተቀባይነትና አስገዳጅነት ጥያቄ ውስጥ መውደቁን አሳይተዋል፡፡ ደቡብ አፍሪካም ለሮሙ ስምምነት የገባችውን ቃል በማጠፍ በሽርን ወደመጡበት በክብር ሸኝታለች፡፡

አለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በአልበሽር ምክንያት ከአፍሪካ መሪዎች ጋር የገባው መቃቃር ወደለየለት ሽኩቻ የተሸጋገረው እንደ አልበሽር ሁሉ በስልጣን ላይ የሚገኙትን የኬንያውን ፕሬዚዳንትና ምክትላቸውን በመክሰሱ ነው፡፡ ኡሁሩ ኬንያታና ምክትላቸው ዊሊያም ሩቶ የቀረበባቸውን ክስ በመቀበል የተጠረጠሩበትን ወንጀል አለመፈጸማቸውን ቢያስረዱም በአፍሪካ ህብረት ውስጥ የሚገኙ ጓደኞቻቸውን በመቀስቀስ ፍርድ ቤቱ አፍሪካዊያንን ብቻ ለማጥቃት የተዘጋጀ ተቋም በመሆኑ አፍሪካ ከፍርድ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ እንድትወጣ መስራታቸው አልቀረም፡፡

የሮሙ ስምምነትን ከፈረሙት አፍሪካዊያን አገራት የመጀመሪያዋ የነበረችው ኬንያ የባለሥልጣናቷን ክስ ተከትሎ ፊርማዋን መቅደዷን ማስታወቋም በፍርድ ቤቱ ስጋት የነበራቸው መሪዎች ከየአቅጣጫው ከአባልነት እንደሚወጡ ዝተዋል፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ፈራሚ ባትሆንም በፍርድ ቤቱ ላይ አፍሪካዊያንን ለማሳመጽ ጠንክራ ሰርታለች፡፡

ከሶስት ዓመት በፊት የአፍሪካ ህብረት የዙር መሪ የነበሩት ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ፍርድ ቤቱን ‹‹ዘረኛ›› በማለት መሰየማቸውም ፍርድ ቤቱ በአፍሪካ መሪዎች የተንሸዋረረ ዕይታ ውስጥ ለመውደቁ ማሳያ ነበር፡፡

October 1, 2013 (ADDIS ABABA) — Ethiopia has renewed its allegations that the International Criminal Court (ICC) is only targeting African leaders while ignoring cases in other parts of the world.

በ2005 ስለ ፍርድ ቤቱ የአገራቸውን አቋም ያብራሩት የውጪ ጉዳይ ሚንስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ፍርድ ቤቱ ከህግ ጉዳዮች በመነሳት ሳይሆን ፖለቲካዊ በሆነ መንገድ የአፍሪካ መሪዎችን እንደሚከስ በማስታወስ ‹‹ኢትዮጵያ አፍሪካ የራሷን የሆነ የህግ ተቋማት በመገንባት እንድትዳኝ ለማድረግ ጠንክራ ትሰራለች›› ብለው ነበር፡፡

‹‹የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካዊያን ይዳኛል›› በማለት በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ላይ የተከፈተው ዘመቻ በስልጣን ላይ በሚገኙ የአፍሪካ መሪዎች ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቷል፡፡

ከኃይለማርያም በኂላ የአፍሪካ ህብረትን የመምራት ዕጣ የደረሳቸው የቻዱ ፕሬዚዳንት ኢድሪስ ዴቢይ ‹‹በሁሉም የዓላማችን ክፍሎች ብዙ ነገሮች ተከስተዋል፡፡ ብዙ ግልጽ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ ነገር ግን፣ ግድ የሰጠው የለም›› በማለት ‹‹የፍርድ ቤቱ አይን ያረፈው በአፍሪካ ብቻ ነው›› ብለዋል፡፡

በአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ወቅትም የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዮዌሪ ሙሴቪኒ አለም አቀፉን ፍርድ ቤት በተመለከተ አጀንዳ እንደሚያሲይዙ በማስታወቅ “I WILL BRING A MOTION TO THE AFRICAN UNION’S NEXT SESSION. LET THEM (WESTERNERS) STAY WITH THEIR COURT,” ማለታቸውን የኬንያው ዴይሊ ኔሽን ዘግቦ ነበር፡፡

ሙሴቪኒ እንደዛቱትም ፍርድ ቤቱን አጀንዳ በማድረግ ለህብረቱ ተሰብሳቢዎች አቅርበዋል፡፡ በዚህ ስብሰባ መሪዎቹ ከፍርድ ቤቱ መውጣትን በመደገፍ ከተደረጉ ንግግሮች የሚበዙት ያነሷቸው መከራከሪያዎች ፍርድ ቤቱ አፍሪካዊያንን ለማጥቃት፣ የአህጉሪቱ ዜጎች ፍትህን በአህጉራቸው ማስፈን ባለመቻላቸው በተልዕኮ ሊያሰፍኑልን በተነሱ ‹‹እናውቅላችኂለን›› ባዮች የተመሰረተ በማለት አብጠልጥለውታል፡፡

የሙሴቪኒ አጀንዳ እስካሁን አንድ ወጥ አቋም ተይዞበት ለውሳኔ ባይቀርብም የህብረቱ መሪዎች ሆላንድ በሚገኘው ፍርድ ቤት መዳኘትን የሚያስቀምጠውን የሮም ስምምነት ከቀድሞዎቹ የቅኝ ግዛት ውሎች ነጥለው እንደማይመለከቱት አሳይተውበታል፡፡

በቅርቡ የኤርትራን የሰብዓዊ መብት አከባበር የተመለከተው የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በምስራቅ አፍሪካዊቷ አገር እጅግ የሚዘገንኑ ኢ-ሰብዓዊ ወንጀሎች በዜጎች ላይ ሲፈጸሙ መቆየታቸውን እንደደረሰበት በመግለጽ ጉዳዮን ለአለም አቀፉ ፍርድ ቤት መምራቱን አስታውቋል፡፡

የፍርድ ቤቱ ጠበቆችም የደረሳቸውን ሰነድ ተመልክተው የኤርትራውን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳይስ አፈወርቂን ጨምሮ የተወሰኑ ከፍተኛ ባለስልጣናትን በተለያዩ ወንጀሎች ሊከሷቸው እንደሚችሉ በስፋት ይታመናል፡፡ አሁን ጥያቄው ፍርድ ቤቱ የኤርትራን መሪዎች የሚከስ ከሆነ የአፍሪካ መሪዎች ለሁኔታው የሚሰጡት ምላሽ ምን ይሆናል የሚለው ነው፡፡

ምንም እንኳን ኤርትራ የአፍሪካ ህብረት አባል አገር ባትሆንም አፍሪካውያን መሪዎች ከዚህ ቀደም ፍርድ ቤቱ አፍሪካዊያንን ለማጥቃት በፖለቲካ መነሳሳት የተፈጠረ ነው ሲሉት የነበረ በመሆኑ አፍሪካ ውስጥ ለምትገኘው ኤርትራ ይህ እንደሚሰራ በማመን ድጋፋቸውን ለአልበሽርና ለኡሁሩ እንደሰጡ ለኢሳይያስ ይሰጡ ይሆን?

የኤርትራውን መሪ በተደጋጋሚ በጸብ አጫሪነት፣ ተቃዋሚዎችን አስታጥቃ በመላክና ጦርነት በመክፈት የሚከሰው የአቶ ኃይለማርያም አስተዳደርስ በፍርድ ቤቱ ላይ ሲያራግበው የነበረውን አቋም በማለሳለስ የኢሳይያስን መከሰስ ይደግፍ ይሆን ወይስ መርሁን ለፖለቲካ ጠላትነት ሳያውል ኢሳይያስ የተከሰሱት በፖለቲካ መነሳሳት (political Motivation) ነው በማለት የኤርትራን መከሰስ እንደ ጣልቃ ገብነት ይመለከቱታል?

ከወዲሁም የኢትዮጵያ መንግስትን ቀጣይ አቋም የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በቅርቡ በድንበር አካባቢ ለተፈጠረው ግጭት የኢትዮጵያ መንግስት የሰጠው ምክንያት ‹‹በተባበሩት መንግስታት የወጣውን ሪፖርት ተከትሎ የኤርትራ መንግስት ትኩረት ለማስቀየስ ግጭት ቀስቅሷል›› ማለቱ ተሰምቷል፡፡ አንድ ሪፖርት ወጣ ተብሎ ጦር መምዘዝ አስገራሚ የፖለቲካ ትንተና ቢመስልም ኢትዮጵያ በሪፖርቱና ሪፖርቱ ይዞት በሚመጣው ውጤት ከወዲሁ ደስተኛ መስላ መቅረቧን ያሳያል፡፡


በጋሻው መርሻ የተጻፈው ‹‹እንጸባራቂው ኮከብ›› የሚል መጽሐፍ ገበያ ላይ ዋለ፡፡ መጽሐፉ ስለፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ታሪክና ሥራ በስፋት የሚዳስስ ሲሆን የመሸጫ ዋጋው 81፡00 ብር ነው፡፡ መጽሐፉም በሁሉም የመጽሐፍ መደብሮች ይገኛል፡፡





ፍርድዉቃል ጓጉሜ

# ቅጥ ያጣው ቤት



*ከሪዮ ኦሎምፒክ የኢትዮጵያ የማራቶን ቡድን ምርጫ ውስጥ የተዘለለው ቀነኒሳ በቀለ*

የ2016ቱ የኦሎምፒክ ውድድር በሀገረ ብራዚል ሊጀመር የወራት እድሜ ብቻ ነው የቀረው፡፡ ይህ በየአራት አመቱ አንዴ የሚከናወነው የኦሎምፒክ ውድድር በመጣ ቁጥር ሰርክ ውጤትን በሚያስመዘግቡልን፣ በደስታ ውቂያኖስ ውስጥ በሚያሰምጡን ብርቅዬና ጀግና አትሌቶቻችን ሳቢያ እኛም ይህን ውድድር በጉጉት የምንጠብቅ ህዝቦች ሆነናል፡፡ አዎ! ደግሞም እስከ ለንደኑ የ2012ቱ ውድድር ድረስ እኚህ ጀግና አትሌቶቻችን የጠበቅነውን አሳጥተውን አያውቁም፡፡

በ2012ቱ የለንደን ኦሎምፒክ ላይ የኢትዮጵያውያን ውጤታማነት እና አስተማማኝ ብቃት በእጅጉ ወርዶ የታየ ሲሆን ከጥቂት ምርጥ አትሌቶቻችን በስተቀር ለወትሮ የኛ የነበሩ ርቀቶች ላይ እንኳን ሳይቀር ተፈላጊውን ውጤት አጥተናል፡፡ በተለይ ‹‹አረንጓዴው ጎርፍ›› የሚል ቅፅል ስም የወጣለት የአትሌቶቻችን የቡድን ስራ በእጅጉ ቀዝቅዞ ታይቷል፡፡

በጀግና አትሌቶቻችን መሃል የነበረው የመተካካትና ውጤትን የማስቀጠል ሒደት ራሱ አደጋ ውስጥ እንደሆነ በለንደኑ ውድድር ላይ ታይቷል፡፡ ከዚህ በፊት በወንዶች ምሩፅ ይፍጠር በሃይሌ ገ/ስላሴ፣ ሃይሌ ገ/ስላሴ ደግሞ በቀነኒሳ በቀለ ባግባቡ ሲተካኩ ያስተዋልን ሲሆን በለንደኑ ኦሎምፒክ ግን በቀጣይ የቀነኒሳ ተተኪ ማን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አልተቻለም፡፡ ‹ቀነኒሳን ማን ይተካዋል› የሚለው ጥያቄም ዛሬም ድረስ ምላሽ አላገኘም፡፡ በሴቶቹም ረገድ ያለው ሂደት ተመሳሳይ ነው፡፡ ደራርቱ ቱሉ በነ ጌጤ ዋሚና ብርሃኔ አደሬ፤ እነ ጌጤና ብርሃኔ ደግሞ በነጥሩዬና በነመሰረት በሚገባ የተተኩ ሲሆን ዛሬ ላይ ግን ‹የነጥሩዬና የነመሲ ተተኪ ማን ነው› ለሚለው ምንም ምላሽ የለም፡፡

ይህ የተተኪ እጥረት በሰፊው በሚታይበትና ለዚህ ክፍተት እልባት ከማግኘት ተቆጥቦ እጁን አጣጥፎ የተቀመጠው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ይባስ ብሎ ከሪዮ ኦሎምፒክ ጋር በተያያዘ እጅግ አሳፋሪ የሆነ ስህተትን መስራቱ ‹‹ኧረ ጎበዝ ምን አይነት ሰዎች ነው በየዘርፉ እየመሩን ያሉት›› ያስብላል፡፡

የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ለሪዮ ኦሎምፒክ ሀገርን ይወክላሉ ብሎ አትሌቶችን የመረጠበት ሂደት በጣም ኋላ ቀርና አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ አንድ በአግባቡ ማሰብ ከሚችልና ንቃተ ህሊና ካለው ሰው የማይጠበቅ ነው፡፡ አዎ! ከረጅም ጊዜ ጉዳት አገግሞ ወደ ሩጫው የተመለሰውና በቅርቡ እንግሊዝ ሃገር በተደረገ የማራቶን ውድድር ውጤታማ የነበረው ብርቅዬ አትሌታችን ቀነኒሳ በቀለን ፌዴሬሽኑ ከሪዮ ኦሎምፒክ ውጪ ማድረጉ ሀገራዊ ቁጣን የቀሰቀሰ ሲሆን በተለይ የሀገራችን ስመ ጥር አንጋፋ እና ወጣት አትሌቶች በዚህ በፌዴሬሽኑ የተሳሳተ ተግባር ዙሪያ መጠነ ሰፊ የሆነ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፡፡

ይህ ፌዴሬሽን በርግጥም ያልተረዳቸው መሰረታዊ እውነታዎች አሉ፡፡

አንደኛ፡- እስከዛሬ ለሀገራችን በየተሳተፉበት ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ የሚያመጡና ባንዲራችን ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረጉ አትሌቶቻችን እስከዛሬ ላመጡት ስኬት ባለድርሻው አካል ራሳቸው አትሌቶቹ ብቻ ከመሆናቸው አንፃር ለእነርሱ በጣም ተገቢ የሆነ ክብርን መቸር አለበት፡፡ አዎ፣ እስከዛሬ በግላቸው ጥረት ነው እንጂ በፌዴሬሽኑ ድጋፍ አይደለምና በአለም አቀፍ ደረጃ ስኬታማ የሆኑት፡፡

ሁለተኛ፡- እነዚህን ብርቅዬ አትሌቶቻችንን በግላቸው ጥረት ባሳኩት ገድል ነው የኢት/አ/ፌዴሬሽን አሁን ላይ ያገኘውን ተቀባይነት ያገኘውና የገዘፈ ተቋም መሆን የቻለው፡፡ እንጂ ያለእነዚህ አትሌቶቻችን የፌዴሬሽኑ ቤት እኮ ኦና ነው፡፡

ሶስተኛ፡- አይደለም በቅርቡ ተወዳድሮ ውጤታማ መሆኑ ቀርቶ ጭራሽ ባይወዳደርና ወደ ሪዮ ማቅናት ባይፈልግ እንኳን ሌላው ቀርቶ ሌሎች አትሌቶቻችን ላይ ከሚዘራው የአሸናፊነት ሥነ-ልቦና አንጻር በግድ አግባብቶ ወደ ሪዮ ኦሎምፒክ ይዞ መሄድ ሲገባው ፌዴሬሽኑ እንዴት እርሱን ከምርጫው ውጪ ያደርጋል፡፡ …ሌላው ሁሉ ነገር ቢቀር እንኳን እንዴትና ስለምን የእስከዛሬ ውለታው ይረሳል? …እንዴት ይህን መሰል አሳፋሪና አስነዋሪ ተግባር ይፈጸማል? …በርሱ ቦታ የተመረጡት አትሌቶችስ በምን አይነት ሥነ-ልቦና ውስጥ ሆነው ተወዳድረው ነው ተፈላጊውን ውጤት ሊያመጡ የሚችሉት? …እስከመቼስ ነው ፍሬያማ የሆነው አትሌቲክሳችንን መሰል ሰዎች የሚመሩት? …መቼስ ነው አትሌቲክሳችን ስፖርቱን ጠንቅቀው በሚያውቁ፣ የተሻለ እውቀት ባላቸውና ለታሪክና ለትውልድ ደንታ ቢስ ባልሆኑ ሰዎች የሚመራው?

የሚገርመው ትላንት ከነደራርቱ፣ ከነሃይሌ ጋር እየተፎካከሩ ሲሮጡ የነበሩት የሌላ ሀገር ዜጎች የሆኑት እነ ሒሻም ኤልግሩዥ፣ ፓውላ ራድክሊፍ እና ማሪያ ዣቦ ዛሬ ላይ በሀገራቸው አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስር እየሰሩ፣ ተቋማቱን እየመሩና ካላቸው የካበተ እውቀትና ልምድ አንፃር ሀገራቸውንንና ስፖርቱን በሚገባ እያገለገሉ ነው፡፡ እኛስ ሀገር …? …እኛ ሀገርማ ጭራሽ ሮጠው በማያውቁና በአስተውሎት ነገሮችን በማይተገብሩ ሰዎች ነው የአትሌቲክሳችን እጣ ፈንታ የሚወሰነው፡፡

አዎ! ዛሬ ላይ ቀነኒሳ በቀለ አለመመረጡን ተከትሎ በርካቶች የአትሌቲክስ ፌዴሬሽናችንን ምልዐተ ጉድለት ነጥለው እንዲያዩ አደረጋቸው እንጂ ላስተዋለው ሰው ፌዴሬሽኑ ዘንድ ከፍተኛ ጉድለት እንዳለበት የሚያስታውቀው ገና የዛሬ አራት እና አምስት አመት ብርቅዬ አትሌቶቻችንን የሚተኩ ውጤታማ አትሌቶችን ማፍራት ባለመቻሉ ነበር፡፡ ያው ሁላችንም በተጠናወተን የወረት አባዜ ሳቢያ የውድድር ዋዜማ፣ መባቻ እና ማግስት ላይ ብቻ ለነገሮች ትኩረት ሰጥተን ከዛ ጉዳዩን እንረሳዋለን እንጂ ሁላችንም ይሄን ጉዳይ ስራዬ ብለን ብንይዘው ኖሮ ይህ የፌዴሬሽኑ አመራር ከለንደን ኦሎምፒክ በኋላ በስልጣን ላይ መቆየት አልነበረበትም፡፡ አዎ! ሌላው ቀርቶ ከዛ ኦሎምፒክ ጀምሮ እስካሁን በነበሩት አራት አመታት ውስጥ ፌዴሬሽን አንድም ተጠቃሽ ስራ አለመስራቱ ይባስ ብሎም ጥፋቱ መደራረቡ ይህንን እውነታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በአጠቃላይ ግን ይህ ፌዴሬሽን ቀነኒሳን ያልመረጠበትን አካሔድ የሚሰማው ተቃውሞ በሪዮው ኦሎምፒክ ላይ ከሚመዘገቡ ውጤቶች በኋላ ቢያንስ ለአንድ እና ሁለት ወር የመወያያ ርዕስ ሆኖ ይቀጥል ይሆናል፡፡ ከዛ በኋላ ግን በቃ ልክ እንደስከዛሬ ጉዳዮች ሁሉ ይረሳል በቃ፡፡ ነገር ግን፣ ነገሮች በዚህ መልኩ መጓዝ የለባቸውም፡፡ አዎ! አትሌቶችም ህብረታቸውን አጠናክረውና በያገባኛል ስሜት ተውጠው፣ ህዝቡም በአንድ ቃል የጋራ መስማሚያ አቋም ላይ ደርሶ ከሪዮ ኦሎምፒክ በኋላ ይህ የፌዴሬሽኑ አመራር አባላት በሙሉ ከኃላፊነታቸው መነሳትና ስልጣነ መንበሩን ስፖርቱን ጠንቅቀው በሚያውቁ ግለሰቦች እንዲያስረክቡ መደረግ አለበት፡፡